# ስለኢስላም፡ ለማወቅ
# በአማርኛ፡ ቋንቋ

# التعريف بالإسلام

باللغة الأمهرية


تأليف : الشيخ محمد ساني حبيب

تحقيق : محمد سعيد فقادو



ደራሲ

ሐጅ፡ ሙሐመድ፡ ሣኒ

አሣታሚና አዘጋጅ

ሐጅ ሙሐመድ ሰይድ

ⓒ دار أبوالقاسم للنشر ، ١٤١٦هـ

*فهرسة مكتبة الملك فهد الوطنية أثناء النشر*

حبيب ، محمد سامي

التعريف بالإسلام / تحقيق محمد سعيد فقادو ـ جدة.

١٣٤ صفحة ؛ ٢١ × ١٤ سم

ردمك ٠-٥٦-٧٩٢-٩٩٦٠

النص باللغة الأمهرية

١ - الدعوة الإسلامية  ٢ - الوعظ والإرشاد  ٣ - التربية الإسلامية

أ - فقادو ، محمد سعيد ( محقق )  ب - العنوان

ديوي ٢١٣  ١٦/٢١٩٣

رقم الإيداع : ١٦/٢١٩٣

ردمك : ٠-٥٦-٧٩٢-٩٩٦٠

ኣቡል ቃሲም

የእስልምና መፅሐፍ መደብር

ፖ.ሣ.ቁ 6156

ጅዳ 21442

ስ/ቁ 6714793

ሳዑዲ አረቢያ

# ማ ው ጫ


| | | ገጽ |
|---|---|---|
| ምዕራፍ ፩ | ፈጣሪ/አላህ ስለመኖሩ በዕውቀት ላይ የተመሠረቱ ማስረጃዎች … … … … … … … … … | 7 |
| ምዕራፍ ፪ | ከአንድ አላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም … … … … … | 19 |
| ምዕራፍ ፫ | አላህ ለሰው ልጅ መመሪያ ሲሰጥ ስለመቆየቱ … … … … | 23 |
| ምዕራፍ ፬ | የቁርአን ይዘት ከአላህ ለሰው ልጅ የወረደ መመሪያ ለመሆን ማረጋገጫ ነው … … … … … | 25 |
| ምዕራፍ ፭ | እስላም ማለት ምን ይሆን ? … … … … … … … | 32 |
| ምዕራፍ ፮ | በዲን (በሃይማኖት) ማስገደድ የለም … … … … … | 45 |
| ምዕራፍ ፯ | የአላህን አንድነትና የሙሐመድን መልእክተኛነት መመስከር … … … … … … … | 53 |
| ምዕራፍ ፰ | ሶላት … … … … … … … … … … … | 57 |
| ምዕራፍ ፱ | ዘካት … … … … … … … … … … … | 77 |
| ምዕራፍ ፲ | ሲያም (ጾም) … … … … … … … … … | 86 |
| ምዕራፍ ፲፩ | አልሀጅ … … … … … … … … … … | 103 |
| ምዕራፍ ፲፪ | መልእክት … … … … … … … … … … | 120 |

# መ ግ ቢ ያ

በአላህ ርኅሩኅና አዛኝ በሆነው
ስም ፤ እጀምራለሁ ።

ማንኛውም ጽሑፍ እንዲዘጋጅ የሚያነሳሱና የሚገፋፉ ምክንያቶች እንዳሉት ሁሉ ይህ ጽሑፍ የተዘጋጀበትም የራሱ የሆነ ምክንያት አለው ። ቁም ነገሩ እነዚህ ምክንያቶች ሊከሰቱና ጽሑፉንም እንዲዘጋጅ ለማድረግ የሚበቁት የአላህ (ጥራትና ልዕልና የርሱ ይሁን) ፈቃድ ሲሆን ብቻ ነው ። አላህ ሲፈቅድ በጣም የሚያስገርሙ ነገሮች እንደሚከሰቱ ሁሉ ያለ እርሱ ፈቃድ የሚሆን ከተውንም ምንም ነገር አይኖርም ።

ይህን ጽሑፍ ለማዘጋጀት ምክንያት የሆኑን የኢስላም ሃይማኖትን በሚመለከት የሚገኙ መጽሐፎች አብዛኞቹ በዓረብኛ ቋንቋ ፡ አልፎ አልፎም በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተዘጋጁ በመሆናቸውና በአማርኛ የተዘጋጁ እምብዛም አለመኖራቸው ያሳሰበን በመሆኑ ነው ። የዓረብኛውንና የእንግሊዝኛውን ጽሑፍ አንብበው ለመረዳት የማይችሉ ቁጥራቸው በጣም ብዙ ለሆኑት ምዕመናን መልዕክት ለማድረስ ያለው የተሻለ አማራጭ አማርኛ ቋንቋ ነው ።

ስለዚህ ይህ ጽሑፍ በመጀመሪያ ደረጃ በሌላ ቋንቋ የእስላምን ሃይማኖት ዋና ዋና መልዕክትና መሠረታዊ ሕጎችን አንብቦ ለመረዳት ዕድል ላላገኙ ምዕመን እንዲረዳ ተብሎ በአጭሩ የተዘጋጀ መሆኑ ታውቆ የእስላም ሃይማኖት (ዲን) መልዕክትና ትምህርት ፤ ሥርዓትና ሕግ ይኸው ብቻ እንደሆነ ሊታሰብ እንደማይገባና ጽሑፉ እንደ መንደርደሪያ ለጀማሪዎች የተዘጋጀ መሆኑን ከወዲሁ ለማስታወስ እንፈልጋለን ።

ይህም ስለተባለ ስለእስላም ሃይማኖት ጠለቅ ያለ ዕውቀት ያላቸው ምሁራን ይህን ጽሑፍ ሊያነቡት አይገባም ማለት አይደለም ። በተጻራሪው ቢያነቡት ጽሑፉን ለማደርጀትና ተጨማሪ አስተያየቶችን ለማከል ፡ ራሳቸውም ቢሆኑ ሕብረተሰባችን ሊረዳው በሚችል በሀገሬው ቋንቋ ተጨማሪ ጽሑፎችን አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ስለሚገፋፋቸው ማንበባቸው ጠቃሚ ነው ።

ይህ ጽሑፍ ከአንድ ደራሲ ሃሳብ ፈልቆ የተዘጋጀ ሳይሆን የተለያዩ የእስላም ሃይማኖት ምሁራን ካዘጋጁዋቸው ልዩ ልዩ መጽሐፎች ከአስተሳሰባቸውና ካቀራረባቸው አንጻር እየተመረጠ በማቀናጀት አብዛኛውን ጊዜ በመተርጎም ፣ አልፎ አልፎም በማብራራትና ሃሳቡን አጠቃልሎ አጠር ባለ መልክ በማቅረብ ብቻ በመወሰን የተዘጋጀ ነው ።

ጽሑፉ እየሰፋ ሄዶ በቀላሉ ለማቅረብ እንዳያስቸግርና ለአንባቢያንም እንዳያሰለች በመፍራት በተቻለ መጠን ለዛው ሳይጠፋ በማሳጠር ፣ ሰፋ ያለ ሥፍራ ሊወስዱ የሚችሉ ፀሎቶችን (ዱዓዕ) ከማስፈር በመቆጠብ ፣ በጣም አስፈላጊ መስለው የታዩንን ብቻ አቅርበናል ። አልፎ አልፎም ጣዕማቸውን ለማስተላለፍ በመሠረታዊ ቋንቋው ፣ በዓረብኛ መጠናት የሚገባቸውን የቁርአን አንቀጾችና የፀሎት መልዕክቶች ለአንባቢው እንዲረዱ በዓረብኛ እንዲሠፍሩና ትርጉማቸው እንዲቀርብ ተደርጎዋል ። የቁርአኑን አንቀጽ መልዕክት በአማርኛ ለማቅረብ ጥንቃቄ በማስፈለጉ በአማርኛ "የቅዱስ ቁርአን" ትርጉም ከቀረበበት መጽሐፍ ትርጉሙ እንዳለ ተገልብጦ ተወስዶዋል ።

የጽሑፉን አቀራረብ በሚመለከት አንድ ሰው ስለሃይማኖቱ ይዘት ከማወቁ በፊት ለራሱም ሆነ ለመላው ዓለም ባለቤትና ፈጣሪ ያለው መሆኑን ማመን ስለሚገባ ጥርጣሬው ካለው ለማስወገድ የሚረዱ የአካባቢን ተጨባጭ ምልክቶች በማስረጃነት በማቅረብ አእምሮውን ለመቀስቀስ የሚረዳ ትንተና ቀርቦዋል ።

ለመላውዓለም(ለዩኒቨርስ) ከአንድ አላሕ በቀር ሌላ ባለቤት ሊኖረው የማይችል መሆኑን የሚያስረዱ የአካባቢ ማስረጃዎችና ምልክቶችን በማቅረብ ማብራሪያ ተሰጥቶ አንባቢ ይበልጥ እንዲያስብበት የሚገፋፉ ጽንሰ ሃሳቦች ቀርበዋል ።

አላህ (ጥ. ል. የ. ይ) አንድነቱንና አጋር የሌለው መሆኑን የሚያስተምሩ መልዕክተኞችን የላከና ልንገዛለትና ልንከተለው የሚገባ የርሱ ፈቃድ ምን እንደሆነ እንድናውቅ መመሪያ የሰጠ ለመሆኑ ፣ በየዘመኑ ከነበሩትና ከተላኩት መልዕክተኞች አንዱና የመጨረሻው ሙሐመድ (ሰልላ አላሑ ዓለይሒ ወሠላም) መሆናቸውና ቁርአንም ከአላሕ በመመሪያነት የተሰጣቸው ስለመሆኑ ተብራርቶዋል ።

ቁርአን የአላህ (ጥ.ል.የ.ይ) መልዕክት ስለመሆኑ ዋናው ማስረጃ ይዘቱ መሆኑን የሚያስረዱ ምሳሌዎችን በመውሰድ ለማስረዳት ተሞክሮዋል ።

በየዘመኑ ከአላሕ (ጥ.ል.የ.ይ) የተላኩ ሃይማኖቶች (ዲኖች) በሙሉ ይዘታቸው የሰውልጅ ራሱን ለአላህ ፈቃድ እንዲያስገዛ የሚመሩ መሆናቸውና "እስላም" ማለትም ይህንኑ የሚያንፀባርቅ ስለመሆኑ ተብራርቶዋል ።

በነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.አ.ዓ.ወ) አማካኝነት የተላከው የእስላም ሃይማኖት (ዲን) በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊስፋፋና በአሁኑም ጊዜ እየተስፋፋ እንዲሄድ የሚያደርገው ይዘቱ መሆኑን በማስረዳት ፣ ለመስፋፋቱ ግንባር ቀደም ሚና የተጫወተው ኃይል ነው የሚለው አመለካከት መሠረተ ቢስ መሆኑ ተገልጾዋል ።

ከስድስቱ የእስላም የዕምነት ጽንሰ ሐሳቦች (አርካኑል ኢማን) ባሻገር በተግባር የሚተረጎሙ አምስቱ የእስላም መሠረታዊ ሕጎች (አርካኑል እስላም) ተብለው የሚታወቁትን አንድ በአንድ በመውሰድ አንባቢ በተግባር ሊተረጉማቸው በሚችልበት መልክ በቂ ገለጻ ተደርጎባቸዋል ።

የአላሕ (ጥ. ል. የ. ይ) መልዕክት የሆነውን የእስላም ሃይማኖት (ዲን) በማድረሳቸው ነቢዩ ሙሐመድና (ሰ. አ. ዓ. ወ) አብረዋቸው የነበሩት ተከታዮቻቸው (ሰሃበሕ) የደረሰባቸውን ግፍና የእነርሱን ቆራጥ አቋም ለማስረዳት ተሞክሮዋል ። የአላህን (ጥ. ል. የ. ይ) መመሪያ ተቀብለው ተግባራዊ ለሚያደርጉ ምዕመናን አስፈላጊውን እርዳታ የሚያደርግላቸውና ፣ የዚህን ዓለምና የመጭውንም ዓለም ኑሮዋቸው የተሳካ እንዲሆንላቸው ለማድረግ አላሕ ቃል የገባ መሆኑ ተብራርቶዋል ። በዘመናችን የምንገኝ የሙስሊሞችን የእምነት ጥንካሬ አንጻራዊ በሆነ መልክ ለማመልከትና የአላሕን ፈቃድ አለመፈጸም ምን ሊያስከትል እንደሚችል ተጠቁሞዋል ።

በመጨረሻም በአንባቢውና በሙስሊም ሕብረተሰባችን ላይ ሃይማኖቱ (ዲኑ) ምን ኃላፊነት እንደጣለና ኃላፊነታችንን ለመወጣት ምን ማድረግ እንደሚገባን በመውላና ሼኽ ሙሐመድ ኢልያስ ጽሑፍ የተሰጠውን የመፍትሔ መልዕክት ለአንባቢ በማቅረብ ግዴታውን ለመወጣት የራሱን ጥረት እስካደረገ ድረስ አላህ ስለሚረዳው እንዲበረታ አስተያየት ሠፍሮ በዚህ ጽሑፍ የቀረበው መልዕክት ያበቃል ።

በዚህ ጽሑፍ የተሳሳተ መልዕክት ለአንባቢ እንዳይቀርብ በማሰብ በሀገሪቱ ካሉት ስመ ጥሩ የእስላም ሃይማኖት (ዲን) ምሁራን ከእነ ሐጂ ሙሐመድ ሳኒ ሐቢብ ፣ ወኢትዮ

ጵያ የእስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ጉባኤ ሊቀ መንበርና ከሌሎችም በርካታ የሃይማኖት ምሁራን አስተያየት ለማግኘትና ለማሳረም ጽሑፉ ቀርቦላቸው ሃሳባቸውን በማግኘት ጥረት እንዲኖረው ተደርጎዋል ።

ይህን ጽሑፍ ለማዘጋጀት ላበረታቱን ፣ በሞራልና በሃሳብ ለረዱን ፣ አንብበው ለማ ረምና ለማስተካከል ለተባበሩን ፣ የእጅ ጽሑፉን ታይፕ በማድረግና በማሳተም ለረዱን ፣ እንዲሁም የማባዣ እስቴንስልና ወረቀት በነጻ ለለገሱን በሙሉ የነቢዩን ስልል አላሁ ዓይለሂ ወሰለም (ሰ.አ.ዓ.ወ) መልዕክት ለማድረስ አስተዋጽኦ ያደረጉ ስለሆነ አላሕ ፣ ጥራትና ልዕልና የርሱ ይሁን ፤ (ጥ.ል.የ.ይ) እዝነቱንና ርሕራሔውን እንዲለግሥልን እንለምናለን ። ከሁሉም በላይ ደግሞ ጊዜያቸውን መስዋዕት በማድረግ ባላቸው ዕውቀትና ችሎታ ይህን የትርጉም ሥራ ለመሥራት ለተባበሩን ምሁራን ከፍ ያለ ምስጋና እና ቀርባለን ።

በዚህ ጽሑፍ መልዕክት ተጠቃሚዎችና በተግባር የምናውል እንድንሆን አላህ ፣ ጥራትና ልዕልና የርሱ ይሁን ፤ ይርዳን ። አሚን!!!

የሰው ልጅ አእምሮ እየዳበረ በመምጣቱ በአሁኑ ወቅት በደረሰበት ደረጃ በዚህ ዓለም ካሉት የተፈጥሮ ክስተቶች ብዙ ሳይታወቁ የቆዩትን ጉዳዮች በምርምር ሊያገኝ ችሎዋል ። ለሰው ልጅ የተሰጠው የዕውቀት ደረጃ በጣም ዝቅተኛ ስለመሆኑ አላህ ሲናገር እንዲህ ብሎዋል ።

وَمَآ أُوتِيتُم مِّنَ ٱلۡعِلۡمِ إِلَّا قَلِيلٗا الإسراء ٨٥

ትርጉሙም"ከዕውቀትም ጥቂትን እንጂ አልተሰጣችሁም" ፣ (ም ፲፯ ቁ ፹፭) ይህም ሆኖ ባለው የዕውቀት ደረጃ ባደረገው ምርምር የተገኘው ውጤት ማንኛውም ነገር እጅግ አስገራሚና ረቂቅ ሆኖ መገኘቱ እንዲሁም የራሱ የሆነ ሥርዓትና ደንብ ኖሮት እርሱን የሚከተል ሆኖ መገኘቱ ባለቤት ያለው መሆኑን ለተመራማሪው ይበልጥ እያረጋገጠለት መጥቶዋል ።

ከዚህ ቀጥሎ ስለ ፈጣሪ መኖር አንዳንድ ማስረጃዎችን በማቅረብ አንባቢ እንደ አእምሮው ብስለት ደረጃ የራሱን ነፃ ውሳኔ እንዲሰጥ እንጋብዛለን ።

## 1.2. ይህ ዓለም (ዩኒቨርስ) ስለ አላህ መኖር ማስረጃ ነው ፤

የዚህ ዓለም አፈጣጠር ስለ አላህ መኖር ታላቁ ማስረጃ ነው ። የምንኖርበት ምድርና በሰማይ ኅልተው የሚታዩ የከዋክብት ጥርቅም አተኩረን እንድናስተውላቸው ያስገድዱናል ። የማስተዋሉ ውጤት እድናቆትን የሚያሳድር ብቻ ሳይሆን የሠሪያቸውን ታላቅነት የሚያረጋግጥ ይሆናል ።

ቅዱስ ቁርአን የሰው ልጅ ዓለምን ፣ ሰማያትና ምድርን አጠቃልሎ በአንክሮ እንዲመለከት የሚጋብዙ በርካታ አንቀጾች ይዞዋል ። ከጥርጣሬ ነጻ ሆኖ ዕምነቱን ለማጠናከር እንዲችል ስለ ዓለም ምሥጢር ግንዛቤ እንዲኖረው ያነቃቃል ። አላህ (ሰብሓነሁ ወተዓላ)[3] እንዲህ ይላል ።

قُلِ ٱنظُرُواْ مَاذَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۚ وَمَا تُغۡنِي ٱلۡأٓيَٰتُ وَٱلنُّذُرُ عَن قَوۡمٖ
لَّا يُؤۡمِنُونَ يونس ١٠١

"በሰማያትና በምድር ያለውን (ታምር) ተመልከቱ ፣ በላቸው ታምራቶችና አስፈሪዎችም ለማያምኑ ሕዝቦች አይጠቅሙም" ። (ም ፲ ቁ ፻፩)

أَوَلَمۡ يَنظُرُواْ فِي مَلَكُوتِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَمَا خَلَقَ ٱللَّهُ مِن شَيۡءٖ وَأَنۡ عَسَىٰٓ
أَن يَكُونَ قَدِ ٱقۡتَرَبَ أَجَلُهُمۡۖ فَبِأَيِّ حَدِيثِۭ بَعۡدَهُۥ يُؤۡمِنُونَ الأعراف ١٨٥

"በሰማያትና በምድር ግዛት ውስጥ ከማንኛውም ነገር አላህ በፈጠረውም ሁሉ ፣ የሞት ጊዜያቸውም በእርግጥ በቅርቡ የሚፈራ መሆኑን አያስተውሉምን ? ከርሱም (ከቁርአን) ወዲያ በየትኛው ንግግር ያምናሉ ።" (ም ፲፯ ቁ ፻፹፭)

خَلَقَ ٱللَّهُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ بِٱلۡحَقِّۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَةٗ لِّلۡمُؤۡمِنِينَ
العنكبوت ٤٤

ቁርአን ፈጣሪ መኖሩን የሚክድ ሰው ዓለምንና በውስጡዋ የሚገኘውን ደንብና ሥርዓት ፣ ምስጢሯንም አተኩሮ ካስተዋለ ፈጣሪ ያላቸው መሆኑን የሚጠቁመው ነው ብሎ ይገልጻል ። ከዚህ የበለጠ ማስረጃ ሊቀርብለት የማይችል መሆኑንም ያስገነዝባል ። ምዕመናን ስለ አላህ መኖር በዚህ ዓለም አፈጣጠር ሊገነዘቡ የሚችሉ ስለመሆናቸው ቁርአን እንዲህ ይላል ።

[3] ጥራትና ልዕልና የርሱ ይሁን እንደ ማለት ነው ።

"አላህ ሰማያትና ምድርን ዕውነተኛ ሆኖ ፈጠረ ፤ በዚህ ውስጥ ለምዕመናን ተአምር አለበት ።" ( ም ፳፱ ቁ ፵፬) ተጥሉም እንዲህ ይላል ።

إِنَّ فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ لَأٓيَٰتٍ لِّلْمُؤْمِنِينَ الجاثية ٣

"በሰማያትና በምድር ውስጥ ለምዕመናን ሁሉ (ለችሎታቸው) እርግጠኛ ምልክቶች አሉ ።" (ም ፵፭ ቁ ፫)

ስለዓለም ሲነገር ምድርና ሌሎች ፕላኔቶችን ፣ ፀሐይን ፣ ጨረቃን ፣ ሌሎተ ከዋክብትን ያጠቃልላል ። የከዋክብት ጥናት (የሥነ ፈለክ) ምሁራን ብዛታቸው በመቶ ሺህ ሚሊዮን የሚገመት ከዋክብት መኖራቸውን ይገልጻሉ ። ፀሐይ ከምድራችን ፺፫ ሚሊዮን ማይልስ የምትርቅና ይህ ርቀት ጨረቃ ከምድር ካላት ርቀት ፬፻ ጊዜ የሚበልጥ መሆኑን ፣ ከፕላኔቶች ራቅ ያለችውና ፐሉቶ ተብላ ከምትጠራው ፕላኔት ብርሃን በሴኮንድ 186,000 ማይልስ እየተጓዘ ምድራችን ለመድረስ 4.14 ሰዓት የሚፈጅበት መሆኑን ፣ የቀሩት ከዋክብት እስከ 2000 ሚሊዮን የብርሃን ዓመት ከእኛ መራቃቸውን ይገልጻሉ ። በዚህ ርቀት መገኘታቸው የሚያስገርም ብቻ ሳይሆን ዓላማ ያለው መሆኑን ሁኔታው ይጠቁማል ።

እነዚህ በብዙ ቢሊዮን የሚቆጠሩ ከዋክብት በሥርዓት በዓለም ተሠራጭተው መገኘታቸውና በሥርዓት መንቀሳቀሳቸው ፣ አንዱ ከሌላው ሳይጋጭ መጓዙ ለአላህ መኖር ሊታበል የማይችል ከፍተኛ ማስረጃ ነው ።

فَلَآ أُقْسِمُ بِمَوَٰقِعِ ٱلنُّجُومِ ﴿٧٥﴾ وَإِنَّهُۥ لَقَسَمٌ لَّوْ تَعْلَمُونَ عَظِيمٌ
الواقعة ٧٥ - ٧٦

ቁርአን እንዲህ ይላል ፤

"በከዋክብት መጥለቂያዎች እምላለሁ ። እርሱም ከታወቀ ታላቅ መሃላ ነው" (ም ፶፮ ቁ ፸፭-፸፮)

ስለከዋክብት ምንነት ምሥጢራቸው በቅርቡ ከብዙ ጥናትና ምርምር በኋላ የመስኩ ባለሙያዎች በትላልቅ መሣሪያዎች አማካኝነት ከማወቃቸው በፊት የወረደው የቁርዓን አንቀጽ ምንጩ አላህ መሆኑን ለሚያስተውል አእምሮ ሊያረጋግጥ ይችላል ።

ዶክተር ማሪት ስታንሊ ኮንጂድን የአሜሪካው የተፈጥሮ ጥናት ማህበር አባል ሲናገሩ "በዓለም ያለው ነገር ሁሉ የአላህን መኖር ይመሰክራል ፤ ችሎታውንና ታላቅነቱንም ይጠቁማል ፤ እኛ ምሁራን ስለዚህ ዓለም ገጽታዎች ስንመራመርና ስናጠና ስለአላህ መኖርና ታላቅነት ምልክቶቹን ከማስተዋል የተለየ ሥራ አይደለም የምንሠራው"[4] ብለዋል ። ስለዚህ የዓለምን ፍጥረታት በማስተዋልና በውስጡ በምናገኛቸው ዕውነታዎች (ፋክትስ) ቅንና ትክክለኛ በሆነው አእምሮዋችን ሁኔታውን ካጤን የፈጠራቸው ኃይል ያለ መሆኑን እምነን ልንረካ እንችልምን ? በቁርአን የመጣውና ስለዚህ ጉዳይ አግባብ ያለውን አንቀጽ ብንጠቅስ ዕምነታችንን እና አቋማችንን ሊያጠናክርልን ይችላል ።

إِنَّ فِي خَلْقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَٱخْتِلَٰفِ ٱلَّيْلِ وَٱلنَّهَارِ لَأٓيَٰتٍ لِّأُو۟لِى
ٱلْأَلْبَٰبِ ﴿١٩٠﴾ ٱلَّذِينَ يَذْكُرُونَ ٱللَّهَ قِيَٰمًا وَقُعُودًا وَعَلَىٰ جُنُوبِهِمْ

[4] ፋህል ዲኒል እስላሚይ ከዓሪፍ አብዱልፈታህ ጠባራህ 17ኛው ዕትም ገጽ 69—70

وَيَتَفَكَّرُونَ فِي خَلْقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ رَبَّنَا مَا خَلَقْتَ هَٰذَا بَٰطِلًا

آل عمران ١٩٠-١٩١

"ሰማያትንና ምድርን በመፍጠር ፣ ሌሊትና ቀንን በመተካት ፣ ለባለ አእምሮዎች በእርግጥ ምልክቶች አሉ ። (እነርሱም) እነዚያ ቆመው ፣ ተቀምጠውም ፣ በጎኖቻቸውም ተጋድመውም አላህን የሚያወሱ ፣ በሰማያትና በምድር አፈጣጠርም የሚያስተነትኑ፣ጌታችን ሆይ ! ይህን በከንቱ አልፈጠርከውም ።" (ም ፫ ቁ ፻፺-፻፺፩)

## 1.2.1. ሌሊትና ቀን ፣ ፀሐይና ጨረቃ አላህ ስለመኖሩ ማስረጃዎች ናቸው ፤

ከቁርአን አንቀጽ ብንጀምር እንዲህ ይላል ፤

وَمِنْ ءَايَٰتِهِ ٱلَّيْلُ وَٱلنَّهَارُ وَٱلشَّمْسُ وَٱلْقَمَرُ لَا تَسْجُدُوا۟ لِلشَّمْسِ
وَلَا لِلْقَمَرِ وَٱسْجُدُوا۟ لِلَّهِ ٱلَّذِى خَلَقَهُنَّ إِن كُنتُمْ إِيَّاهُ تَعْبُدُونَ

فصلت ٣٧

"ሌሊትና ቀንም ፣ ፀሐይና ጨረቃም ከምልክቶቹ ናቸው ፤ ለፀሐይና ለጨረቃ አትስገዱ ፣ ለዚያም ለፈጠራቸው አላህ ስገዱ ፤ እርሱን ብቻ የምትገዙ እንደ ሆናችሁ (ለሌላ አትስገዱ)" ። (ም ፵፩ ቁ ፴፯)

የሌሊትና ቀን መፈራረቅ መሬት በራስዋ እንዝርት (ዛቢያ) ላይ የመሽከርከሩዋ ውጤት ነው ። ይህም የመሬት መሽከርከር ግልጽ የሆነ ለአላህ መኖር ማስረጃ ነው ። የመሽከርከሩ ፍጹም ሚዛናዊነትና አንዲት ሰኮንድ ለውጥ እንኳን የማይታይበት መሆኑ የተመልካችን የማስተዋል ስሜት የሚቀሰቅስ ነው ። የተወሰኑ ግራሞች የሚመዘነው የእጅ ሰዓት ትክክለኛ ጊዜን የሚነግረን መሆኑን ከማረጋገጣችንም በላይ በከፍተኛ ጥበብ የሠራው ባለቤት ያለው መሆኑን አንጠራጠርም ፤ እንመሰክራለን ፤ ዳሩ ግን በየዕለቱ የተወሰኑ ሰኮንዶች ሲሳሳት እናያለን ። የመሬትን ያክል ግዙፍ አካል ያለ ምንም ስህተት የመሽከርከሩን ዙር ለዘመናት ሲያካሂድ መታየቱ ሠሪ ያለው መሆኑን ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን ሠሪው ወደር የለሽ የሆነ የጥበብ ባለቤት መሆኑን እንድንቀበል አያስገድደንምን ? የዚህ የመሬት መሽከርከር በላይዋ ላይ ባለው ሕይወት ላይ ከፍተኛ ሚና አለው ። ይህ መሽከርከር ባይኖር ኖሮ ምን ሁኔታ ይከሰት እንደ ነበር ለአንድ አፍታ እናስተውል ። ባሕሮችና ሐይቆች የያዙት ውኃ ተና ባለቀና ባዶ በሆኑ ነበር ። መሽከርከሩም ካለበት ፍጥነት ቢጨምር ኖሮ መሬት ላይ ያለው ነገር ሁሉ መኖሪያ ቤትና ታላልቅ ሕንፃ ጭምር ፍርክርኩ በወጣ ነበር ። ፍጥነቱ ቢዘገይ ኖሮም በሙቀትና በብርድ ምክንያት መሬት ላይ ያለው ነገር ሁሉ በጠፋ ነበር ።

ስለመሬት መዞር ቁርአን ሲናገር እንዲህ ይላል ፤

وَتَرَى ٱلْجِبَالَ تَحْسَبُهَا جَامِدَةً وَهِىَ تَمُرُّ مَرَّ ٱلسَّحَابِ ۚ صُنْعَ ٱللَّهِ ٱلَّذِىٓ أَتْقَنَ كُلَّ شَىْءٍ ۚ

النمل ٨٨

“ጋራዎችንም እርስዋ እንደ ደመና እስተላለፍ የምታልፍ ስትሆን ፣ የቆሙች ናት ብለህ የምታስባት ሆና ታያጋላህ ፤ የዚያን ነገሩን ሁሉ ያጠነከረውን የአላህን ጥበብ ተመልከት” (ም ፳፯ ቁ ፹፰)

ስለአላህ መኖር ፀሐይ ትልቅ ማስረጃ ናት ሲባል ሕይወት ላላቸው በመሬት ለሚኖሩ ነገሮች ስለ መኖራቸው ዋስትና ሆና የተሰጠች መሆኑ ነው ። ሙቀቷን ፀሐይ ከየት ታመጣዋለች ? በውስጡዋ ከተከማቸ ኃይል ቢሆን ኖር የፀሐይ ሙቀት ዕድሜ ውሱን ይሆን አልነበረምን ? ወደ ኋላ ራቅ ብለው ያለፉትን ዘመናት ብናስተውል ፀሐይ ለመሬት የሰጠችው የሙቀት መጠን አዝርዕትን ፣ እንስሳትንና የሰውን ልጅ ለማኖር ከሚያስችለው መጠን እንሶ አያውቅም ። ከዚህ ሐቅ የምንገነዘበው ለፀሐይ የማያልቅ ሙቀት የሚሰጣትና ፣ የምታስተላልፈው የሙቀት መጠን ከልኩ በልጦ የሚያቃጥልና የሚፋጅ ወይም ቀንሶ ብርዱ የሚያኮማትርና የሚያረጋ ሳይሆን ሚዛኑን ጠብቃ እንድትሰጥ የሚያደርጋት ኃይል መኖሩን ነው ።

ጨረቃ ጊዜን ስለመቁጠርና ሌሊት የምትሰጠውን ብርሃኑም በሕይወት ላሉ ፍጡራን ከሚሰጠው ጥቅም አንጻር ሲታይ የፀሐይና ጨረቃ አፈጣጠር በፕላንና በዓላማ ላይ የተመሠረተ መሆኑን አይጠቁምምን ?

ሰማይና በውስጡዋ የሚገኙት ከዋክብት አንዱ ከሌላው ሳይጋጭ በስበት ኃይል ሥፍራቸውን (መስመራቸውን) ጠብቀው መጓዝና ካለንበት መሬትም ጋር አለመላተም ፣ መሬታችንም ከያዘችው አዝርዕት ፣ እንስሳት ፣ ተራሮችና ሸለቆዎች ፣ ጅረቶችና ባሕሮች በተወሰነ ሥርዓትና ደንብ ለሰው ልጅ ጠቃሚ በሆነ መልኩ ተደራጅተው መኖርና መጓዝ በዚህ ሥርዓት የፈጠራቸው ሠሪ ባለቤት ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው ።

ምሁሩ ኤ ክሪሲ ሞሪስን “በተፈጥሮ የሚገኙ አስገራሚ ነገሮች ሁሉ የራሳቸው የሆነ ጥቅምና ምክንያት ያላቸው ለመሆኑ ራሳቸው ምስክሮች ናቸው ። በመሬትና በፀሐይ መሀል ያለውን ርቀት ያስተዋለና መሬት ከፀሐይ የምታገኘው ሙቀት ለሕይወት የወሳኝነት ሚና ያለው ከመሆኑ ጋር ያገናዘበ ፣ የአፈርን ይዘት ፣ የውኃን ፣ የካርቦን ዳይኦክሳይድን መጠን ፣ የናይትሮጂንን ሚና ፣ የሰው ልጅ መገኘትና በምድር ገጽ በሕያውነት የመቆየቱን ጉዳይ የጤነ ሁሉ ፣ ከሥርዓት የለሽ ሁኔታ ሥርዓትና ደንብ መፈጠሩንና (እነዚህ ሁሉ) ለምክንያትና ለዓላማ የተገኙ መሆናቸውን በትክክል ይረዳል”[5] ሲል ተናግሮዋል ። ይህንኑ የምክንያትና የዓላማ መኖር እንድናስተውለው በአያሌ አንቀጾች ቁርአን ይጋብዘናል ፤ በከፊሉ ከጠቀስን ፤

إِنَّ فِي خَلۡقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَٱخۡتِلَٰفِ ٱلَّيۡلِ وَٱلنَّهَارِ وَٱلۡفُلۡكِ ٱلَّتِي تَجۡرِي
فِي ٱلۡبَحۡرِ بِمَا يَنفَعُ ٱلنَّاسَ وَمَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مِن مَّآءٍ فَأَحۡيَا بِهِ ٱلۡأَرۡضَ بَعۡدَ
مَوۡتِهَا وَبَثَّ فِيهَا مِن كُلِّ دَآبَّةٍ وَتَصۡرِيفِ ٱلرِّيَٰحِ وَٱلسَّحَابِ ٱلۡمُسَخَّرِ بَيۡنَ
ٱلسَّمَآءِ وَٱلۡأَرۡضِ لَأٓيَٰتٍ لِّقَوۡمٍ يَعۡقِلُونَ البقرة ١٦٤

[5] ሩሀል ዲነል እስላሚይ ገጽ 70—72

"ሰማያትንና ምድርን በመፍጠር ፣ ሌሊትና ቀንንም በማተካካት ፣ በዚያችም ሰዎችን በሚጠቅም ነገር (ተጭና) በባሕር ላይ በምትንሻለለው (የምትንሳፈፈው)[6] ታንኳ ፡ አላህም ከሰማይ ባወረደው ውኃና በርሱም ምድርን ከሞተች በኋላ ሕያው በማድረጉ ፡ በርስዋም ውስጥ ከተንቀሳቃሽ ሁሉ በመበተኑ ፣ ነፍሶችንም (በየአቅጣጫው) በማገለባበጥ ፣ በሰማይና በምድር መካከል በምንነዳውም ደመና ለሚያውቁ ሕዝቦች እርግጠኛ ምልክቶች አሉ ።" ም ፪ ቁ ፩፻፷፬

وَهُوَ ٱلَّذِي مَدَّ ٱلْأَرْضَ وَجَعَلَ فِيهَا رَوَٰسِيَ وَأَنْهَٰرًا ۖ وَمِن كُلِّ ٱلثَّمَرَٰتِ جَعَلَ فِيهَا
زَوْجَيْنِ ٱثْنَيْنِ ۖ يُغْشِي ٱلَّيْلَ ٱلنَّهَارَ ۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ

الرعد ٣

"እርሱም ያ ምድርን የዘረጋ ፣ በርስዋም ተራራዎችንና ወንዞችን ያደረገ ፣ በውስጥዋም ከፍሬዎች ሁሉ ሁለት ሁለት ዓይነቶችን ያደረገ ነው ፤ ሌሊትን በቀን ይሸፍናል ፤ በዚህም ውስጥ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች ምልክቶች አሉ ።"
( ም ፲፫ ቁ ፫)

وَمِنْ ءَايَٰتِهِۦ يُرِيكُمُ ٱلْبَرْقَ خَوْفًا وَطَمَعًا وَيُنَزِّلُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءً فَيُحْيِۦ
بِهِ ٱلْأَرْضَ بَعْدَ مَوْتِهَآ ۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يَعْقِلُونَ

الروم ٢٤

"ብልጭታዋም (መብረቅን) ፈሪዎችና ከጃዮች ስትሆኑ ለናንተ ማሳየቱ ፣ ከሰማይም ውኃን ማውረዱ በርሱም ምድርን ከሞተች በኋላ ሕያው ማድረጉ ፣ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው ፤ በዚህም ውስጥ ለሚያስቡ ሕዝቦች ታዕምራቶች አሉበት ።" (ም ፴ ቁ ፳፬)

ከነዚህ የቁርአን አንቀጾች የምንገመግመው ከብዋ መሬት በእንዝርትዋ (በዛቢያዋ) ላይ በመዞሩዋ ምክንያት ሌሊትና ቀን መፈጠራቸውን የመሬት መዞር የሚፈጥረው አየር ውኃን በትነት መልኩ ከየባሕሩ ተሸከሞ ወደ ሩቅ ሥፍራዎች ካጓጓዘ በኋላ በዝናብ መልክ ወርዶ ለመሬት አዲስ ሕይወት በመስጠት የተለያየ ጣዕም ያላቸው አዝርዕትና ፍራፍሬዎች መገኘታቸውና የሰው ልጅና የእንስሳት መርኪያ መሆናቸውን ነው ።

ቁርአን የዚህችን ሕይወት ምስጢር እንድናስተውል በገሃድ እየጋበዘ ባለቤት ያላት ለመሆኑ በአእምሮዋችን ተመራምረን እንድንደርስባት ያነቃቃናል ።

## 1.2.2. የአዝርዕት አፈጣጠር ለአላህ መኖር ማስረጃ ነው ፤

መሬት የምታበቅለው አዝርዕትና ፍራፍሬ የአላህን መኖር ለማረጋገጥ በቂ ማስረጃ ስለመሆኑ ቁርአን እንዲህ ይላል ፤

[6] ቃሉን ለማብራራት የተጨመረ ነው ።

وَهُوَ ٱلَّذِيٓ أَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءً فَأَخْرَجْنَا بِهِۦ نَبَاتَ كُلِّ شَيْءٍ فَأَخْرَجْنَا مِنْهُ
خَضِرًا نُّخْرِجُ مِنْهُ حَبًّا مُّتَرَاكِبًا وَمِنَ ٱلنَّخْلِ مِن طَلْعِهَا قِنْوَانٌ دَانِيَةٌ
وَجَنَّٰتٍ مِّنْ أَعْنَابٍ وَٱلزَّيْتُونَ وَٱلرُّمَّانَ مُشْتَبِهًا وَغَيْرَ مُتَشَٰبِهٍ ۗ ٱنظُرُوٓا۟ إِلَىٰ
ثَمَرِهِۦٓ إِذَآ أَثْمَرَ وَيَنْعِهِۦٓ ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكُمْ لَءَايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يُؤْمِنُونَ    الأنعام ٩٩

"እርሱም ያ ከሰማይ ውኃን ያወረደ ነው ፤ በርሱም የነገሩን ሁሉ በቃይ አወጣን ፣ የተደራረበንም ቅንጣት ከርሱ የምናወጣ የሆነን ለምለም (አዝመራ) አረንጓዴ ነገር[7] ከርሱ አወጣን ፣ ከዘንባባም ከእንቡጡዋ የተቀራረቡ የሆኑ ዘለላዎች አሉ ፤ ከወይናችም ፣ ከወይራም ፣ ከሩማንም ፣ (ቅጠላቸው) ተመሳሳይና (ፍሬያቸው) የማይመሳሰል ሲሆኑ አትክልቶችን (አወጣን) ፤ ባፈራ ጊዜ ወደ ፍሬውና ወደ መብሰሉ ተመልከቱ ፤ ባይናችው ለሚያምኑ ሕዝቦች ምልክቶች አሉ ።" (ም ፮ ቁ ፺፱)

ከላይ ከተመለከተው ውስጥ አላህ ፍሬን ከአትክልት አረንጓዴ ክፍል የሚያወጣ መሆኑን መናገሩን ማስተዋል ተገቢ ነው ። ይህ አባባል ከብዙ የሳይንስ ምርምር በኋላ የሰው ልጅ የደረሰበት ሳይንሳዊ ሐቅ መሆኑ በቁርአን የተሰጠን ጥቆማ የአዝርዕት አበቃቀልና ለፍሬ መብቃት ጥበብ በተሞላው መልክ የፈጠራቸው ሠሪ ባለቤት ያላቸው መሆኑን አይጠቁምምን ?

ቁርአን እንደ አፈሩና ውኃው ውህደት የአትክልት ጣዕም የሚለያይ መሆኑን ሲናገር እንዲህ ይላል ፤

وَفِى ٱلْأَرْضِ قِطَعٌ مُّتَجَٰوِرَٰتٌ وَجَنَّٰتٌ مِّنْ أَعْنَٰبٍ وَزَرْعٌ وَنَخِيلٌ صِنْوَانٌ
وَغَيْرُ صِنْوَانٍ يُسْقَىٰ بِمَآءٍ وَٰحِدٍ وَنُفَضِّلُ بَعْضَهَا عَلَىٰ بَعْضٍ فِى ٱلْأُكُلِ ۚ
إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يَعْقِلُونَ    الرعد ٤

"በምድርም ለተጎራበቱ ቁርጥራጮች ፣ አዝርዕቶችም መንታዎችና መንታዎች ያልሆኑ ዘንባባዎች አሉ ፤ በአንድ ውኃ ይጠጣሉ ፤ (በጣዕም ይለያያሉ) ከፊሉዋንም በከፊሉ ላይ በሚበላው ሰብል እናበልጣለን ፤ በዚህም ውስጥ ለሚያውቁ ሕዝቦች ታምራት አለበት" (ም ፲፫ ቁ ፬)
መሬት የምታመርተው አዝመራ የመልኩን መለያየት እንድናጤን ቁርዓን ሲጋብዘን እንዲህ ይላል ።

أَلَمْ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ أَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءً فَسَلَكَهُۥ يَنَٰبِيعَ فِى ٱلْأَرْضِ ثُمَّ
يُخْرِجُ بِهِۦ زَرْعًا مُّخْتَلِفًا أَلْوَٰنُهُۥ    الزمر ٢١

"አላህ ከሰማይ ውኃን እንዳወረደና በምድርም ውስጥ ምንጮች አድርጎ እንዳስገባው አላየህምን? ከዚያም በርሱ ዓይነቶቹ የተለያየን አዝመራ ያወጣል ፤"
(ም ፴፱ ቁ ፳፩)

---

[7] ቃሉን ለማብራራት የተጨመረ ነው ።

ቁርአን ከአዝመራ አካል (የተባዕታይና አነስታይ) ጾታ መኖሩን መጥቀሱና ይህም ዕውነት መሆኑ በሳይንስ መረጋገጡ ከስተት የአላህን መኖር የሚያስረዳ ነው ። ከፊሉ አዝርዕት ራሱን በራሱ ያረባል ፤ ከፊሉ አርቢው በንፋስና በጥቃቅን ነፍሳት አማካኝነት ከሌላው አዝርዕት ይመጣለታል ። የቁርዓኑ አንቀጽ እንዲህ ይላል ።

أَوَلَمْ يَرَوْا إِلَى ٱلْأَرْضِ كَمْ أَنۢبَتْنَا فِيهَا مِن كُلِّ زَوْجٍ كَرِيمٍ ﴿٧﴾ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَةً ۖ وَمَا كَانَ أَكْثَرُهُم مُّؤْمِنِينَ

الشعراء ٧-٨

"ወደ ምድርም በውስጡዋ ከመልካም (በቃይ) ጎሣ ሁሉ ብዙን እንዳበቀልን አላዩምን? በዚህ አስደናቂ ምልክት አለበት ፤ አብዛኞቻቸውም አማኞች አል ነበሩም ።" (ም ፳፮ ቁ ፯-፰)

የአዝርዕትን አበቃቀል ስናስተውልና ስናጤን ስንዴ ከስንዴ በቀር ገብስ አለማብቀሉ በመሃከላቸው ያለውን የይዘት ልዩነት የሚጠቁም ሲሆን የአበቃቀላቸው ፤ የአመጋገባቸውና የአስተዳደጋቸው መመሳሰል አድናቆት ላይ እንድንወድቅ ያስገድደናል ። የመጀመሪያዋ ዘር ከየት ተገኘች ብለን እንድን ጠይቅም ይገፋፋናል ። በትክክለኛው አስተሳሰብና አእምሮ ዘሩ ራሱን በራሱ ፈጠረ ፤ ወይም በአጋጣሚ ተገኘ የሚለውን አባባል ለመቀበል ፍጹም ያስቸግራል ። የግድ ባለቤትና ፈጣሪ ያለው መሆኑንም ይጠቁማል ።

## 1.2.3. የሰው አፈጣጠርም ለአላህ መኖር ማስረጃ ነው ፤

የሰው ልጅ ዕውቀት በሰፋና ጥበቡም በዳበረ ቁጥር የራሱን አፈጣጠር ፣ የራሱን አካልና ቁመና ቢያስተውል ከደረሰበት የዕውቀት ደረጃ አንፃር እያንዳንዱን የሰውነቱ ክፍል ቢያጤን በጣም የሚያስገርመው ብቻ ሳይሆን ራሱን የቻለ ምክንያትና ዓላማ ያለው መሆኑን ይገነዘባል ። የተለያዩ ተግባራትን በሥርዓትና በቅንጅት የሚያከናውኑት የሰውነት ክፍሎቹ ተጠቃለው ለሰው ልጅ ፍላጎት የተሟላ አገልግሎት እየሰጡ መገኘታቸው የአጋጣሚ ጉዳይ ሳይሆን በታላቅ ጥበብ ለታላቅ ዓላማ ተደራጅተው መሠራታቸውን በቀላሉ ለመገንዘብ ይቻላል ። ምክንያቱም ጫማን የሚያክል ቀላል የሥራ ውጤት "እንዲሁ በአጋጣሚ ተገኘ" የሚለውን አባባል ፈጽሞ የማይቀበለው አእምሮዋችን የሰው ልጅን የመሰለ በጣም የተወሳሰበ ፍጡር "እንዲሁ በአጋጣሚ ተገኘ" የሚለውን አባባል ስለማይቀበል ነው ። የሰው ልጅ በፍትወት ጠብታ መራባቱ ፣ በእናቱ ማኅፀን የሚቆይባቸው ሁኔታዎች ፣ የሚያደርጋቸው የእድገት ለውጦች ፣ አመጋገቡ ፣ ከተወለደ በኋላም ያለው የአመጋገብ ሥርዓት ፣ ለሰውነት ገንቢ የሆኑትን ወደ ሰውነቱ በመርጨት ጠቃሚ ያልሆኑትን ከሰውነቱ እንዲወጣ ማድረጉን ብቻ እንኳን ብንወስድ የዚህ አስደናቂ ክንውን ባለቤት የሆነ ሠሪ ያለው መሆኑን አያመለክትምን ?

የደም ከልብ ወደ መላው ሰውነታችን ቁጥር ሥፍር በሌላቸው ሥሮች አማካኝነት መጓዝ ፣ በምንተነፍሰው ንፁሕ አየር አማካኝነት የተበከለው ደም መጥራትና ሰውነታችንን ማገልገል እያንዳንዱ ክፍል ለምክንያት የተፈጠረ ፣ የተወሰነ ዓላማን የሚያገለግል ሆኖ መገኘት በዚህ ረቂቅ መልኩ እንዲደራጅ ያደረገ ኃይል አይኖርምን ? የሰውን የመስማት ኃይል ፣ የማየት ኃይል ፣ የመ

"ለናንተም ከነፍሶቻችሁ (ከጎሶቻችሁ) ሚስቶችን ወደነሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ ፣ በመካከላችሁም ፣ ፍቅርና እዝነትን ማድረጉ አስደናቂ ምልክቶቹ ነው ፤ በዚህ ውስጥ ለሚያስተውሉ ሕዝቦች ታምራቶች አሉ ።" (ም ፴ ቁ ፳፩)

وَٱللَّهُ جَعَلَ لَكُم مِّنْ أَنفُسِكُمْ أَزْوَٰجًا وَجَعَلَ لَكُم مِّنْ أَزْوَٰجِكُم بَنِينَ وَحَفَدَةً
وَرَزَقَكُم مِّنَ ٱلطَّيِّبَٰتِ ۚ أَفَبِٱلْبَٰطِلِ يُؤْمِنُونَ وَبِنِعْمَتِ ٱللَّهِ هُمْ يَكْفُرُونَ النحل ٧٢

"አላህ ከነፍሶቻችሁ (ከጎሶቻችሁ) ለናንተ ሚስቶችን አደረገ ፤ ለናንተም ከሚስቶቻችሁ ወንዶች ልጆችን ፣ የልጅ ልጆችንም አደረገላችሁ ፤ ከመልካሞችም ፀጋዎች ሰጣችሁ ፣ ታዲያ በውሸት (በጣዖት) ያምናሉን ? በአላህም ፀጋ እነሱ ይክዳሉን ?" (ም ፲፮ ቁጥር ፸፪)

## 1.2.4. የእንስሳት ፣ የጥቃቅን ነፍሳት ፣ የአዕዋፍ አፈጣጠርም ለአላህ መኖር በቂ ማስረጃ ነው ፤

ከሰው ልጅ አፈጣጠር ሌላ የእንስሳት ፣ የጥቃቅን ነፍሳትና የአዕዋፍ አፈጣጠርም ስለ አላህ መኖር በቂ ማስረጃዎች ስለመሆናቸው አላህ በቁርአን እንዲህ ይላል ፤

وَٱللَّهُ خَلَقَ كُلَّ دَآبَّةٍ مِّن مَّآءٍ ۖ فَمِنْهُم مَّن يَمْشِى عَلَىٰ بَطْنِهِۦ وَمِنْهُم مَّن يَمْشِى عَلَىٰ رِجْلَيْنِ وَمِنْهُم
مَّن يَمْشِى عَلَىٰٓ أَرْبَعٍ ۚ يَخْلُقُ ٱللَّهُ مَا يَشَآءُ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ قَدِيرٌ النور ٤٥

"አላህም ተንቀሳቃሽን ሁሉ ከውኃ ፈጠረ ፤ ከነሱም በሆዱ ላይ የሚሄድ አልለ ፤ ከነሱም በሁለት እግሮቹ የሚሄድ አልለ ፤ ከእነሱም በአራት ላይ የሚሄድ አልለ ፤ አላህ የሚሻውን ሁሉ ይፈጥራል ፤ አላህ በነገሩ ላይ ሁሉ ቻይ ነው ።" (ም ፳፬ ቁጥር ፵፭)

أَلَمْ يَرَوْا۟ إِلَى ٱلطَّيْرِ مُسَخَّرَٰتٍ فِى جَوِّ ٱلسَّمَآءِ مَا يُمْسِكُهُنَّ إِلَّا ٱللَّهُ ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ
لَءَايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يُؤْمِنُونَ النحل ٧٩

"ወደ በራሪዎች በሰማይ አየር ውስጥ (ለመብረር) የተገሩ ሲሆኑ (ከመውደቅ) አላህ እንጂ ሌላ የማይዛቸው ሆነው አይመለከቱምን ? በዚህ ውስጥ ለሚያምኑ ሕዝቦች በእርግጥ ታምራቶች አልሉ ።" (ም ፲፮ ቁጥር ፸፱)

ከላይ የተመለከቱት አያሌ ምልክቶች የአላህን መኖር የሚያስረዱ ቢሆንም የሰው ልጅ በተጨባጭ ነገር ላይ በተመሠረተው ዕውቀቱ በሚያያቸው ብቻ የአላህን መኖር በሙሉ ተቀብሉ ላያምን ይችላል ። የተሟላ ዕምነት ላይ የሚደርሰው በዕውቀት ላይ ተመሥርቶ ያገኘውን መረጃ ከነፍስ (መንፈስ) ጋር ከተዛመደው መረጃ ጋር በማዋሃድ ሊያስፋቸው ሲችል ብቻ ነው ። ውስጣዊ ስሜቱ ተቀስቅሶ የአካባቢው ፍጥረታት የሚሰጡትን መረጃ በማስተዋል ከመንፈሱ መሠረታዊ ፍላጎት ጋር ለማጣጣምና ለማዋሃድ ሲችል በአላህ መኖርና የፈጣሪነት ሚናው ሙሉ በሙሉ ለማመን ይችላል ።

## 1.2.5. የሕይወት አፈጣጠር ራሱ ለዓለም አንድ ባለቤት ፣ አንድ ጌታ ፣ አላህ መኖሩን በሚያስረዳ መልክ የተከናወነ ከመሆኑም በላይ የአላህን መኖር ማመን ከሕይወት ጋር ተዋህዶ የተፈጠረ ነው ። የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ በየዘመናቱ ሕይወቱ ከአምልኮት ጋር የተቆራኘ እንደ ነበረ ከታሪክ ለመረዳት ይቻላል ። አላህ የሰው ልጅ ሕይወት አንድን ፈጣሪ ከማመን ጋር የተቆራኘች መሆንዋን ሲያስረዳ በቁርዓን እንዲህ ይላል ።

فَأَقِمْ وَجْهَكَ لِلدِّينِ حَنِيفًا فِطْرَتَ ٱللَّهِ ٱلَّتِي فَطَرَ ٱلنَّاسَ عَلَيْهَا لَا تَبْدِيلَ
لِخَلْقِ ٱللَّهِ ذَٰلِكَ ٱلدِّينُ ٱلْقَيِّمُ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَ ٱلنَّاسِ
لَا يَعْلَمُونَ ﴿٣٠﴾ ۞ مُنِيبِينَ إِلَيْهِ وَٱتَّقُوهُ وَأَقِيمُوا۟ ٱلصَّلَوٰةَ وَلَا تَكُونُوا۟
مِنَ ٱلْمُشْرِكِينَ الروم ٣٠-٣١

"ወደ ዕውነት ተዘንባይ ሆነህም ፊትህን ለሃይማኖት ቀጥ አድርግ ፤ የአላህን ፍጥረት ፣ ያችን አላህ ሰዎች በርስዋ ላይ የፈጠረባትን (ሃይማኖት ያዝዋት) የአላህን ፍጥረት መለወጥ የለም ፤ ይህ ቀጥተኛ ሃይማኖት ነው ፤ ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያውቁም ። ወደርሱ ተመላሽ ሆናችሁ (የአላህን ሃይማኖት ያዙ) ፤ ፍሩትም ፤ ሰላትንም አስተካከላችሁ ስገዱ ፤ ከአጋሪዎችም አትሁኑ ።" (ምዕ ፴ ቁጥር ፴-፴፩) የሰው ልጅ አደጋ በደረሰበት ቁጥር ፣ ወይም ጭንቀት ውስጥ በገባ ቁጥር ከዚያ የሚገላግለው አንድ ኃይል መኖሩን ስሜቱ ስለሚነግረው ይማጸናል ። ዳሩ ግን ከጭንቀቱ ከተላቀቀ በኋላ የዚያን ኃይል መኖር ይዘነጋል ፤ ይክዳልም ። ስለዚህ ሁኔታ አላህ ሲያስታውሰን እንዲህ ይላል ።

وَإِذَا مَسَّ ٱلنَّاسَ ضُرٌّ دَعَوْا۟ رَبَّهُم مُّنِيبِينَ إِلَيْهِ الروم ٣٣

"ሰዎችንም ችግር ባገኛቸው ጊዜ ጌታቸውን ወደርሱ ተመላሽ ሆነው ይጠሩታል" (ምዕ ፴ ቁጥር ፴፫)

وَإِذَا غَشِيَهُم مَّوْجٌ كَٱلظُّلَلِ دَعَوُا۟ ٱللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ لقمان ٣٢

"እንደ ጥላዎችም የሆነ ማዕበል በሸፈናቸው ጊዜ አላህን ፣ ሃይማኖትን ለእርሱ ብቻ ያጠሩ ሆነው ይጠሩታል ።" (ምዕ ፴፩ ቁ ፴፪)

## 1.2.6. የዕውቀት መዳበር በአላህ ማመንን የሚጠይቅ ስለመሆኑ ፤

ባለፉት አራት ምዕተ ዓመታት (፬፻ ዓመት) የነበሩትን የታላላቅ ፈላስፎች ታሪክ በማጥናት ጀርመናዊው ዶክተር ዴይነርት ያገኙት ውጤቱ የሚከተለው ነው ።[8]

"ካጠኑዋቸው ፪፻፺ ታላላቅ ፈላስፎች ውስጥም ምንም ዓይነት ዕምነት ለመከተል ያልወሰኑ ቁጥራቸው ፳፰ ነበር

"፪፻፵፪ የሚሆኑት የፈጣሪን መኖር መስክረው ዕምነት የነበራቸው መሆኑን አረጋገጡ ፤

[8] ሩሀል ዲኒል እስላሚይ ገጽ 84

“፰ የሚሆኑት ግን ስለዕምነት ወይም ክህደት ግድ የለሽ የነበሩ መሆኑንም አረጋገጡ ።

አንድን ዕምነት ለመከተል ያልወሰኑትንም ፈጣሪ የለም ከሚሉት ጋር ብንደ ምራቸው እንኳ ከታላላቅ ምሁራን (ፈላስፎች) ውስጥ 92% በፈጣሪ መኖር የሚያምኑ መሆኑን እንገነዘባለን ።

ታላላቁ ምሁራን በምርምራቸው ውጤት ስለፈጣሪ መኖር ካረጋገጡ በኋላ ብዙ የጻፉት ቢኖርም የእንግሊዙ ፈላስፋ ፍራንስ ቤከን የተናገሩት ጎልቶ የሚታይ ነው ። ቁርዓን ስለምሁራን ሲናገር እንዲህ ይላል

إِنَّمَا يَخْشَى ٱللَّهَ مِنْ عِبَادِهِ ٱلْعُلَمَٰٓؤُاْ فاطر ٢٨

“አላህን ከባሮቹ ውስጥ የሚፈሩት ፣ አዋቂዎቹ ብቻ ናቸው ።” (ም ፴፭ ቁጥር ፳፰)

شَهِدَ ٱللَّهُ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ وَٱلْمَلَٰٓئِكَةُ وَأُوْلُواْ ٱلْعِلْمِ قَآئِمَۢا بِٱلْقِسْطِ آل عمران ١٨

“አላህ በማስተካከል የቆመ (አስተናባሪ) ሲሆን ፣ ከርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የሌለ መሆኑን መሰከረ ፤ መላዕክቶችና የዕውቀት ባለቤቶችም (እንደዚሁ መሰከሩ) ፤” (ም ፫ ቁጥር ፲፰)

ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት መግለጫዎችና ማስረጃዎች አንጻር ፣ “ፈጣሪ የለም ፣ ዓለምና በውስጡዋ የሚገኙ ሁሉ ፣ ከሚከተሉት ሥርዓትና ደንብ ጭምር በአ ጋጣሚ ፣ ድንገት የተገኘ ክስተት ነው” ለሚሉት አንባቢ የራሱን መልስ ለመስጠት ይችላል ። አላህ ክብሩ ይስፋና ሙሐመድን ሰልላ አላሁ ዓለይሂ ወሰለም (ሰ. አ. ዓ. ወ)[9] እንዲህ ብሎዋቸዋል ።

إِنَّكَ لَا تَهْدِى مَنْ أَحْبَبْتَ وَلَٰكِنَّ ٱللَّهَ يَهْدِى مَن يَشَآءُ القصص ٥٦

“(ሙሐመድ ሆይ ! ) አንተ የወደድከውን (ሰው) ወደ ቀናው ጎዳና ልትመራው አትችልም ፣ አላህ ነው የፈለገውን (ሰው) ወደ ቀናው ጎዳና የሚመራ ፤” (ም ፳፰ ቁጥር ፶፮)

ከዚህ በላይ የፍጥረታት ሁሉ ባለቤት የሆነ ፈጣሪ አላህ መኖሩን አንባቢ በግልጽ እንዲረዳ ለማድረግ የተሞከረ ሲሆን ቀጥሎ ባለው ምዕራፍ ፈጣሪ ወይም አላህ አንድ ብቻ ስለመሆኑ ለመግለጽ ይሞከራል ።

[9] “የአላህ እዝነትና ሠላም ይድረሳቸውና” እንደ ማለት ነው ።

## 2. ከአንድ አላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም

### 2.1. ትክክለኛ የአእምሮ አስተሳሰብ ከአንድ በላይ ፈጣሪ (አላህ) መኖሩን አይቀበልም ።

ነቢዩ ዩሱፍ (ዓለይሂ ሰላም) ሠላም ለርሳቸው ይሁንና የተናገሩትን ከቁርዓን መጥቀሱ ጠቃሚ ይሆናል ።

ءَأَرْبَابٌ مُّتَفَرِّقُونَ خَيْرٌ أَمِ ٱللَّهُ ٱلْوَٰحِدُ ٱلْقَهَّارُ ﴿٣٩﴾ مَا تَعْبُدُونَ مِن دُونِهِۦٓ
إِلَّآ أَسْمَآءً سَمَّيْتُمُوهَآ أَنتُمْ وَءَابَآؤُكُم مَّآ أَنزَلَ ٱللَّهُ بِهَا مِن
سُلْطَٰنٍ ۚ إِنِ ٱلْحُكْمُ إِلَّا لِلَّهِ ۚ أَمَرَ أَلَّا تَعْبُدُوٓا۟ إِلَّآ إِيَّاهُ يوسف ٣٩-٤٠

"የተለያዩ አማልክቶች ይሻላሉ ? ወይስ አሸናፊው አንዱ አላህ ? ከርሱ ሌላ እናንተና አባቶቻችሁ (አማልክት ብላችሁ) የጠራችኋቸውን ስሞች እንጂ አትገዙም ፤ አላህ በእርስዋ ምንም አስረጂ አላወረደም ! ፍርዱ የአላህ እንጂ የሌላ አይደለም ፡ እርሱን እንጂ ሌላን እንዳትገዙ አዞአል ።" (ም፲፪ ቁ ፴፱-፵)

አንድን አምላክ ብቻ ማምለክ ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ለማስወገድ እንደሚችል ብዙ አያከራክርም ። ዕውነቱን ለማግኘት ይበልጥ የተመራመረ ደግሞ በርካታ አማልክት እያሉ አንዱን ብቻ ማምለክ ችግሩን ሊያቃልለው ስለማይችል ከአማልክቱ ኃያል የሆነውን መርጦ እንደ ኃያልነቱ በቅደም ተከተል ማሰለፍ የሚገባው መሆኑን ይረዳል ። እንደ ኃያልነታቸው በቅደም ተከተል ማሰለፉን ካጠናቀቀ በኋላ ከሁሉም በላይ ኃያል ሆኖ በመጀመሪያው ደረጃ የተሠለፈው አምላክ የቀሩት አማልክት ሥልጣኑን እንዲጋሩት ለምን ይፈቅድላቸዋል ? የሚል ጥያቄ ማንሳቱ አይቀርም ። ኃያሉ አምላክ ደካሞቹን በማጥፋት ብቸኛው የበላይ ባለሥልጣን እንዲሆን መወሰኑና በተግባር ማዋሉ አይቀርም የሚል ስሜትም ያድርበታል ። በስሜቱ ያደረውም ዕውን እንዲሆን መመኘቱ የማይቀር ነው ። ምክንያቱም አንድ ኃያል የሆነ አምላክ እስካለና እያሌ ኃይላቸው እኩል ወይም የተቀራረበ አማልክት ካሉ አንዱ ያቀደውን ሌላው እየተቃወመ ፤ አንዱ የሠራውን ሌላው የማፍረስ ወይም የማጥፋት ርእምጃ ስለሚወስድበት ዘወትር የሥርዓተ አልበኝነትና የሽብር ሂደት ስለሚሰፍን የዓለም አመራር የሚኖረው ገፅታ ስለሚያስፈራራው ነው ። እንኳን ምድርና ሰማይን እንዲሁም በውስጣቸው የሚገኘውን ነገር ሁሉ የሚያንቀሳቅስ ኃይል ይቅርና በምድራችን በጣም አነስተኛ የሆነውን አንድ ሀገር ብቻ እንኳን ለማስተዳደር ባንድ ወቅት ሁለት ወይም በርካታ እኩል የሆነ ሥልጣን ያላቸው መሪዎች ሊኖሩት እንደማይችሉ አዕምሮዋችን ይነግረናል ። አላህ ራሱ ለተነሱት ጥያቄዎች የሰጠውን መልስ ከቁርአን መጥቀሱ ይጠቅማል ፤

أَمِ ٱتَّخَذُوٓا۟ ءَالِهَةً مِّنَ ٱلْأَرْضِ هُمْ يُنشِرُونَ ﴿٢١﴾ لَوْ كَانَ فِيهِمَآ ءَالِهَةٌ إِلَّا ٱللَّهُ
لَفَسَدَتَا ۚ ﴿٢٢﴾ الأنبياء ٢١-٢٢

“ይልቁንም ከምድር የሆኑን ፣ እነሱ ሙታንን የሚያስነሱን አማልክት ያዙን ? (የለም) ። በሁለቱ (በሰማያትና በምድር) ውስጥ ከአላህ ሌላ አማልክት በነበሩ ኖሮ ፣ በተበላሹ ነበር ፤ (ም ፳፩ ቁጥር ፳፩-፳፪)

مَا ٱتَّخَذَ ٱللَّهُ مِن وَلَدٍ وَمَا كَانَ مَعَهُۥ مِنْ إِلَٰهٍ ۚ إِذًا لَّذَهَبَ كُلُّ إِلَٰهٍۭ بِمَا خَلَقَ
وَلَعَلَا بَعْضُهُمْ عَلَىٰ بَعْضٍ ۚ سُبْحَٰنَ ٱللَّهِ عَمَّا يَصِفُونَ المؤمنون ٩١

“አላህ ምንም ልጅን አልያዘም ፤ (አልወለደም) ፤ ከእርሱም ጋር አንድም አምላክ የለም ፤ ያን ጊዜ (ሌላ አምላክ በነበረ) ፤ አምላክ ሁሉ ፣ በፈጠረው ነገር በተለየ ነበር ከፊላቸው በከፊሉ ላይ በላቀ ነበር ፤ አላህ ከሚመጥኑት ሁሉ ጠራ ።” (ም ፳፫ ቁጥር ፺፩)

## 2.2. <u>የዓለም (ዩኒቨርስ) አንድ ወጥ ሥርዓት የፈጣሪን አንድነት ያስረዳል ፤</u>

የአላህ አንድ ብቻ መሆን ከሚያስረዱ መረጃዎች ውስጥ በጣም አስገራሚ የሆነውን አንዱን በመለየት ቁርአን የሚያቀርበው የዓለም (ዩኒቨርስ) አንድ ወጥ ሥርዓት ነው ። ይህ ሥርዓት አንድ ፈጣሪ ብቻ ያለው መሆኑንበትክክል ይጠቁማል ። ይህን የሚያስረዳው የቁርአን አንቀጽ እንዲህ ይላል ።

قُل لَّوْ كَانَ مَعَهُۥٓ ءَالِهَةٌ كَمَا يَقُولُونَ إِذًا لَّٱبْتَغَوْا۟ إِلَىٰ ذِى ٱلْعَرْشِ سَبِيلًا ﴿٤٢﴾ سُبْحَٰنَهُۥ
وَتَعَٰلَىٰ عَمَّا يَقُولُونَ عُلُوًّا كَبِيرًا ﴿٤٣﴾ تُسَبِّحُ لَهُ ٱلسَّمَٰوَٰتُ ٱلسَّبْعُ وَٱلْأَرْضُ وَمَن فِيهِنَّ ۚ وَإِن
مِّن شَىْءٍ إِلَّا يُسَبِّحُ بِحَمْدِهِۦ وَلَٰكِن لَّا تَفْقَهُونَ تَسْبِيحَهُمْ ۗ إِنَّهُۥ كَانَ حَلِيمًا غَفُورًا

الإسراء ٤٢-٤٤

“(ሙሐመድ ሆይ !) በላቸው እንደምትሉት ከርሱ ጋር አማልክት በነበሩ ኖር ያን ጊዜ ወደ ዐርሹ ባለቤት መንገድን በፈለጉ ነበር ። ጥራት ይገባው ፤ ከሚሉትም ነገር ሁሉ ከፍ ያለን ልቅና ላቀ ። ሰባቱ ሰማያትና ምድርም በውስጣቸውም ያለው ሁሉ ለርሱ ያጠራል ፤ ከነገርም ሁሉ ከማመስገን ጋር የሚያጠራው እንጂ አንድም የለም ፤ ግን ማጥራታቸውን አታውቁትም ፤ እርሱ ታጋሽ መሐሪ ነው ።” (ም ፲፯ ቁጥር ፵፪-፵፬)

ከዚህ ለመረዳት የሚቻለው በዓለም ላይ ከአንዱ አላህ በቀር ሌሎች አማልክት ቢኖር ኖሮ ወደ ዋናው የዓርሽ ባላቤት ወደ ሆነው አላህ መንገዱን ፈልገው በመሄድ እርሱን ይጋገቱት እንደነበረና በአንድ ወጥ ሥርዓት በመመራት ላይ ባለው ዓለም (ዩኒቨርስ) ላይ እያንዳንዱ አምላክ ባለቤትነት ባለው አካል ላይ ገናናነቱን ለማረጋገጥና ወሳኝነት ያለው መሆኑንም ለማሳየት የበኩሉን እርምጃ በመውሰድ ሥርዓት ባሳጣው ነበር ። ሂደቱም የማያስተማምን ፣ ተለዋዋጭ ፣ አንዱ ከሌላው የማይጣጣም ፣ የሚቃረንና የሚጋጭ ስለሚሆን የዘወትር ብጥብጥ በነገሠ ነበር ። የዚህ ሁኔታ አለመከሰትና የዓለም በሥርዓት

መመራት የዓለም ባለቤት የሆነ አንድ አላህ ብቻ መኖሩን የሚያረጋግጥና ታላቅነቱንና ኃያልነቱንም የሚያስረዳ ነው ።

የአላህን አንድነትና ገናናነት ለተገነዘበ አንባቢ ለአላህ አጋር ማድረግ ፣ ወይም ልጅ ፣ መሰየም የማይቻል መሆኑን ማስገንዘብ ጠቃሚ ስለሚሆን ከዚህ በታች ይቀርባል ።

## 2.3. ለአላህ አጋር (ሽሪክ) ማድረግ ከፍተኛ በደል ስለመሆኑ ፤

ለአላህ አጋር ማድረግ የሚለው አባባል ለአምልኮትና ለፀሎት ከአላህ ጋር የተለያዩ ነገሮችን ፣ ምስልን ፣ ጣዖትን ፣ ዛፍን ፣ እንስሳን ፣ ፀሐይን ፣ ጨረቃን ፣ ሰውን ፣ ወዘተ ይጠቅማሉ ፣ ወደርሱ ያቀርባሉ ፣ በእነርሱ አማካኝነት የሚቀርብ ፀሎት ብቻ ነው ተቀባይነት ያለው ወዘተ - - ብሎ ማቅረብና ለአላህ ልጅ አለው ፤ የሚለውን ያጠቃልላል ።

አላህ ለእርሱ አጋር ማድረግ ይቅርታ የማይደረግለት በደል መሆኑን ሲናገር በቁርአን እንዲህ ይላል ፤

إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَغْفِرُ أَن يُشْرَكَ بِهِۦ وَيَغْفِرُ مَا دُونَ ذَٰلِكَ لِمَن يَشَآءُ ۚ وَمَن
يُشْرِكْ بِٱللَّهِ فَقَدْ ضَلَّ ضَلَٰلًۢا بَعِيدًا
النساء ١١٦

"አላህ በእርሱ ማጋራትን አይምርም ፤ ከዚህም ወዲያ ያለውን ለሚሻው ሰው ይምራል ። በአላህም የሚያጋራ ሰው ፣ (ከውነት) የራቀን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ ።" (ም ፬ ቁጥር ፩፻፲፮)

ቀጥሎም አላህ የዓለም ባለቤትና ጌታ እርሱ ብቻ ስለመሆኑ ፣ ልጅም ሆነ ለሥልጣኑ አጋር የሆነ ምንም ነገር የሌለው ስለመሆኑ ፣ በርሱ ምርጫና ልዩ በሆነ ሥርዓት እያንዳንዱን ነገር የፈጠረ ስለመሆኑ ፣ በማረጋገጥ ሙሽሪኮች[1] ምንም የማይጠቅማቸውንና ሊጎዳቸውም የማይችለውን ነገር ለአላህ አጋር እንዳያደርጉ በቁርአን ሲያስተምር እንዲህ ይላል ፤

ٱلَّذِى لَهُۥ مُلْكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَلَمْ يَتَّخِذْ وَلَدًا وَلَمْ يَكُن لَّهُۥ شَرِيكٌ فِى
ٱلْمُلْكِ وَخَلَقَ كُلَّ شَىْءٍ فَقَدَّرَهُۥ تَقْدِيرًا ﴿٢﴾ وَٱتَّخَذُوا۟ مِن دُونِهِۦٓ ءَالِهَةً
لَّا يَخْلُقُونَ شَيْـًٔا وَهُمْ يُخْلَقُونَ وَلَا يَمْلِكُونَ لِأَنفُسِهِمْ ضَرًّا وَلَا نَفْعًا
وَلَا يَمْلِكُونَ مَوْتًا وَلَا حَيَوٰةً وَلَا نُشُورًا
الفرقان ٢-٣

"(እርሱ) ያ የሰማያትና የምድር ንግሥና የርሱ ብቻ የሆነ ፤ ልጅም ያልያዘ ፤ በንግሥናውም ተጋሪ የሌለው ፣ ነገሩንም ሁሉ የፈጠረና ፣ በትክክልም ያዘጋጀው ነው ። (ከሐዲዎች) ከርሱ ሌላ ምንንም የማይፈጥሩን ፣ እነሱም የሚፈ

[1] ለአላህ አጋሪ በማድረግ የሚያመልኩ ማለት ነው ።

ጠሩን ፣ ለነፍሶቻቸውም ጉዳትን ለመከላከል ፣ ጥቅምንም ለማምጣት የማይችሉን ፣ ሞትንና ሕይወትንም ፣ መቀስቀስንም የማይችሉት አማልክት ያዙ!።”
(ም ፳፭ ቁጥር ፪-፫)

በዚህ ምዕራፍ የቀረበውን ለማጠቃለል ብንሞክር ዓለም ያለ ባለቤት በድንገት ወይም በአጋጣሚ ከብዙ ጊዜ በኋላ የተገኘች ሳትሆን ፣ ፈጣሪ ባለቤት ያላትና በከፍተኛ ጥበብ ተቀነባብራና ተቀናጅታ ለተወሰነ ዓላማ የፈጠራትና አንድ ወጥ በሆነ ሥርዓት እንድትመራ ያደረጋት አላህ ያልለ መሆኑን እንገነዘባለን ። ዓለም የምትመራበት አንድ ወጥ የሆነ ሥርዓት የአንድ ባለቤት ፡ የአንድ ጌታ ሥራ እንጂ ለተለያዩ ባለቤቶች ወይም ጌቶች የሚገዛ ዓይነት ሥርዓት ባለመሆኑ ከአንድ አላህ በቀር ሌላ አምላክ የሌለና ሊኖር የማይችል መሆኑን ያስገነዝበናል ።

ዓለም ለተወሰነ ዓላማ መፈጠሯን መገንዘብ ከፍጡሮች ሁሉ የበላይና በዓለም በሚገኙት ነገሮች ሁሉ ተጠቃሚ የሆነው የሰው ልጅ ለምን ዓላማ እንደተፈጠረ ? ከእርሱ ምን እንደሚጠበቅ ? ከእርሱ የሚጠበቀውን ነገር እንዴት እንዲያውቅ እንደተደረገ መመልከቱ አስፈላጊ በመሆኑ በሚከተሉት ምዕራፎች ለማቅረብ እንሞክራለን ።

## 3.1. አላህ ለሰው ልጅ መመሪያ ሲሰጥ ስለመቆየቱ ፡

የመጀመሪያው ሰው የሆኑት አዳም ብቸኛ እንዳይሆኑ አ.ጋር እንድትሆናቸው ሐዋን ተፈ.ጠረ.ች ። ሁለቱም በምድረ ገነት በሰሬው ያሻቸውን ሁሉ እንዲ በሉ ሲፈ.ቀድላቸው የአንዲትን ዛፍ ፍሬ ብቻ ተከለከሉ ። በገነት በፍስሐና በደስታ እየኖሩ ሳለ የተከለከሉትን የዛፍ ፍሬ እንዲበሉ ሰይጣን ስላሳሳ.ታቸው ለተሰጣቸው መመሪያ ተገዥ ባለመሆናቸው ፡ ለፈጸሙት በደል ከገነት ወደ ምድር ተልከው ከመጡበት ጊዜ ጀ.ምሮ ሕይወታቸውን የሚመሩበት ደ.ንብና ሥርዓት ከአላህ የተሰጣቸው ለመሆኑ ከሃይማኖት (ዲን) መጻሕፍት ለመረዳት ይቻላል ።

ከአዳም በኋላም ብዛት ያላቸው መልዕክ.ተኞች የመጡ መሆኑ ሲታወቅ ፣ ከነ ር.ሱ መካከል ያወቅናቸው የአላህ መልዕክተኞች በመካከለኛው ምሥራቅና በአ ካባቢው መልዕክ.ቱን ያደ.ረሱትን ነው ። ዳሩ ግን መልዕክተኛ ያልተላከለት ሕዝብ ወይም የዓለም ክፍል እንደሌለ በቁር.አን ተብራርቶዋል ። አላህ እንዲህ ይላል ፤

وَإِن مِّنْ أُمَّةٍ إِلَّا خَلَا فِيهَا نَذِيرٌ   فاطر ٢٤

“ማንኛይቱም ሕዝብ በውስጡዋ አስፈራሪ (አስጠን.ቃቂ)[1] ያላለፈባት የለ ችም ።” (ም ፴፭ ቁጥር ፳፬)

ከአዳም ጀ.ምር ቁጥራቸው አንድ መቶ ሃያ ሺህ የሚሆኑ ነቢዮች የመጡ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ አንድ መቶ አሥራ ሶስት የሚሆኑ የአላህ መልዕክተኞች የነ በሩ መሆኑም ታውቆዋል ። ከነዚህ ነቢያትና የአላህ መልዕክተኞች መሐል የጥቂቶችን ታሪክ ብቻ ቁርአን የዘረዘረ ሲሆን የሌሎችን ሳይጠቅስ የተዋቸው መሆኑን ሲናገር (ሲገልጽ) እንዲህ ይላል ፤

وَرُسُلًا قَدْ قَصَصْنَاهُمْ عَلَيْكَ مِن قَبْلُ وَرُسُلًا لَّمْ نَقْصُصْهُمْ عَلَيْكَ

النساء ١٦٤

“ከዚህም በፊት በአንተ ላይ በእርግጥ የተረከናቸውን መልዕክተኞች ፣ ባንተ ላይም ያልተረከናቸውን መልዕክተኞች ፣ (እንደላክን ፣ ላክንህ) ።” (ም ፬ ቁጥር ፩፻፷፬)

እንግዲህ የነዚህ ሁሉ ነቢያትና መልዕክተኞች መምጣት የሰው ልጅ በዚህች ዓለም በሕይወት እስካለ ድረስ በምን መመሪያ እንደሚኖርበት ፣ ከእርሱ ምን እንደሚጠበቅ ፣ በምን እንደ.ታዘዘ ፣ ከምን እንደተከለከለ ፣ ለማሳወቅ መሆኑ ግልጽ ነው ። ነቢያት በመሠረቱ ቀናውን መንገድ አውቀው ለራሳቸው እንዲመ ሩበት ራዕይ (ወህይ) የወረደ.ላቸው ሲሆን ተግባራቸው መልካም ምሳሌነት ኖሮት የሚከተሏቸው ሰዎች በራሳቸው ፈ.ቃድ ሊከተሉዋቸው ከሚችሉ በተር እንደ (ረሱሉች) መልዕክተኞች በያለበት እየዞሩ ሕዝቡን በመቀስቀስ አያስ ተምሩም ። የአላህ መልዕክተኞች ግን መልዕክተኛ መሆናቸውን በይፋ በመ

[1] ለማብራራት የተጨመረ ቃል ነው ።

ግለጽ ሕዝቡ ያለበትን ድክመት ማለትም ጠማማ አመለካከት ጥሎ ቀናውን መንገድ እንዲይዝ ምን ማድረግ እንዳለበት ለማስተማር እንደመጡና እንዲመራበትም ሲጎተጉቱት መቆየታቸውን ለመረዳት ይቻላል ።

ነቢያትና መልዕክተኞች ምን አስተማሩ ለሚለው ጥያቄ ዝርዝር መልስ ለመስጠት የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ባለመሆኑና ሥፍራውም ስለማይበቃ ዝርዝር ታሪካቸውን ለማወቅ የሚሻ ሰው በግልጽ የወረዱትን መጻሕፍት እንደ ዘቡር ፣ ተውራት ፣ እንጂል ፣ ቁርዓን ያሉትን በማጥናት ለመረዳት ይችላል ። የቀሩት ነበያት ስላስተማሩትም የዲን መሠረተ ሃሳብ በጽሑፍ የተውት ቅርስ ባይኖርም ከታሪካቸው ጋር ተያይዞ ያስተማሩት ትምህርት ፍሬ ሃሳብ በቁርአን ስለተጠቀሰ ጠቅላላ ግንዛቤ ለማግኘት ይቻላል ። ዳሩ ግን ከመልዕክተኞቹ የተልዕኮ ዓላማ አንጻር ለጥያቄው በጥቅሉ መልስ ለመስጠት (ለማግኘት) ከተፈለገ የአላህን አንድ መሆንና አጋር የሌለው መሆን ፣ እርሱን ብቻ በጌታነት አምኖ ለፈቃዱ መገዛት ፣ እርሱ ያዘዛቸውን በጎ ተግባራትና ቀናውን ሥራ መሥራት ፣ የከለከላቸውን እርኩስ ተግባራትና መጥፎ ሥራዎችን መተው ፣ ግዴታው መሆኑን አውቆ እንዲያከብር በዘመናቸው ለነበረው ሕዝብ ያስተማሩ ለመሆኑ ከነቢያቱ ታሪክ ማህደር ለመረዳት ይቻላል ።

የአላህ መልእክተኞች የአላህን አንድ መሆን በማስተማራቸውና ሕዝቡን ወደ ቀናው መንገድ ለመምራት ጥሪ በማቅረባቸው ምክንያት ብቻ ከፍተኛ በደልና ስቃይ ይደርስባቸው እንደነበረም ከታሪክ የምንረዳው ሐቅ ነው ።

መልዕክተኞቹ ከአላህ ዘንድ ስለመላካቸው ማስረጃ እንዲያቀርቡ እየተጠየቁም ከሰው ልጅ የተለመደ የተፈጥሮ ሁኔታ ውጭ ማንም ሰው ሊሠራው ወይም ሊያሳየው የማይችል ተአምር ይዘው በመቅረብ ለማሳመን ቢሞክሩም ከጥቂቶች በቀር አብዛኛውን ሕዝብ ለማሳመን ከፍተኛ ችግር ገጥሞዋቸዋል ።

በዚህ መልክ በየዘመናቱ አንዱ መልዕክተኛ በሌላው (አንዳንዴ በማከታተል ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ እየሰነበተ) እየተተካ የሰው ልጅ የአላህን አንድ ብቻ መሆን አውቆ ለአላህ ፈቃድ ራሱን እንዲያስገዛ ተገቢውን ትምህርት ሲሰጡት ቆይተዋል ።

የአላህ መልዕክተኛ ኢሳ (እየሱስ) (ዓለይሂ ሰላም) ሰላም ይሁንላቸው እንጂልን (ወንጌልን) አስተምረው ከሄዱ በኋላ ከ፭፻ ዓመት በላይ ቆይቶ ለመጨረሻው የአላህ መልዕክተኛ ሙሐመድ (ሰ አ ዓ ወ) ቁርአን ወረደላቸው ። ቁርአን የወረደው በመካ አካባቢ ይኖሩ የነበሩት ዓረቦች በሥነ ጽሑፍ በጣም በተራቀቁና የቋንቋ ችሎታቸውም እጅግ በዳበረበት ዘመን ነው ። ሕዝቡ በተራቀቀበት ቋንቋ ወደር የለሽ የሆነ ጥራትና የላቀ ይዘት ያለው ቁርአን መውረድ ራሱ ለሙሐመድ ታላቅ ተአምራቸው ነው ። የሰው ልጆችና ጂኒዎች (አጋንንት) በሙሉ ተሰባስበው ቢረዳዱም መሰሉ የሆነን መጽሐፍ ለማቅረብ እንደማይችሉ በመግለጽ ቁርአን ለውድድር (ለፉክክር) ይጋብዛቸዋል ።

ቁርአን ከአላህ ዘንድ የወረደ ለመሆኑና መጻፍና ማንበብ የማይችሉ ሙሐመድ (ሰ.አ.ዓ.ወ) በዚያን ዘመን የቁርአንን ቅርጽና ይዘት ያለው ጽሑፍ ለመጻፍ ወይም ከሌላው ለመኮረጅ ፈጽሞ የማይችሉ ስለመሆናቸው ሼክ አብዱል መጂድ ፣ በጂዳ የንጉሥ አብዱልዓዚዝ ዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር ፣ ከቁርአን አንዳንድ አንቀጾችን በመውሰድ በካናዳ ሀገር ባካሄዱት ሴሚናር የሰጡትን ማብራሪያ በሚቀጥለው ምዕራፍ እንዳለ ተርጉመን እናቀርባለን ።

## ምዕራፍ ፬

**<u>የቁርአን ይዘት ከአላህ ለሰው ልጅ የወረደ መመሪያ ለመሆኑ ማረጋገጫ ነው ።</u>**

**<u>ይህ ሐቅ በሼኽ አዱልመጂድ ሲብራራ ፤</u>**

“ከሰው ልጅ አፈጣጠር እያንዳንዱ የአካሉ ክፍል የተለያየ ሚና እንደሚጫወት ይታወቃል ። የሚያስበው በአዕምሮው ሲሆን ስሜቱ የንዴትና የመገንፈል ባሕሪይው በቀልቡ (በልቡ እንደ ማለት ነው) እንደሚመራ ይነገራል ። የእስላም ዲን (ሃይማኖት) መለያው ዲኑን በአዕምሮ ተመራምረን እንድንቀበለው ማስተማሩ ነው ። አላህ ዲኑን በአዕምሮዋችን (በአንጎላችን) ተመራምረን እንድናጠናው ያዘናል ።

የማንኛውም ነገር ፣ ዕውቀት ጭምር መመራመሪያ መሣሪያ አዕምሮ ነው ። አዕምሮ የምርምሩን ተግባር ከመጀመሩ በፊት ለማየት በሚያስችለን ዓይን ፣ ማየትን ፣ ለመስማት በሚያስችለን ጆሮ አማካኝነት መስማትን ፣ ከተቀዳጀን በኋላ ነው ስለአየነውና ወይም ስለ ሰማነው ጉዳይ ማሰብና መመራመር የምንጀምረው ።

አላህ ክብሩ ይስፋና ፣ እነዚህን የማየት ፣ የመስማትና የማሰብ መሣሪያዎችን (ሕዋሳትን) ገና በእናታችን ማኅፀን ሳለን ሰጥቶናል ። ስለዚህ ከሁሉም ነገር በፊት እነዚህን ሕዋሳት የሰጠንን አላህ ፣ ስለ አላህ ሊያስተምሩን የተላኩትን መልዕክተኞች ፣ እንዲሁም ስለመድረሻችን ማወቅ ይኖርብናል ።

አላህ ክብሩ ይስፋና የተፈጠርንለትን ምክንያት እንዲያስተምሩንና እንዲመሩን መልዕክተኞችን ላካቸው ። አላህ መልዕክተኞቹ በቀላሉ ተቀባይነት እንደ ማያገኙና ሐሰተኞች ናችሁ እንደሚባሉም ስለሚያውቅ ዕውነተኞች ለመሆናቸው ማረጋገጫ ምልክት እየሰጠ ላካቸው ። ለነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.አ.ዓ.ወ) ምልክት እንዲሆናቸው ለሁሉ ዘመንና ሥፍራ አግባብነት ያለውን ቁርዓን ሰጥቶ ላካቸው ።

አላህ ክብሩ ይስፋና እንዲህ ይላል ፤

قُلْ أَيُّ شَيْءٍ أَكْبَرُ شَهَادَةً قُلِ ٱللَّهُ شَهِيدٌ بَيْنِي وَبَيْنَكُمْ    الأنعام ١٩

“ሙሐመድ ሆይ ! የትኛው ነገር ከፍተኛ ምስክርነት ሊሆን ይችላል ? በላቸው ። አላህ በኔና በእናንተ መሐል መስካሪ ነው በላቸው ።” (ም ፮ ቁጥር ፲፱)
አላህ ክብሩ ይስፋና እንዴት አድርጎ ለሙሐመድ ራሱ ምስክር ይሆናቸዋል ? ለሚለው ጥያቄ አላህ (ሲመልስ) እንዲህ ይላል ፤

لَٰكِنِ ٱللَّهُ يَشْهَدُ بِمَآ أَنزَلَ إِلَيْكَ أَنزَلَهُۥ بِعِلْمِهِۦ    النساء ١٦٦

“አላህ ምስክርነቱን የሚሰጠው ለሙሐመድ ባወረደው መጽሐፍ አማካኝነት ነው ፤ ያወረደውም በዕውቀቱ ነው ።” (ም ፬ ቁጥር ፩፻፷፮) ሲል ከፍተኛ የምስክርነት ቃሉን ሰጥቶዋል ።

ለሙሐመድ ይህን ዕውነታ (ፋክት) ማን ነገራቸው ? የአላህ ተአምር መሆኑ ግልጽ ይሆናል ። በዚህ ውይይት ምሳሌዎች ብቻ የምንወስድ ሲሆን ብዙ ምርምር የሚጠይቁ የቁርአን አንቀጾች ያሉ ስለሆነ ልንመረምራቸው ይገባል ።

## 4.2. በሰማይ የመተንፈስ ሁኔታና የአየር ሁኔታን በሚመለከት

ሰዎች (ከአቧዋራማው ምድር) ወደ ሰማይ ከፍ ባልን ቁጥር ንፁሕና ያልተበከለ አየር እናገኛለን የሚል አስተሳሰብ የነበራቸው መሆኑ የቅርብ ጊዜ ታሪክ ነው ። ይህም ይባልበት የነበረው አንዱ ምክንያት ወደ ላይ ከፍ ባልን ቁጥር አቧዋራ አይኖርም በሚል አስተሳሰብ ነበር ። ዳሩ ግን ከብዙ ምርምርና ሰው ሠራሽ በራሪዎችና አይሮፕላኖች ከተፈለሰፉ በኋላ ሁኔታው የተገላቢጦሽ ሆኖ ተገኝቶዋል ። ወደ ላይ ከፍ ባልን ቁጥር በአየር ውስጥ የሚገኘው የኦክሲጂን መጠን እየቀነሰ ስለሚሄድና የአየር ግፊት መጠንም ስለሚቀንስ በደረታችን ላይ የጥበት ስሜት እየተከሰተ የመተንፈስ ችግር ይገጥመናል ። ምድር ላይ ግን የኦክሲጂን እጥረት ባለመኖሩ የአየር ግፊት መጠንም ከፍተኛ በመሆኑ በደረታችን ላይ አንዳችም የጥበት ስሜት አይኖርም ፤ የመተንፈስም ችግር አይገጥምም ። ይህ ሁኔታ የሰው ልጅ ዕውቀት በምርምር እየጎለበተ ከመጣ በኋላ በአሁኑ ዘመን ሊታወቅ ችሎዋል ። ቀደም ባለው ጊዜ ግን አይታወቅም ነበር ። ዳሩ ግን ከአሥራ አራት ምእተ ዓመት በፊት የተገለጸው (የመጣው) ቁርአን ይህ ሁኔታ በትክክል ሲያስቀምጠው እንዲህ ይላል ፤

فَمَن يُرِدِ ٱللَّهُ أَن يَهۡدِيَهُۥ يَشۡرَحۡ صَدۡرَهُۥ لِلۡإِسۡلَٰمِۖ وَمَن يُرِدۡ أَن يُضِلَّهُۥ
يَجۡعَلۡ صَدۡرَهُۥ ضَيِّقًا حَرَجٗا كَأَنَّمَا يَصَّعَّدُ فِي ٱلسَّمَآءِۚ الأنعام ١٢٥

"አላህም ሊመራው የሚሻውን ሰው ደረቱን (ልቡን) ለእስልምና ይከፍትለታል ፤ ሊያጠማውም የሚሻውን ሰው ደረቱ ጠባብ ፣ ችጋራ ፣ ወደ ሰማይ ለመውጣት እንደሚታገል ያደርገዋል ።" (ም ፮ ቁጥር ፩፻፳፭) ታዲያ ለሙሐመድ አይሮፕላን ሳይኖራቸው ይህን ሁኔታ ማን ገለጸላቸው ?

## 4.3. መሬትና ተራሮችን በሚመለከት ፤

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ መሬትና ተራሮች አንድ ዓይነት ይዘት ያላቸውና ተራራም ከመሬት ተለይቶ በልዩ ልዩ ምክንያት የሚወጣ መሆኑ ሲነገር ቆይቶዋል ።

እ ኤ አ በ፲፰፻፶፪ ዓ/ም ከእንግሊዝ ሀገር አንድ አጥኚ ቡድን በሕንድ ሀገር የሚገኘውና በዓለም የታወቀውን ከፍተኛ ተራራ (ሂማላያን) በጎበኘበት ወቅት ቡድኑ ፍጹም አስደናቂ ነገር ያገኛል ። ከዚህ ጊዜ በኋላ የሳይንስ ሊቃውንት ከመሬት ስበት ጋር በማዛመድ የተለያዩ ተራሮችን ማጥናት ጀመሩ ። የጥናታቸውም ውጤት የተባለው ፍጹም አስደናቂ ነገር በሁሉም ተራሮች ላይ መገኘቱን አረጋገጡ ። ቀጥሎም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ "ሲስሞ ግራፍ" የተባለው መሣሪያ በመፈልሰፉ ምክንያት ስለመሬት የሚደረገው ጥናት በተሻለ ሁኔታ ሊከናወን ችሎዋል ። በየተራራው ሥር ጥልቀቱ የተራራውን 4¼ ጊዜ ርዝመት ያለው የተራራው አካል (ሥር) በመሬት ውስጥ መኖሩ እየታወቀ መጣ ። የተራራ ሥር (ሩት) ጠፍጣፋው መሬት ላይ (ገጥሞ) የሚቆም

ከዝናብ ውኃ ፣ ከቅጠላቸው ፣ ወይስ ከሌላ ነገር ፣ የሚለውን ካጠኑ በኋላ ምግባቸው የሚሠራው "ክሎሮፊል" ከሚባለው የቅጠላቸው አረንጓዴ ክፍል መሆኑን ተገንዝበዋል ። ቁርአን ይህን ዕውነታ ገልጾዋል ፤

وَهُوَ ٱلَّذِىٓ أَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءً فَأَخْرَجْنَا بِهِۦ نَبَاتَ كُلِّ شَىْءٍ فَأَخْرَجْنَا مِنْهُ خَضِرًا نُّخْرِجُ مِنْهُ حَبًّا مُّتَرَاكِبًا الأنعام ٩٩

"እርሱም ያ ከሰማይ ውኃን ያወረደ ነው ፤ በርሱም የነገሩን ሁሉ በቃይ አወጣን ፤ የተደራረበንም ቅንጣት ከርሱ የምናወጣ የሆነን ለምለም[1] (አዝመራ) ከርሱ አወጣን ፤" (ም ፮ ቁ ፺፱)

## 4.6. ባሕሮችን በሚመለከት ፤

እ ኤ አ በ፲፱፻፸፪ ዓ/ም የጀርመን ሳይንቲስቶች የሕንድ ውቅያኖስና የቀይ ባሕርን ባሕሪያት ሲያጠኑ የየራሳቸው የተለያየ ባሕሪያት ያላቸው መሆኑን አገኙ ። የሁለቱን ውኃዎች የተለያየ ክብደት (ዴንሲቲ) የተለያየ የጨው ይዘት (ሶልት ኮንቴንት) እና በውስጣቸው የሚገኙ ነፍሳት የመለያየት ሁኔታን አወቁ ። ሁለቱ ባሕሮች በተወሰነ ቦታ ላይ ይገናኛሉ ። (ሆኖም የመገናኛው ሥፍራ ወይም መስመር እንደ አየሩ ጠባይ ይለያያል ፤ (በመገናኛቸው ሥፍራ ላይ ልዩነታቸው በግልጽ የሚታይ ሲሆን ሁለቱ እንዳይደባለቁ የሚከላከል የሚመስል ግድግዳ መሳይ መስመር በግልጽ ይታያል ። ይህ መስመር ወደ ፊትና ወደ ኋላ ይመላለሳል ፤ ወይም ይረግባል ። ይህ ሁኔታ በጥቁር ባሕር ፣ በነጭ ባሕር ወዘተ - - ላይም መከሰቱን ተገንዝበዋል ። መስመሩንም በሳተ ላይት አማካኝነት ፎቶግራፍ ለማንሳት ችለዋል ። ይህን ዕውነታ ቁርአን እንዲህ ሲል ገልጾታል ፤

مَرَجَ ٱلْبَحْرَيْنِ يَلْتَقِيَانِ ﴿١٩﴾ بَيْنَهُمَا بَرْزَخٌ لَّا يَبْغِيَانِ الرحمن ١٩-٢٠

"ሁለቱን ባሕሮች የሚገናኙ ሲሆኑ ለቀቃቸው ። (እንዳይዋሐዱ) በመካከላቸው ጋራጅ አለለ ፤) አንዱ ባንዱ ላይ (ወሰን አያልፉም") (ም ፶፭ ቁጥር ፲፱-፳) ይህንንስ ለሙሐመድ ማን ገለጸላቸው ? የአላህ ተአምር መሆኑ አያጠያይቅም ። (ቀደም ባለው ጊዜ የነበሩት ተርጓሚዎች አንድ ዓይነት መጋረጃ መኖሩን ከመናገር በቀር በሚገባ ስላልተረዱት "አላህ ያውቃል" በማለት አልፈውታል)

## 4.7. አልሚ ምግቦች ከአንጀታችን ወደ ደም መግባቱን በሚመለከት ፤

ከብዙ ዘመናት ጥናት በኋላ የተመገብነው ምግብ ከጨጓራችን ወደ አንጀታች ደንዳኔ ከተዛወረ በኋላ ከተለያዩ ንጥረ ነገሮች (ኢንዛይምስ) ጋር በልዩ ዕጢዎች አማካኝነት ተደባልቆ በቀላሉ ሊወሰድ ወደሚችል የምግብ ንጥረ ነገር ነት ይለወጣል ።

ከተለወጠም በኋላ ተመጦ በደንዳኔው ወይም ከአንጀት ግድግዳዎች ውስጥ ወደ ደም ቧንቧ በመዛወር የተዘጋጀው ምግብ ወደ ሰውነታችን ይገባል ።

[1] አረንጓዴው ቡቃያ የሚል ቃል ነው ፣ የአረቢኛው ጽሑፍ የሚያመለክተው ።

ከዚያም በእናቶች (በተለይ) በደምና በፈርስ ﴿ فـرث ﴾ አማካኝነት ለሕፃናት አስፈላጊ የሆነው ምግብ በጡት ውስጥ በወተትነት ይዘጋጃል ። ቁርአን ይህን የምግብ መሥሪያ ሂደት ሲገልጽ ፤

وَإِنَّ لَكُمْ فِي ٱلْأَنْعَٰمِ لَعِبْرَةً نُّسْقِيكُم مِّمَّا فِي بُطُونِهِۦ مِنۢ بَيْنِ فَرْثٍ وَدَمٍ لَّبَنًا خَالِصًا
سَآئِغًا لِّلشَّٰرِبِينَ النحل ٦٦

"ለናንተም በግመል ፣ በከብት ፣ በፍየል ፣ በእርግጥ መገምገሚያ አለላችሁ ፤ በሆዶቹ ውስጥ ካለው ከፈርስና ከደም መካከል ጥሩ ወተትን ለጠጭዎቹ ተዋጭ ሲሆን እናጠጣችኋለን ።" (ም ፲፮ ቁ ፷፮)

ይህንንስ ለሙሐመድ በዚያን ዘመን ማን ነገራቸው ?

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ምሳሌዎች ለብዙ ዘመናት በተለያዩ ኮሌጆች ሰፋ ያለ ጥናት ከተደረገባቸው በኋላ የተገኙት ውጤቶች ናቸው ።

የትምህርቱ ዘርፍ የከዋክብትን ጥናት (አስትሮኖሚ) ፣ የማዕድን ጥናት (ጂኦ ሎጂ) የዕጽዋት ጥናት (ቦታኒ) ፣ የእንስሳት ጥናት (ዚኦሎጂ) ወይም የሰውነት ክፍል ጥናት (ፊዚኦሎጂ) የውኃ ጥናት (ሃይድሮሎጂ) ፣ ወዘተ - - የሚያጠ ቃልል ነው ።"

የሼክ አብዱልመጂድን ንግግር ለማጠቃለል የሚረዳ ሞሪስ ቦኬይል የተባለው ፀሐፊ "The Bible, the Qur'an and Science" (መጽሐፍ ቅዱስ ፣ ቁርአንና ሳይንስ) በተሰኘው መጽሐፉ ሲያጠቃልል በገጽ ፪፻፴፭ ላይ የጻፈውን ተርጉ መን እንጠቅሳለን ።

"በሙሐመድ ዘመን በነበረው የዕውቀት ደረጃ አንጻር ሲታይ በቁርአን ውስጥ የሚገኙት (በተለይ) ከሳይንስ ጋር የተያያዙት ብዙ አረፍተ ነገሮች የሰው ልጅ ሥራ ናቸው ብሎ ማመን የሚታሰብ አይሆንም ። በተጨማሪም ቁርአን በወህይ (በራዕይ) የወረደ ነው ማለት ብቻ ሳይሆን ስለትክክለኛነቱ (ከሥርዝ ድልዝና ከመጨመርና መቀነስ ነጻ ስለመሆኑ) የሚሰጠው ዋስትና እና የሳይ ንስ ይዘት ያላቸው ጽንሰ ሐሳቦች በእርሱ ውስጥ መገኘቱ በጣም ልዩ የሆነ ሥፍራ እንዲሰጠው ከማስገደዱም በላይ በዛሬው ዘመን ሲጠና (ይዘቱ) ለሰው ልጅ አገላለጽ እንደ መፈተኛ (ቻሌንጅ) ሆኖ ይታያል ።" ብሎዋል ።

ይህ አባባል ስለ ቁርአን ምንነት ለማወቅ ለሚሹ በቂ መነሻ ነው ። ቁርአኑን በጥልቀት በማጥናትም የራሳቸው የሆነ ማስረጃዎችን ለማግኘት ይችላሉ ። ከላይ የተጠቀሰው የሞሪስ ቦኬይል መጽሐፍ አንጻራዊ በሆነ ሁኔታ ቁርአንን የሚተነትን ስለሆነ አንባቢ መጽሐፉን ፈልጎ እንዲያነብ በዚህ አጋጣሚ እን ጋብዘዋለን ።

ባለፉት ምዕራፎች በየዘመኑ የተላኩት መልዕክተኞች ለሰው ልጅ ከአላህ ዘንድ መመሪያ እየወረደላቸው ሲያስተምሩትና ወደ ቀናው መንገድ ሲመል ሱት የቆዩ መሆናቸውን ፣ የመጨረሻው መልዕክተኛ የሆኑትም ሙሐመድ (ሰ አ ዓ ወ) የአላህ መመሪያ የሆነውን ቁርአን ይዘው የመጡና ያስተማሩ መሆኑ ተገልጾአል ።

ነቢዩ ሙሐመድ ያስተማሩት ሃይማኖት በአብዛኛው የዓለም ክፍል "እስላም" በሚል መጠሪያ የሚታወቅ ቢሆንም "እስላም" ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማብራራት ያስፈልጋል ። በሀገራችን በተለድምዶ አጠራር የሃይማኖቱ ተከታዮች "እስላም" ሃይማኖቱ ደግሞ "እስልምና" ተብሎ ቢታወቅም ይህ አጠራር ከሃይማኖቱ ትክክለኛው ስምና በዓለም አቀፉ ደረጃም ከተለመደው አጠራር የሚጋጭና አለመግባባትን የሚያስከትል በመሆኑ መታረም ይሆርበታል ። እስላም የሃይማኖቱ ስም ሲሆን የዕምነቱ ተከታዮች ትክክለኛው መጠሪያ ሙስሊም ነው ።

ስለዚህ "እስላም" ምን እንደሆነ ለአንባቢያን የተሻለ ግንዛቤ ለመስጠት በሚቀጥለው ምዕራፍ ይቀርባል ።

# ምዕራፍ ፭

## እስላም ማለት ምን ይሆን ?

ይህ እርእስት እስላምን ለተቀበለ አግኝ ብቻ ሳይሆን በሙስልሞች አካባቢ ለሚኖሩ ፣ ወይም ስለ እስላም ለማወቅ ለሚሻ ሁሉ መሠረታዊ መሆኑ አያጠያይቅም ።

5.1. እስላም የሚለው ቃል ከቋንቋ አንጻር ሲታይ ከአረብኛ ቃል "ሠሊመ" ከሚለው ግሥ የመነጨ መሆኑ ይታወቃል ። ትርጉሙም ፤

ሀ/ ግልጽ ከሆነ ወይም ከተደበቀ ጭንቀት ወይም ችግር መከራ ነፃ ወጣ ማለት ይሆናል ። እንዲሁም ፣

ለ/ በተጣሉ ወገኖች መሐል ዕርቅና ሠላም ወረደ ማለት ይሆናል ፤ እንዲሁም

ሐ/ ራስን ለሌላው ፈቃድ ማስገዛት ማለትም ይሆናል ።

"ሠሊመ" የሚለው ቃል ይህንን ሶስት ትርጉም ያጠቃለለ ነው ። ከዚህም ቃል እስላም የሚለው መጠሪያ ስም ሊመነጭ ይችላል ። እስላም የሚለውን መጠሪያ ለነቢዩ ሙሐመድ ሃይማኖት (ዲን) መለያ በማድረግ መላው ዓለም ሲጠቀምበት ይታያል ። ይህ ሁኔታ እንዴት ሊከሰት እንደቻለ ለማወቅ ያህል እንዲረዳ መግለጹ ጠቃሚ ነው ። እስላም የሚለውን መጠሪያ አላህ ሙሐመድ ላስተማሩት ሃይማኖት (ዲን) መጠሪያ እንዲሆን የመረጠው መሆኑን ከሚጠቁሙ የቁርአን አያቶች (አንቀጾች) አንዱን እንጠቅሳለን ።

ٱلْيَوْمَ أَكْمَلْتُ لَكُمْ دِينَكُمْ وَأَتْمَمْتُ عَلَيْكُمْ نِعْمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ ٱلْإِسْلَٰمَ
دِينًا ۚ المائدة ٣

"ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ ፤ ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ ፤ ለእናንተም እስልምናን [1] ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ ።" (ም ፭ ቁ ፫)

ስለዚህ አላህ ክብሩ ይስፋና ለነቢዩ ሙሐመድ ተከታዮች "እስላም" ሃይማኖት (ዲን) እንዲሆናቸው በመምረጡ ለሃይማኖቱ (ዲኑ) መጠሪያ ቃሉ ጸደቀ ማለት ነው ። በዚህ ዓይነት የመጣውና ለዲኑ መጠሪያ የሆነው "እስላም" የሚለው ቃል ከቋንቋ አንጻር ብቻ ሳይሆን በዲኑ በኩል ያለውን ትርጉም ማየቱ እጅግ ጠቃሚ ይሆናል ።

በዲኑ ወይም በሸሪዓ አንጻር "እስላም" ማለት ትርጉሙ አላህ ከራሱ በቀር ሌላ ሸሪክ (አጋር) የሌለው መሆኑን አምኖ መቀበልን ፤ ይህንንም ተገንዝቦ በሙሉ ልብና ቆራጥነት ለእርሱ መገዛትና መታዘዝን ፣ ከአላህ ዘንድ የተላኩትን ዲኖች መቀበልና በየዘመኑ ከአላህ ተልኮ ተግባራዊነት ባለው ዲን በፍጹም መመራት ማለት ይሆናል ።

---

[1] የተለመደውን ቃል ለትርጉም ተጠቀመበት እንጂ ቃሉ እስላም ነው ።

ያህንን ትርጉም ትክክለኛ ነው ለማሰኘት የሚረዱ አንዳንድ አንቀጾች ከቁር
አን መጥቀሱ ይረዳል ፣

قُلْ أَغَيْرَ ٱللَّهِ أَتَّخِذُ وَلِيًّا فَاطِرِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَهُوَ يُطْعِمُ وَلَا يُطْعَمُ ۗ قُلْ إِنِّيٓ
أُمِرْتُ أَنْ أَكُونَ أَوَّلَ مَنْ أَسْلَمَ ۖ وَلَا تَكُونَنَّ مِنَ ٱلْمُشْرِكِينَ

الأنعام ١٤

፩ "ሰማያትንና ምድርን ፈጣሪ ከሆነው አላህ ፣ እርሱ የሚመግብ ፣ የማይ
መገብ ሲሆን ፣ ሌላን አምላክ እይዛለሁኝ ? እኔ መጀመሪያ ትእዛዝን
ከተቀበለ ሰው ልሆን ታዘዝኩ ፤ ከአጋሪዎችም አትሁን (ተብያለሁ)
በላቸው ።" (ም ፮ ቁ ፲፬)

ከዚህ በቀላሉ ሙስልም ለአላህ ታዛዥና ለአላህ ሽሪክ (አጋር) የማያደርግ
መሆኑን እንረዳለን ።

وَلَا يَأْمُرَكُمْ أَن تَتَّخِذُوا۟ ٱلْمَلَٰٓئِكَةَ وَٱلنَّبِيِّـۧنَ أَرْبَابًا ۗ أَيَأْمُرُكُم بِٱلْكُفْرِ بَعْدَ إِذْ
أَنتُم مُّسْلِمُونَ آل عمران ٨٠

፪/ "መላዕክቶችና ነቢዮችን ጌቶችና ጠባቂዎች አድርጋችሁ እንድትወስዱ
ዋቸውም አላህ አያዛችሁም ። እንዴትስ ለአላህ ፈቃድ ለመገዛት ወስና
ችሁ ፤ ከተቀበላችሁ በኋላ እንድትክፉሩ (ከትክክለኛው መስመር ወጣ
ችሁ ለፈቃዱ እንዳትገዙ) ያዛችኋል ።" (ም ፫ ቁ ፹)

ከዚህ አንቀጽ ለመላዕክትና ለነቢዮች ሳይሆን ለአላህ ብቻ እንድንገዛና ፈቃ
ዱን እንድንፈጽም ማስፈለጉና ይህ ሙስልም ለመሆን መሠረታዊ ጉዳይ ፣
ከዚህ ውጭ መሆን ፈጣሪን የሚያስከድ መሆኑን እንገነዘባለን ።

وَمَنْ أَحْسَنُ دِينًا مِّمَّنْ أَسْلَمَ وَجْهَهُۥ لِلَّهِ وَهُوَ مُحْسِنٌ وَٱتَّبَعَ مِلَّةَ
إِبْرَٰهِيمَ حَنِيفًا ۗ النساء ١٢٥

፫/ "እርሱ መልካም ሠሪ ሆኖ ፊቱን ለአላህ ከሰጠና የኢብራሂምን መንገድ
ቀጥተኛ ሲሆን ፣ ከተከተለ ሰው ይበልጥ ሃይማኖቱ ያማረ ማን አለ ?"
(ም ፬ ቁ ፻፳፭) ካለ በኋላ ሌላው አንቀጽ ደግሞ የሚከተለውን አስፍሮ
ዋል ፤

وَأَنِيبُوٓا۟ إِلَىٰ رَبِّكُمْ وَأَسْلِمُوا۟ لَهُۥ الزمر ٥٤

፬/ "ወደ ጌታችሁ (በመጸጸት) ተመለሱ ፣ ለእርሱም ታዘዙ ።" (ም ፴፱
ቁጥር ፶፬) ከእነዚህ ሁለት አንቀጾች እስላም ማለት ራስን ወደ አላህ
መልሶ ለእርሱ መታዘዝ መሆኑን እንገነዘባለን ።

ከላይ ከተጠቀሱት አራት የቁርአን አንቀጾች እስላም ማለት አጋር የሌለው
ብቸኛ አላህን አምኖ መቀበልና ለእርሱ ፈቃድ ራስን ማስገዛትና መታዘዝ
ማለት መሆኑን ለመረዳት ይቻላል ። ስለዚህ በዲን አንጻር ለ"እስላም"
የሚኖረው ትርጉም ይህ መሆኑን በመገንዘብ ወደሚቀጥለው ትንተናችን
አንባቢ እንዲያመራ እንጋብዘዋለን ።

## 5.2. ዲን ወይም “የእስላም” ትምህርት

በየዘመናቱና በየሀገሩ አላህ ለሕዝቦች ነቢያትን መላኩን ከታሪክ እንግራለን ። አላህ ነቢያትን የሚልክበት ዋናው ምክንያት ለምዕመናኑ የአላህ ፈቃድ ምን እንደሆነ እንዲያስተምሩና ምዕመኑ ከተማረ በኋላ ለአላህ ፈቃድ ራሱን እንዲ ያስገዛና እንዲታዘዝ አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር ነው ። ከዚህ ውጭ አላህ ነቢያትን የሚልክበት ምንም ምክንያት አይኖርም ።

ይህን መሠረተ ሐሳብ አምነን ከተቀበልን በቀላሉ ዲን “እስላም” መሆኑን ከቃሉ ትርጉምና ከመጡለት (ከተላኩለት) ምክንያትም አንጻር እንረዳለን ። ከዚህ በትክክለኛ አስተሳሰብ ከተደረሰበት መደምደሚያ ባሻገር ነቢያት በሙሉ ያስተማሩት ዲን እስላም ለመሆኑ ከቁርአን አንዳንድ አንቀጾችን መጥቀስ ይጠቅማል ፣

፩/ **<u>የአላህ መልዕክተኛ ኑህ እንዲህ ብለዋል ፣</u>**

وَأُمِرْتُ أَنْ أَكُونَ مِنَ ٱلْمُسْلِمِينَ    يونس ٧٢

“- - - ከእስላሞች እንድሆንም ታዝዣለሁ ።” (ም ፲ ቁ ፸፪)

፪/ **<u>የአላህ መልዕክተኛ ኢብራሂም እንዲህ ብለዋል ፣</u>**

إِذْ قَالَ لَهُۥ رَبُّهُۥٓ أَسْلِمْ ۖ قَالَ أَسْلَمْتُ لِرَبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ    البقرة ١٣١

“ጌታው ለርሱ ታዘዝ ባለው ጊዜ (መረጠው) ፣ ለዓለማት ጌታ ታዘዝኩ አለ ።” (ም ፪ ቁጥር ፩፻፴፩)

፫/ **<u>የአላህ መልዕክተኛ ዩሱፍ እንዲህ ብለዋል ፣</u>**

أَنتَ وَلِىِّۦ فِى ٱلدُّنْيَا وَٱلْءَاخِرَةِ ۖ تَوَفَّنِى مُسْلِمًا وَأَلْحِقْنِى بِٱلصَّٰلِحِينَ

يوسف ١٠١

“አንተ በቅርቢቱና በመጨረሻይቱ ዓለም ረዳቴ ነህ ፣ እስላም ሆኘ ግደለኝ ፥ በመልካሞቹም አስጠጋኝ ፣ (አለ) ።” (ም ፲፪ ቁ ፻፩)

፬/ **<u>የአላህ መልዕክተኛ ሙሣ እንዲህ ብለዋል ፣</u>**

يَٰقَوْمِ إِن كُنتُمْ ءَامَنتُم بِٱللَّهِ فَعَلَيْهِ تَوَكَّلُوٓا۟ إِن كُنتُم مُّسْلِمِينَ    يونس ٨٤

“ሕዝቦቼ ሆይ በአላህ አምናችሁ እንደ ሆነ ፥ በርሱ ላይ ተጠጉ ፣ ታዛ ዦች እንደሆናችሁ (በአላህ ላይ ትመካላችሁ) ።” (ም ፲ ቁ ፹፬)

፰/ የአላህ መልዕክተኛ ኢሣ እንዲህ ብለዋል ፤

فَلَمَّآ أَحَسَّ عِيسَىٰ مِنْهُمُ ٱلْكُفْرَ قَالَ مَنْ أَنصَارِيٓ إِلَى ٱللَّهِ قَالَ
ٱلْحَوَارِيُّونَ نَحْنُ أَنصَارُ ٱللَّهِ ءَامَنَّا بِٱللَّهِ وَٱشْهَدْ بِأَنَّا مُسْلِمُونَ

آل عمران ٥٢

"ኢሣ ከነርሱ ክሕደት በተሰማው ጊዜ ወደ አላህ (ተጨምረው) ረዳቶቼ እነማን ናቸው ? አለ ፤ ሐዋርያት እኛ የአላህ (ሃይማኖት) ረዳቶች ነን ፤ በአላህ አምነናል ፤ እኛም ትክክለኛ ታዛዦች መሆናችንን መስክር ፤ አሉ ።" (ም ፫ ቁ ፶፪)

፱/ አላህ ስለመልዕክተኛው ሙሐመድ እንዲህ ብሎዋል ፤

إِنَّآ أَوْحَيْنَآ إِلَيْكَ كَمَآ أَوْحَيْنَآ إِلَىٰ نُوحٍ وَٱلنَّبِيِّـۧنَ مِنۢ بَعْدِهِۦ ۚ وَأَوْحَيْنَآ إِلَىٰٓ
إِبْرَٰهِيمَ النساء ١٦٣

"እኛ ወደ ኑሕና ከርሱ በኋላ ወደ ነበሩት ነቢያት እንዳወረድን ፣ ወደ አንተም አወረድን ፣ ወደ ኢብራሂምም ፣ ወደ - - -" (ም ፬ ቁ ፩፻፷፫)

እነዚህአንቀጾች በሙሉ ቀደም ሲል በትክክለኛው አስተሳሰብ ከደረስንበት መደምደሚያ በመነሳት አላህ የሚልካቸው መልዕክተኞች የእርሱን ፈቃድ የሚያስተምሩና የሰው ልጅ ለአላህ ፈቃድ ራሱን ተገዥ እንዲያደርግ የሚመሩ ስለሆነ ያስተማሩት ዲን "እስላም" ነው ፤ ያልነው በቁርአን አላህም ያረጋገጠው መሆኑን ያስረዱናል ።

## 5.3. የአላህ መልዕክተኞች ባስተማሩት ትምህርት (ዲን) መሐል ልዩነት ለምን ይታያል ?

በየዘመኑ የተላኩት የአላህ መልዕክተኞች ያስተማሩት "እስላም" ነው ፤ ከተባለ በኋላ የግዴታ የሚነሳና መልስ ማግኘት የሚገባው ጥያቄ አለ ። እርሱም ለአላህ መልዕክተኛ ሙሣ ፣ በተሰጠው መጽሐፍ "ተራውት" (ኦሪት) ለአላህ መልዕክተኛ ዳውድ በተሰጠው መጽሐፍ "ዘቡር" (መዝሙረ ዳዊት) ፣ ለአላህ መልዕክተኛ ኢሣ ፣ በተሰጠው መጽሐፍ "እንጂል" (ወንጌል) እንዲሁም ለአላህ መልዕክተኛ ሙሐመድ በተሰጠው መጽሐፍ "ቁርአን" (ቅዱስ ቁርአን ) መሐል ልዩነት ስለሚታይና በዕምነቱ ተከታዮች መሐልም ልዩነት ስለሚታይ ፣ ይህ ልዩነት እንዴት ሊከሰት ቻለ ? የሚል ነው ።

የዚህ ጥያቄ መልስ የሚከተሉ ነጥቦችን ያቀፈ ይሆናል ፤

፩/ ማንኛውም የአላህ መልዕክተኛ የተላከው የሰው ልጅ አንድን አምላክ ብቻ እንዲያምንና ዲባዳ እንዲያደርግ (እንዲያመልክ) መሆኑን ፤

፪/ ከሙሐመድ በፊት የተላኩት መልዕክተኞች ለሕዝባቸው በቀጥታ የተላኩ ሲሆን ፣ ነቢዩ ሙሐመድ ግን ለዓለም ሕዝብ በሙሉ መሆኑን ፤

ንተ ላይ ያለብህ ማድረስ ብቻ ነው ። አላህም ባሮቹን ተመልካች ነው ።”
(ም ፫ ቁጥር ፲፰-፳)

شَرَعَ لَكُم مِّنَ ٱلدِّينِ مَا وَصَّىٰ بِهِۦ نُوحًا وَٱلَّذِىٓ أَوْحَيْنَآ إِلَيْكَ وَمَا وَصَّيْنَا
بِهِۦٓ إِبْرَٰهِيمَ وَمُوسَىٰ وَعِيسَىٰٓ أَنْ أَقِيمُوا۟ ٱلدِّينَ وَلَا تَتَفَرَّقُوا۟ فِيهِ كَبُرَ عَلَى ٱلْمُشْرِكِينَ
مَا تَدْعُوهُمْ إِلَيْهِ ٱللَّهُ يَجْتَبِىٓ إِلَيْهِ مَن يَشَآءُ وَيَهْدِىٓ إِلَيْهِ مَن
يُنِيبُ ﴿١٣﴾ وَمَا تَفَرَّقُوٓا۟ إِلَّا مِنۢ بَعْدِ مَا جَآءَهُمُ ٱلْعِلْمُ بَغْيًۢا بَيْنَهُمْ وَلَوْلَا
كَلِمَةٌ سَبَقَتْ مِن رَّبِّكَ إِلَىٰٓ أَجَلٍ مُّسَمًّى لَّقُضِىَ بَيْنَهُمْ وَإِنَّ ٱلَّذِينَ أُورِثُوا۟
ٱلْكِتَٰبَ مِنۢ بَعْدِهِمْ لَفِى شَكٍّ مِّنْهُ مُرِيبٍ ﴿١٤﴾ فَلِذَٰلِكَ فَٱدْعُ
وَٱسْتَقِمْ كَمَآ أُمِرْتَ وَلَا تَتَّبِعْ أَهْوَآءَهُمْ وَقُلْ ءَامَنتُ بِمَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ مِن
كِتَٰبٍ وَأُمِرْتُ لِأَعْدِلَ بَيْنَكُمُ ٱللَّهُ رَبُّنَا وَرَبُّكُمْ لَنَآ أَعْمَٰلُنَا وَلَكُمْ
أَعْمَٰلُكُمْ لَا حُجَّةَ بَيْنَنَا وَبَيْنَكُمُ ٱللَّهُ يَجْمَعُ بَيْنَنَا وَإِلَيْهِ ٱلْمَصِيرُ

الشورى ١٣-١٥

“ለናንተ ከሃይማኖት ያንን በርሱ ኑሕን ያዘዘበትን ደነገገላችሁ ፤ ያንንም ወዳንተ ያወረድነውን ያንንም በርሱ ኢብራሂምን ፣ ሙሳንና ኢሣንም ያዘዘበትን ሃይማኖት በትክክል አቋቁሙ ፤ በርሱም አትለያዩ ማለትን (ደነገገን) ፣ በአጋሪዎቹ ላይ ያ ወደርሱ የምትጠራቸው ነገር ከበዳቸው ፤ አላህ የሚሻውን ሰው ወደርሱ (እምነት) ይመርጣል ፤ የሚመለስንም ሰው ወደርሱ ይመራል ። (የሃይማኖት ሰዎች) ዕውቀቱም ከመጣላቸው በኋላ በመካከላቸው ለምቀኝነት እንጂ ለሌላ አልተለያዩም ፤ እስከ ተወሰነም ጊዜ (በማቆየት) ከጌታህ ያለፈች ቃል ባልነበረች ኖሮ በነሱ መካከል (አሁን) በተፈረደ ነበር ። እነዚያም ከኋላቸው መጽሐፉን እንዲወርሱ የተደረጉት ከእርሱ በእርግጥ በአወላዋይ ጥርጣሬ ውስጥ ናቸው ። ለዚህ (ድንጋጌ ሰዎችን) ጥራ ፤ እንደታዘዝከውም ቀጥ በል ፤ ዝንባሌዎቻቸውንም አትከተል ፤ በላቸውም ከመጽሐፉ አላህ ባወረደው አመንኩ ፤ በመካከላችሁም ላስተካክል ታዘዝኩ ፤ አላህ ጌታችን ጌታችሁም ነው ፤ ለኛ ሥራዎቻችን አሉን ፣ ለናንተም ሥራዎቻችሁ አሏችሁ ፤ በኛና በናንተ መካከል ክርክር የለም ፤ አላህ (እኛና እናንተን) ) በመካከላችን ያሰባስባል ። መመለሻም ወደርሱ ብቻ ነው ።” (ም ፵፪ ቁጥር ፲፫-፲፭)

እነዚህ የቁርአን አንቀጾች ለተነሳው ጥያቄ አጥጋቢ የሆነ መልስ ከመስጠታቸው ባሻገር በመልዕክተኞች አማካኝነት በተለያዩ ዘመናት ለሕዝቦች ከአላህ የተላኩት ሃይማኖቶች በመሠረቱ አንድ መሆናቸውንና ሙሐመድ የተላኩት በዚያው ሆና ከእርሳቸው በፊት በተላኩት መጽሐፍት በሙሉ የሚያምኑና የተላኩትም ለማስተካከል መሆኑን አንባቢ ሊረዳ ይችላል ።

## 5.3. አላህ ከምዕመናን “እስላም” እንጂ ሌላ እምነት የማይቀበል ስለመሆኑ ፤

ከአላህ ዘንድ የተላከው የዲን መመሪያ እስላም ሆኖ በየዘመኑ እንደ ሕዝቡ የእድገት ደረጃ እየተስተካከለና እየዳበረ የመጣ መሆኑ ከተረጋገጠ እንዱ ትውልድ ከእርሱ በፊት በተላኩት የአላህ መልዕክተኞች የማመንና ያመጡትን መጽሐፍ የመቀበል ፣ በእርሱ ዘመን የተላከውን መልዕክተኛ ሙሉ በሙሉ

ተቀብሎ የእርሱን መመሪያ መከተል ግዴታው ይሆናል ። ሙሐመድ የመጨረሻው መልዕክተኛ ሲሆኑ በእርሳቸው አማካኝነት የመጣው ቁርአንም የመጨረሻው የአላህ መመሪያ ስለሆነ ከበስተፊቱ የተላኩትን መጽሐፎች በማስተካከል ፣ በማዳበርና አንዳንዱን መመሪያም ሽሮ በሌላ የመተካት ባሕሪይ ይዞ ስለመጣ ከእርሱ በፊት የመጡትን መጽሐፎች አምና ከመቀበል ባሻገር ለመመሪያነት ከእርሱ ሌላን መርጦ ለመያዝ የማይቻል መሆኑ ግልጽ ነው ።

አላህም ክብሩ ይስፋና ከእስላም በቀር ሌላ ሃይማኖት ለሚሻ ወይም ለሚከተል ተቀባይነት የማይኖረው ለመሆኑ እንዲህ ይላል ፤

وَمَن يَبْتَغِ غَيْرَ ٱلْإِسْلَٰمِ دِينًا فَلَن يُقْبَلَ مِنْهُ وَهُوَ فِى ٱلْءَاخِرَةِ مِنَ ٱلْخَٰسِرِينَ

آل عمران ٨٥

“ከእስልምና ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈጽሞ ከእርሱ ተቀባይ የለውም ፤ እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሣሪዎቹ ነው ።” (ም ፫ ቀ ፹፭'

ሙሐመድ የተላኩትም ለመላው የዓለም ሕዝብ መሆኑን አላህ ሲያረጋግጥ እንዲህ ይላል ፤

وَمَآ أَرْسَلْنَٰكَ إِلَّا كَآفَّةً لِّلنَّاسِ بَشِيرًا وَنَذِيرًا سبا ٢٨

“አንተንም ለሰዎች ሁሉ በመላ ፣ አብሳሪና አስፈራሪ አድርገን ቢሆን እንጂ አልላክንህም ፤” (ም ፴፬ ቁጥር ፳፰)

## 5.5. የመጨረሻው የአላህ መመሪያ ሆና የመጣው የቁርአን መሠረታዊ ትምህርት

ከላይ በቀረቡት ንኡሳን ርእሶች አማካኝነት “እስላም” ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጉሙ ፣ አላህ በየዘመኑ መልዕክተኞቹን የላከበት ምክንያት ምን እንደሆነና ዓላማው አንድ መሆኑን ፣ “እስላም” ያስተማሩና ከ“እስላም” በቀር ሌላ እምነት በአላህ ዘንድ ተቀባይነት የማይኖረው መሆኑ ተገልጾአል ።

በዚህ ንኡስ አርእስት ሥር ከበፊቱ የነበሩትን የሃይማኖት ትምህርት እያስተካከለ ፣ እያሻሻለና አዳዲስ ደንቦችን እየደነገገ እስከ አኺራ (ምፅዓት) ድረስ ለየዘመኑ ተስማሚ ሆና ወርዶዋል ተብሎ በሙሐመድ (ሰ አ ዓ ወ) አማካኝነት የመጣልንን የእስላም ዲን ፤ በተለይም የቁርአንን መሠረታዊ ትምህርት ከዋና ዋናው ነጥቦች አጠር ባለ መልክ እናቀርባለን ።

### 5.5.1. (አምልኮት/ ዒባዳህ) عبـــادة

ዒባዳህ (አምልኮትን) በሚመለከት በርካታ አንቀጾች በቁርአን ውስጥ የሚገኙ ሲሆን ጥቂቶቹን እንጠቅሳለን ።

وَقَضَىٰ رَبُّكَ أَلَّا تَعْبُدُوٓا۟ إِلَّآ إِيَّاهُ الإسراء ٢٣

ላህ ፈቃድ በእርሱ ቀደም ሲል በተወሰነው መሠረት ብቻ የሚፈጸም "በቀ ዳዕና በቀደር" መሆኑን እንድናምን ፤ በጠቅላላው በዓይናችን ባላየናቸው ከላይ በተጠቀሱት ጽንሰ ሐሳቦች እንድናምን አስተምሮ አዞናል ።
እንዲሁም አላህ በቁርአን ባዘዘውና በሙሐመድ በተብራራው መሠረት ሶላትን ፤ ሲያምን (ጾምን) ዘካትን ፤ (ምጽዋት) አቅማችን ሲፈቅድ በሕይወታችን ቢያንስ አንድ ጊዜ ሐጅ ማድረግን ተቀብለን በተግባር እንድንፈጽም ፤ አላህ ያዘናል ። እነዚህ ከዒባዳ ጋር የተያያዙ ሲሆን ከነዚህም ሌላ ማህበራዊ ኑሮን በሚመለከት ትክክለኞች እንድንሆን ፤ በጎ ተግባርን እንድንፈጽም ፤ ለቅርብ ዘመዶች ማድረግ የሚገባንን ችሮታ እንድናደርግ ፤ በሽያጭ ተግባር ከተሠማራን ሚዛንን እንድንሞላ (እንዳናጭበረብር) ፤ ቃል ኪዳን ከገባን ቃል ኪዳናችንን እንድናከብር ፤ ዕውነተኞች ፤ ታጋሾችና ትሁቶች እንድን ሆን ፤ አላህ በግልጽ አዞናል ።

እነዚህን መሠረታዊ ትእዛዛት የሚያረጋግጡ የቁርአን አንቀጾችን እንጠቅ ሳላን ። ዒባዳን በሚመለከት ፤

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ ءَامِنُوا۟ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ وَٱلْكِتَٰبِ ٱلَّذِى نَزَّلَ عَلَىٰ
رَسُولِهِۦ وَٱلْكِتَٰبِ ٱلَّذِىٓ أَنزَلَ مِن قَبْلُ ۚ وَمَن يَكْفُرْ بِٱللَّهِ وَمَلَٰٓئِكَتِهِۦ
وَكُتُبِهِۦ وَرُسُلِهِۦ وَٱلْيَوْمِ ٱلْءَاخِرِ فَقَدْ ضَلَّ ضَلَٰلًۢا بَعِيدًا النساء ١٣٦

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ ! በአላህና በመልዕክተኛው ፤ በዚያም በመልዕክ ተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ ፤ በዚያም ከበፊቱ ባወረደው መጽሐፍ እመኑ ፤ በአላህና በመላእክቱም ፤ በመጽሐፎቹም ፤ በመልዕክተኞቹም ፤ በመጨረሻውም ቀን የካደ ሰው (ከዕውነት) የራቀን መሳሳት በእርግጥ ተሳ ሳተ ።"[2] (ም ፬ ቁ ፩፻፴፮)

أَفَحَسِبْتُمْ أَنَّمَا خَلَقْنَٰكُمْ عَبَثًا وَأَنَّكُمْ إِلَيْنَا لَا تُرْجَعُونَ المؤمنون ١١٥

"የፈጠርናችሁ ፤ ለከንቱ መሆኑን እናንተም ወደኛ የማትመለሱ መሆናችሁን ጠረጠራችሁን ?" (ም ፳፫ ቁጥር ፩፻፲፭)

وَأَقِيمُوا۟ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتُوا۟ ٱلزَّكَوٰةَ وَٱرْكَعُوا۟ مَعَ ٱلرَّٰكِعِينَ البقرة ٤٣

"ሶላትንም ደንቡን ጠብቃችሁ ስገዱ ፤ ዘካንም (ግዴታ ምጽዋትን) ስጡ ፤ (ለጌታችሁ) ከአጎንባሾች ጋርም አጎንብሱ ።" (ም ፪ ቁ ፵፫)

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ كُتِبَ عَلَيْكُمُ ٱلصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى ٱلَّذِينَ
مِن قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ البقرة ١٨٣

[2] በሌላ አነጋገር ፤ የፈጠርናችሁ ለቀልድ መሰላችሁን ? እናንተም ወደኛ የማትመለሱ መሰላችሁ ? ተብሉ ተተርጉሞዋል ።

"እላንተ ያመናችሁ ሆይ ! ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደተጻፈ ፣ በናንተም ላይ ተጻፈ ፤ (ተደነባ) ፤ ልትጠነቀቁ ይከጀላልና ።"
(ም ፪ ቁጥር ፩፻፹፫)

وأتموا الحج والعمرة لله

البقرة ١٩٦

"ሐጅንና ኡምራንም ለአላህ ሙሉ ፤" ም ፪ ቁጥር ፻፺፮

<u>ማህበራዊ ኑሮን በሚመለከት</u> ፤

"አላህ በማስተካከል ፣ በማሳመርም ፣ ለዝምድና ባለቤት በመስጠትም ያዛል ፤"
(ም ፲፮ ቁ ፺)

ስለእስላም ሸሪዓ (አላህ ያዘዛቸውና የከለከላቸውን ተግባራት በሚመለከት) ለማወቅ ለሚፈልጉ በዝርዝር በመደበኛ ትምህርት እስከ ኮሌጅ ከዚያም በአንድ መስክ የላቀ ጥናት (SPECIALISE) ሊደረግ የሚችል በጣም ሰፊ ትምህርት በመሆኑ እዚሁ ሊቀርብ ባይችልም ዋናውን መልዕክት ለአንባቢ ለማቅረብ በሚረዳ መልክ በቁርአን ተጠቃሎ የቀረበውን አንቀጽ ከመጥቀሳችን በፊት በአላህ የታዘዝነውን እንዳቀረብን ሁሉ በአላህ የተከለከሉ ዋና ዋና ነጥቦችንም እናቀርባለን ።

አላህ ከብሩ ይስፋና አጋር እንዳናደርግለት ፣ ልጆቻችንን እንዳንገድል ፣ ብልግናን ፣ ጸያፍ ተግባርንና ግፍን እንዳንፈጽም ፣ በዙልም (በበደል) በግፍ ነፍስን እንዳንገድል ፣ አባት የሌላቸው ሕፃናትን ሀብት እንዳንነካ ፣ በሐሰት እንዳንመሰክር ፣ እንዳናታልል ፣ እንዳንኩራራና ትዕቢተኛም እንዳንሆን ፣ ብኩን እንዳንሆን ፣ ቆንቋናም እንዳንሆን ፣ እንዳናመነዝር ፣ ከሚያሰክር መጠጥ እንዳንደርስ ፣ ቁማር እንዳንጫወት ፣ እንዳንሰርቅ ፣ እንዳንዋሽ ፣ ሌሎችን እንዳናማ ፣ ንፁሐንን እንዳናሳጣ ፣ በራሱ የሞተን እንስሳ (በከት) እንዳንበላ ፣ ደም ፣ የዓሣማና ከርከሮን ሥጋም እንዳንበላ ፣ ከአላህ በቀር ለሌላው የተሰዋን ከብት ፣ ታንቆ የተደገለን ከብት እንዳንበላ ከልክል አድርጎዋል ።

አባቶቻችን አግብተዋቸው የነበሩትን ሴቶች እንዳናገባ ፣ የእርስ በእርሳችን የሆነውን ገንዘብ አግባብ ባልሆነ መንገድ እንዳንበላ ይከለክለናል ።

አግባብ ካላቸው የቁርአን አንቀጾች እንጠቅሳለን ፤

قل تعالوا أتل ما حرم ربكم عليكم ألا تشركوا به شيئا
وبالوالدين إحسانا ولا تقتلوا أولادكم من إملاق نحن نرزقكم
وإياهم ولا تقربوا الفواحش ما ظهر منها وما بطن ولا تقتلوا
النفس التي حرم الله إلا بالحق ذلكم وصاكم به لعلكم تعقلون ﴿١٥١﴾
ولا تقربوا مال اليتيم إلا بالتي هي أحسن حتى يبلغ أشده وأوفوا الكيل
والميزان بالقسط لا نكلف نفسا إلا وسعها وإذا قلتم فاعدلوا ولو
كان ذا قربى وبعهد الله أوفوا ذلكم وصاكم به لعلكم
تذكرون ﴿١٥٢﴾ وأن هذا صراطي مستقيما فاتبعوه ولا تتبعوا السبل
فتفرق بكم عن سبيله ذلكم وصاكم به لعلكم تتقون

الأنعام ١٥١-١٥٣

"ኑ ፣ ጌታችሁ በናንተ ላይ እርም ያደረገውን ነገር ፡ (በርሱም ያዘዛችሁን) ነገር ላንብብላችሁ በላቸው ፣ በርሱ (በአላህ) ምንንም ነገር አታጋሩ ፣ ሉወላጆችም በጎን ሥራ (ሥሩ) ፡ ልጆቻችሁንም ከድህነት (ፍራቻ) አትግደሉ ፣ እኛ እናንተንም እነርሱንም እንመግባችኋለንና ፣ መጥፎ ሥራዎችንም ከርስዋ የተገለጸውንም ፣ የተደበቀውንም ሁሉ አትቅረቡ ፤ ያችንም አላህ እርም ያረጋትን ነፍስ በሕግ ቢሆን እንጂ አትግደሉ ፤ ይሃችሁ[3] ታውቁ ዘንድ (አላህ) በርሱ አዘዛችሁ ።

የየቲምንም[4] ገንዘብ ብርታቱን (አካለ መጠን) እስኪደርስ ድረስ በዚያች እርስዋ መልካም በሆነች ሁኔታ እንጂ አትቅረቡ ፤ ስፍርንና ሚዛንንም በትክክሉ ሙሉ ፤ ነፍስን ችሎታዋን እንጂ አናስገድድም ፤ በተናገራችሁም ጊዜ በዘመዶቻችሁ ላይ ቢሆንም እንኳ (እውነትን በመናገር) አስተካክሉ ፤ በአላህም ቃል ኪዳን ምሉ ፤ ይሃችሁ ትገሠጹ ዘንድ በርሱ አዘዛችሁ ።

ይህም ቀጥተኛ ሲሆን መንገዴ ነው ፤ ተከተሉትም (የጥመት) መንገዶችንም አትከተሉ ፣ ከ(ቀጥተኛው) መንገድ እናንተን ይለያዩዋችኋልና ። ይሃችሁ ትጠነቀቁ ዘንድ በርሱ አዘዛችሁ ።" (ም ፮ ቁጥር ፩፻፶፩-፩፻፶፫)

እነዚህ ጥቂቱ የቁርአን አንቀጾች ሲሆኑ አንባቢ ከ"እስራዕ" ምዕራፍ ፲፯ ከአንቀጽ ፳፫-፴፱ ፣ እንዲሁም ከ"አልሁጅራት" ምዕራፍ ፵፱ ከአንቀጽ ፱-፲፪ ያሉትን ማንበቡ ተጨማሪ መመሪያዎችን እንዲያውቅ ይረዳዋል ። ከነዚህም ሌላ እያሌ የቁርአን አንቀጾች ደግ ተግባሮችን ከመጥፎ በመለየት በደጉ የሚያዙና ከመጥፎ የሚከለክሉ ስላሉ አንባቢ ቁርአንን በተጨማሪ ደግሞ በማንበብ ይበልጥ መረዳት ይኖርበታል ።

ባጭሩ "እስላም" የሚለው ቃል ከላይ የተዘረዘሩትን የሚያጠቃልል ስለሆነ በዚህ ጽሑፍ በጥቅሉ የቀረበው ሃሳብ በተለይ ስለ "እስላም" ምንነት ለማያውቁ መንደርደሪያ እንደሚሆን ተስፋ ይደረጋል ።

## 5.5.3. "እስላምን" መቀበል የግል ምርጫ ነው ?

አላህ ክብሩ ይስፋና "እስላም" ምን እንደሆነ የሰው ልጅ በነቢያትና በመልዕክተኞች አማካኝነት እንዲያውቅ ካደረገ በኋላ አስቀድሞ በዘረጋው ፕላን (እቅድ) መሠረት ከፍጥረታት ሁሉ መርጦ በሚያስብ አእምሮ የካነውን የሰው ልጅ የራሱን ምርጫ እንዲያደርግ ሙሉ ሥልጣን ሰጠው ። የሰው ልጅ ከፈለገ "እስላምን" ተቀብሎ በትክክለኛው ጎዳና እንዲመራና በመጭው ዓለም ወሮታውን እንዲያገኝ ፣ ከፈለገም "እስላምን" ሳይቀበል ለፈጸመው በደል ተጠያቂ እንዲሆን ምርጫው የራሱ እንዲሆን ተደርጎዋል ። የመልእክተኞችሚና የአላህን መልዕክት ማድረስ ፣ ማብራራት ፣ ማስታወስ እና ማስጠንቀቅ እንጂ የሰው ልጅ ቀናውን መንገድ እንዲይዝ የሚያስገድዱ አይደሉም ። አላህ ይህን አስመልክቶ እንዲህ ይላል ፤

لَآ إِكۡرَاهَ فِي ٱلدِّينِۖ قَد تَّبَيَّنَ ٱلرُّشۡدُ مِنَ ٱلۡغَيِّۚ البقرة ٢٥٦

---

[3] እነሆ ።

[4] የሙት ልጆች ።

“በሃይማኖት ማስገደድ የለም ፣ ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ ፣”
(ም ፪ ቁጥር ፪፻፶፮)

(በሃይማኖት ማስገደድ የሌለና “እስላም” ያልተቀበሉትን ያላስገደደ መሆኑን ራሱን በቻለ ምዕራፍ እናቀርባለን ።)

ከላይ እንደተገለጸው “እስላም” ለእያንዳንዱ ሰው የተላከ ዲን ሆኖ ግለሰቡ አእምሮውን ተጠቅሞ በራሱ ፈቃድ ከወደደ የሚቀበለው እንጂ በጭፍን አባትና እናቱ የተቀበሉት እምነት ስለሆነ ብቻ የሚከተለው ወይም ያለፈቃዱ ተገዶ የሚቀበለው ዲን አለመሆኑን አንባቢ ሊገነዘበው ይችላል ።

አላህ ክብሩ ይስፋና አንድ ሰው ቤተሰቡ ስለተቀበለው ብቻ አንድን እምነት የሚከተለውን ሰው አላዋቂነት ሲጠቁም እንዲህ ይላል ፣

وَإِذَا فَعَلُوا فَاحِشَةً قَالُوا وَجَدْنَا عَلَيْهَا آبَاءَنَا وَاللَّهُ أَمَرَنَا بِهَا ۗ قُلْ إِنَّ اللَّهَ

لَا يَأْمُرُ بِالْفَحْشَاءِ ۖ أَتَقُولُونَ عَلَى اللَّهِ مَا لَا تَعْلَمُونَ    الأعراف ٢٨

“መጥፎንም ሥራ በሠሩ ጊዜ በርስዋ ላይ[5] አባቶቻችንን አገኘን ፣ አላህም በእርስዋ አዞናል ይላሉ ፣ አላህ በመጥፎ ነገር አያዝም ፣ በአላህ ላይ የማታውቁትን ትናገራላችሁን ? በላቸው ።” (ም ፯ ቁጥር ፳፰)
ቀጥሎም ቤተሰቡ የሚያደርገውን ወይም የሚከተለውን እምነት በጭፍን መከተሉ ተገቢ አለመሆኑን ከመግለጽ አልፎ ለአላህ አጋር እንዲያደርግ አባት እናቱ ካዘዙት ለሌላው ትእዛዛቸው ተገዥ እንዲሆን የሰውን ልጅ አላህ ያዘዘው ቢሆንም በዚህ ነጥብ ላይ ግን እንዳይታዘዛቸው በግልጽ ራሱ አዙዋል ።
ቁርአን እንዲህ ይላል ፣

وَإِن جَاهَدَاكَ عَلَىٰ أَن تُشْرِكَ بِي مَا لَيْسَ لَكَ بِهِ عِلْمٌ فَلَا تُطِعْهُمَا

لقمان ١٥

“ለአንተ በእርሱ ዕውቀት የሌለህን ነገር በኔ እንድታጋራ ቢታገሉህም አትታዘዛቸው ።” (ም ፴፩ ቁጥር ፲፭)

አላህ ክብሩ ይስፋና ስለእርሱ መኖር ይህች ዓለም ጊዜያዊና አላቂ መሆኑዋን ፣ የእኛ በዓለም መኖር ለምክንያትና ለዓላማ መሆኑን ፣ በጊዜያዊ ጫዋታና ደስታ ፣ እንዲሁም ሥጋዊ ፍላጎታችንን ለማርካት ብቻ በመሯሯጥ ጊዜያችንን በከንቱ እንዳናሳልፍ እንደ አፈጣጠራችንና እንደ አኗኗታችን ሁሉ በትንሣኤው ዕለት እንደምንነሣ አያሌ አያቶችንና (ምልክቶችን) ምሳሌዎችን እየጠቀሰ ፣ አስታውሱ ፣ አስተውሉ ፣ አስቡ ፣ እያለ ወደ ቀናው መንገድ እንድንመራ በመልዕክተኞቹ አማካኝነት በማስተማር እንድናውቅ አድርጎዋል ።

ይህን ሁሉ በማድረግ የሰው ልጅ ወደ ቀናው መንገድ እንዲመራ ካመቻቸ በኋላ አላህ ባስቀመጠው አጠቃላይ ፕላን (እቅድ) መሠረት ማንም ሰው በአእምሮው ተጠቅሞ ከሚያምን ወይም ከሚክድ (ከሚከፍር) በስተቀር “እስላ

[5] በመጥፎ ሥራ ።

ምን" ለመቀበል ግዳጅ እንዳይኖር ደጋግሞና አበክሮ ለነቢያቱ አስታውቆ ዋል ።

ከላይ ይህንን በሚመለከት አንዳንድ አንቀጾችን ከቁርአን በመጥቀስና ራሱን በቻለ ምዕራፍ የሚብራራ መሆኑ ቢገለጽም ሁለት አንቀጾች እዚህም ላይ መጥቀሱ አግባብ ይሆናል ፤

وَلَوْ شَآءَ رَبُّكَ لَآمَنَ مَن فِي ٱلْأَرْضِ كُلُّهُمْ جَمِيعًا ۚ أَفَأَنتَ تُكْرِهُ ٱلنَّاسَ

حَتَّىٰ يَكُونُوا۟ مُؤْمِنِينَ يونس ٩٩

"ጌታህም ቢሻ ኖሮ በምድር ያሉት ሰዎች ሁሉም የተሰበሰቡ ሆነው ባመኑ ነበር ፤ ታዲያ አንተ ሰዎችን አማኞች እንዲሆኑ ታስገድዳለህን ?" (ም ፲ ቁጥር፡ ፺፱)

وَلَوْ شِئْنَا لَآتَيْنَا كُلَّ نَفْسٍ هُدَىٰهَا وَلَـٰكِنْ حَقَّ ٱلْقَوْلُ

مِنِّى لَأَمْلَأَنَّ جَهَنَّمَ مِنَ ٱلْجِنَّةِ وَٱلنَّاسِ أَجْمَعِينَ السجدة ١٣

በሻንም ኖሮ ነፍስን ሁሉ ቅንነቷን (እምነቷን) በሰጠናት ነበር ፤ ግን ገሀነምንም ከአጋንንትና ከሰዎች የተሰበሰቡ ሆነው በእርግጥ እሞላለሁ ማለት ፣ ቃሉ ከኔ ተረጋግጦዋል ።" (ም ፴፪ ቁጥር ፲፫)

## 5.5.4. "እስላምን" ለመቀበል መርጠን ወስነናልን ?

ከላይ እንደተመለከተው እያንዳንዱ ሰው "እስላምን" ምን እንደሆነ ጠንቅቆ በማወቅ በአእምሮው አማካኝነት ዕውነትነቱንና ትክክለኛነቱን አምኖ ለመቀበል ፣ ወይም ላለመቀበል ሙሉ መብትና ሥልጣን ያለውና ምርጫም የተሰጠው ስለሆነ ሙስሊም ነኝ የሚል ሰው ሁሉ ሃይማኖቱን ጠንቅቆ በማወቅ ለሚያዘው ለመታዘዝ ፣ ለሚከለክለው ለመከልከል ወስና ቃል ኪዳን በመግባት ሙስሊም ስለሚሆን ቢቃል ኪዳኑ የመጽናት ግዴታ ይኖርበታል ። ታዲያ "ሙስሊም" የሆንክ አንባቢ ሆይ ! እስላምን በዕውነት ታውቃለህን ? የሚያዘውን ትታዘዛለህን ? ከሚከለክለውስ ትከለከላለህን ?

ለነዚህ ጥያቄዎች በምትሰጠው መልስ አንጻር የማስተካከል ግዴታ ይኖርብሃል ። አላህ ክብሩ ይስፋና "እስላምን" የሰው ልጅ አምኖ ለመቀበል ቃል ኪዳን እስከገባ ድረስ ቃል ኪዳኑን እንዲያከብር ሲያሳስበው እንዲህ ይላል ።

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ أَوْفُوا۟ بِٱلْعُقُودِ ۚ المائدة ١

"እላንተ ያመናችሁ ሆይ ! በቃል ኪዳናችሁ ሙሉ ፣" (ም ፭ ቁጥር ፩) በራሳችን ምርጫ ለአላህ የገባነውን ቃል ኪዳን ባለመሙላት በመጭው ዓለም ስንጠየቅ እንዳናፍር ዘወትር መጠንቀቅ ይኖርብናል ።

ከዚህ ቀጥሎ የእስላም ዲን ያለ ግዴታ እንዴት ሊስፋፋ እንደቻለ በአጭሩ ለማየት እንሞክራለን ።[6]

---

[6] ትምህርቱ "NO COMPULSION IN RELIGION" ከተሰኘው ከአሊ ዛሒ ረመዳን ጽሑፍ በትርጉም የተወሰደ ነው ።

ምዕራፍ፡ ፮

## በዲን (በሃይማኖት) ማስገደድ የለም !

እስላም ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ጥሪው በማስገደድ ላይ አልተመሠረተም ፤ ጠላቶቹ እንደሚያስተጋቡት በሰይፍ አማካኝነት አልተስፋፋም ። እስላምየተስፋፋው ነፃ በሆነ መልኩ የሰውን ልጅ ወደ ቀናው መንገድ በመምራቱ ነው ። የዕምነቱ ጠላቶች ዕውነቱን ለማወቅ ቢሹ ኖሮ ፣ ወይም ትክክለኛውን ነገር ለማግኘት ቢመራመሩ ኖሮ የምንለው ነገር ዕውነት መሆኑን ባወቁ ነበር ። ይኸውም እስላም የተስፋፋው በኀይል በመጠቀም ሳይሆን ጉዳት ከሚያስከትል ዘዴና መንገድ ውጭ በነፃ ጥሪ ላይ ተመሥርቶ ነው።

ነቢያችን (ሰ.አ.ዓ.ወ) እንዲሁም በመጀመሪያ እምነቱን የተቀበሉት (ሰሃቦች)[1] በሙሉ በቁሬሽ ካፊሮች ቁጣ ከፍተኛ ሲቃይ ደርሶባቸዋል ። ነቢዩ ከሰሃቦች ለከፊሉ ከነቤተሰቦቻቸው ወደ ኢትዮጵያ እንዲሰደዱ ፈቀዱላቸው ። ይህንንም ያደረጉት ኩቁሬሾች[2] ፍትሕ የጎደለው ጥቃት በሕይወታቸው ለማምለጥ እንዲችሉ ነው ። ሆኖም ሙሽሪኮች (ለአላህ አጋር የሚያደርጉት) ሰሃቦችን እንዲያባርሯቸውና እንዲይዙዋቸው ፣ ኢትዮጵያም ከደረሱ በኋላ ንጉሡ ዘንድ በመቅረብ እንዲመለሱ በማድረግ በአዲስ መልክ ሊያሰቃዩዋቸውና ፣ ከአባትና ከአያታቸው የመጣላቸውን ጣኦት የማምለክ እምነት ስለተው ሊበቀሉዋቸው ከሄዱበት የሚመልሱዋቸው ሰዎች ላኩባቸው ።

ይህንን ግልጽ የሆነና ፣ የእስላም ጥሪ ታሪክ በግልጽ የሚያሠፍረው ተጨባጭ ዕውነታን እንዴት ይዘነጋሉ ? የእስላም ታሪክ ነቢያችንና ሰሃቦች የቱን ያህል በቁሬሾች እጅ እንደተሰቃዩና ኑሮዋቸውን የምድር ላይ ገሃነም ያደረጉባቸው መሆኑን አላሳያቸውምን ? ነቢዩ በመስገድ ላይ እያሉ እላያቸው ላይ ይጥሉባቸው የነበረውን ቁሻሻ ረሱትን ? ቢላልንና የያሲር ቤተሰቦችን በበረሃ ፀሐይ ቃጠሎ ዕርቃናቸውን አሸዋው ላይ በማስተኛት ደረታቸው ላይ ቋጥኝ ድንጋይ በመጫን ያሰቃዩዋቸው የነበረውን ረስተውታልን ? ይህም ሆኖ የያሲር ቤተሰብ "ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም" ማለትን አላቋረጡም ። በፈቃዳቸው ከተቀበሉት ሃይማኖት ሊቋቋሙት የማይችሉት ስቃይና መከራ ፣ ረሃብና የውኃ ጥም ቢያደርሱባቸውም አልተመለሱም ። በዚህ ዓይነት ስቃይ ላይ የያሲር ቤተረሰብ እያለ የተመለከቱት ነቢይ "የያሲር ቤተሰብ ጥናቱን ይስጣችሁ ፣ በርቱ ፣ የእናንተ ቀጠር (ቦታ) ገነት ነው !" ብለው ከማጽናናት በቀር ምንም ለማድረግ አልቻሉም ።

ለምንድነው ይህን መሰል ኢሰብአዊ የሆነ ስቃይ ያደረሱባቸው ? ምክንያቱ ነቢዩ ከአላህ ዘንድ ያመጡት ዲን ትክክለኛ የማህበራዊ ኑሮን የሚመሠርት ፣ የሕብረተሰቡን የአኗኗር ዘይቤ በማረም ከእምነት የለሽነት ጨለማ ወደ ብሩህና ግልጽ የሆነ እምነት የሚያሸጋግር በመሆኑ ነው ። ዲኑ የአላህን አንድ መሆን በይፋ ገለጸ ፤ ጣኦታቸውን አወገዘ ፤ በሕዝቦች መሐል ነፃነት እኩልነትና ፍትሕ እንዲሠፍን አስተማረ ፤ በማዕረግና በጎሣ ላይ ተመርኩዞ መኩራ

1 ሰሃባ ማለት ነቢዩን አይቶ ያመነ ነው ።
2 ቁሬሾች በመካ ይኖሩ የነበሩ የዓረብ ጐሣ ናቸው ።

ራትን አስቀረ ፣ ሀብታም ከድሃ ፣ አረብ የሆነው አረብ ካልሆነው አላህን በመ
ፍራት ካልሆነ በቀር ብልጫ የማይኖረው መሆኑን አስተማረ ። ቁርአን በግልጽ
ያሠፈረውን አንቀጽ እንጠቅሳለን ፡

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِنَّا خَلَقْنَٰكُم مِّن ذَكَرٍ وَأُنثَىٰ وَجَعَلْنَٰكُمْ شُعُوبًا وَقَبَآئِلَ لِتَعَارَفُوٓا۟ ۚ
إِنَّ أَكْرَمَكُمْ عِندَ ٱللَّهِ أَتْقَىٰكُمْ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٌ     الحجرات ١٣

“እላንተ ሰዎች ሆይ ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ ፤ እንድትተዋወቁም
ጎሣዎችና ነገዶች አደረግናችሁ ፤ አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያ
ችሁ ነው ።” (ም ፵፱ ቁጥር ፲፫)

ለዚህም ነው ሥልጣናቸውን የገፈፋቸውን ፣ ማዕረጋቸውን ዝቅ ያደረገውንና
ጣኦታቸውን የነቀፈውን ዲን ለመቀበል ቁሬሾች እምቢተኛ የሆኑት ። በነ
ቢዩና በሰሃቦች ላይ ጥቃት ያደረሱትም በአጥቂነት ላይ ተመርኩዘው በበደል
ያገኙትና ሲዝናኑበት የኖሩትን የበላይነት ለማቆየት ነው ። ስቃዩ እየበረታ
ሲሄድ ፣ ነቢዩ ወደ የስሪብ (መዲና) እንዲሄዱ ከአላህ በመፈቀዱ ተሰደዱ ።
አላህም በሚሰደዱበት ዕለት ቁሬሾች ተንኮልና ሴሊት ሊሠይፉዋቸው ከጠነ
ሰሱት አድማ አዳናቸው ።

በስደቱ ጉዞ አብረዋቸው ከነበሩት ከአቡበከር አስዲቅ ጋር ሆነው መዲና
ደረሱ ። ቀድመዋቸው በተሰደዱት ሰሃባትና በአንሳሮች (ለሙስሊሞች ረዳት
የሆኑት የመዲና ነዋሪ ሙስሊሞች) አቀባበል ተደረገላቸው ። እስላም በመ
ዲና ነዋሪዎች ተቀባይነት አግኝቶ ተጠናክሮ አድጎ ሲሄድ የቁሬሽ ካፊሮች
ስደተኞቹን በሰላም እንዲኖሩ አድርገዋል ወይ ? በፍጹም ! ቁጥራቸው በርከት
ያሉ ወገኖቻቸውን ከመሣሪያ ጋር በማሠለፍ ተከታተሉዋቸው ፤ ተዋጉዋቸ
ውም ፣ በጠላትነታቸውም ቀጠሉበት ። ካፊሮች በርካታ ጦርነቶችን በበድር ፣
በኡሁድ ፡ በኸንደቅና በሌሎችም ሥፍራዎች ከፈቱባቸው ፣ ሙስሊሞች ግን
ለዕምነታቸው ከመከላከል በቀር ዲኑ ተቀባይነት እንዲኖረው አላስገደዱም ።
በመጨረሻም ድሉ የሙስሊሞች ሆኖ በበደል ከተባረሩበት የመካ ከተማ በድል
አድራጊነት ለመግባት በቁ ።

ሆኖም ሙስሊሞች በድል አድራጊነት መካ ቢገቡም ዲኑ በዚያን ጊዜም ቢሆን
አደገኛ ሁኔታ ላይ ነበር ። ዓለምን ለመግዛት ይፎካከሩ የነበሩ ሁለት ታላላቅ
ሀገሮች ነበሩ ። እነርሱም የክርስቲያኑ የሮማ መንግሥትና የማጊዩን የፐርሺያ
መንግሥት ነበሩ ። በአረቢያ ፔኒንሱላ (ልሳነ ምድር) እየተስፋፋ የመጣው ሃይ
ማኖት በአካባቢው የነበራቸውን ተሰሚነትና ክብር ስጋት ላይ ስለጣለው
ፈሩ ። ስለዚህም አዲሱን እምነት በእንጭጩ ለመቅጨት ወሰኑ ። በእንጻሩም
ሙስሊሞች ወደ መዲና ከተሰደዱ ጊዜ ጀምሮ በአይሁዶች ይደርስባቸው የነ
በረው መፈታተንና ውጊያ እንደቀጠለ ነበር ።

## 6.1. አይሁዶች ለሙስሊሞች የነበራቸው አመለካከት ፤

አይሁዶች ከሮማዊያን ጭቆና ሸሽተው በማምለጥ በአረቢያ ፔኒንሱላ (ልሳነ
ምድር) ጥገኝነት ጠይቀው ለረዥም ጊዜ ይኖሩ ነበር ። ከአረብ ነዋሪዎችም ጋር
በሰላም ኖረዋል ። ነቢያችን ሙሐመድ (ሰ.አ.ዓ.ወ) ስሃቦች ጓደቻቸው በቁሬሽ

"(ካፊሮች) ቢችሉ ከሃይማኖታችሁ እስከሚመልሱዋችሁ ድረስ የሚዋጉዋ ችሁ ከመሆን አይቦዝኑም ።" (ም ፪ ቁጥር ፪፻፲፯)

በእስላም ላይ ይህ አመለካከት ሊኖራቸው የቻለበት አያሌ ምክንያቶች ሲኖሩ ዋናው እስላም ስለ አላህ አንድነት ማስተማሩ ነው ።

እስላም በሕዝቦች መሐል ልዩነትን ሲያስቀር እንዲህ ይላል ፤

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِنَّا خَلَقْنَٰكُم مِّن ذَكَرٍ وَأُنثَىٰ وَجَعَلْنَٰكُمْ شُعُوبًا وَقَبَآئِلَ لِتَعَارَفُوٓا۟ ۚ
إِنَّ أَكْرَمَكُمْ عِندَ ٱللَّهِ أَتْقَىٰكُمْ ۚ الحجرات ١٣

"እላንተ ሰዎች ሆይ ፣ እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ ፤ እንድትተዋወቁም ጎሣዎችና ነገዶች አደረግናችሁ ፤ አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው ።" (ም ፵፱ ቁጥር ፲፫)

እስላም በፍትሕና በበጎ ሥነ ምግባር ያዛል ፤ ፀያፍ የሆኑ ተግባሮችን ፣ በደልና አመፀኝነትን ይከለክላል ።

፩/ ባይዛንታይኖች በአማን የነበረ ገዢያቸው ፣ ፋርዋህ ቢኒ ኡመር አል ዛኒ የተባለውን በሒጅራ ስድስተኛ ዓመት ሙስሊም ስለሆነ ሰቀሉት ፤

፪/ በሒጅራ ስምንተኛው ዓመት ነቢዩ (ሰ. አ. ዓ. ወ) የትራንስ ጆርዳን ሕዝቦችን ወደ እስላም በሠላም እንዲጠሩ አሥራ አምስት ሰዎችን ላኩ ። የጆርዳን ሕዝቦች አንድ ሰው በቀር የቀሩትን ሁሉ ገደሉዋቸው ፤

፫/ በዚያን ዓመት ለአልሃሪስ ቢኒ ሸሃር አልከሃዛኒ ነቢዩ (ሰ.አ.ዓ.ወ) እስላ ምን እንዲቀበል መልእክት ሲልኩበት የማስፈራራት መልስ ላከባቸው ፤

፬/ ነቢያችን (ሰ አ ዓ ወ) አልሃሪስ ቢኒ ኡመት አልዛዲ የተባሉት ለሄርኩ ለስ የእስላምን ጥሪ እንዲያደርሱለት ላኩዋቸው ፤ ሸራህቢል ተነስቶ አረዳቸው ፤

፭/ በሒጅራ ዘጠነኛ ዓመት ሄርኩለስ የአረቦችን ሀገር ለመውረር ሠራዊ ቱን አዘመተ ። ሙስሊሞችም ተቡክ ላይ ተሰባሰቡ ። ሆኖም ሮማዊያን የሶሪያን ድንበር አቋርጠው በመጥፋታቸውና ሙስሊሞችም የሶሪያን ድንበር ጥሰው ለመግባት ባለመፈለጋቸው ምንም ዓይነት ውጊያ አልተ ካሄደም ።

ከላይ እንደተመለከተው ሙስሊሞች በጠላቶቻቸው ላይ ውጊያ የከፈቱበት ጊዜ አልነበረም ፤ በአንጻሩ ግን ጠላቶቻቸው ውጊያ ይከፍቱባቸው እንደነበርና ሙስሊሞች ራሳቸውን ይከላከሉ እንደነበረ ፣ የአካባቢውንና ራቅ ባለ ቦታ ያሉትንም ሕዝቦች ወደ እስላም ለመጥራት ደብዳቤ ወይም መልእክተኞችን ይልኩ እንደነበርና በመልእክተኞቹ ላይ ይደርስ የነበረው ግፍ ለማየት ይቻ ላል ።

## 6.3. ፐርሺያኖች ለእስላም የነበራቸው አመለካከት ፤

ነቢዩ (ሰ. አ. ዓ. ወ) ለቸሥሮ የእስላምን ጥሪ ሲልኩለት ፐርሺያኖች (የፋርስ ሕዝቦች) የፈጸሙት ከሌሎቹ የተለየ አይደለም ። ቸሥር የነቢዩን (ሰ.አ.ዓ.ወ)

ደብዳቤ ቀዶ በመጣል እርሱን የሚከተሉትን ዓረቦች በአዋሳኞቻቸው በሚገኙት ሙስሊሞች ላይ ወረራ እንዲፈጽሙ አነሳሳቸው ። ዳሩ ግን ኻሊድ ቢኒ ልወሊድ ገቱዋቸው ። ያዝዳገር የተባለው የፐርሺያ ንጉሥም ጉዳዩ ከንክናት ሙስሊሞችን ለማስወገድ (ለማጥፋት) ወታደሮች ቢልክም አልተሳካለትም ።

የፐርሺያኖች የማጥቃት ዘመቻ አላህ (ሱ.ወ.) ድሉን ለሙስሊሞች ሰጥቶ ፐርሺያ እስከገቡ ድረስ ቀጥሉ ነበር ። ሙስሊሞች ከፐርሺያ ነዋሪዎች እስላምን እንዲቀበሉ አንዳቸውንም አላስገደዱም ። ለስላም በእነዚህ ትግሎች ውስጥ ራሱን ከመከላከል ሌላ ምን ሚና ነበረው ?

## 6.4. እስላም ስለካፊሮች ያለው አመለካከት ፤

የእስላም ጠላቶች እስላም ስለ ከሐዲዎች (አፈንጋጮች) ባለው አመለካከት ላይ ይበልጥ ያተኩራሉ ። ከዚህም በመነሳት እስላም ሰዎችን በሰይፍ በማስፈራራት እንዲቀበሉት አስገደደ በሚል የተሳሳተ አመለካከት እስላምን ተወቃሽ ለማድረግ ፈለጉ ።

ታሪኩን ከመነሻው ጀምር መጥቀስ ያስፈልጋል ። የካፊሮች ንቅናቄእንጣስና በሙስሊሞችና በከሐዲዎች መሐል የተከፈተውን ጦርነት እንዲጀመር ያደረጉትን ሁኔታዎች መግለጽ ያስፈልጋል ።

በነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.አ.ዓ.ወ) ሞት ምክንያት ከተከሰተው ከፍተኛ ድንጋጤ በኋላ አቡበከርሲዲቅ (ረዲያ አላሁዓንሁ) ተነስተው የአላህን ቃል ደጋግመው ማሰማት ጀመሩ ፤

وَمَا مُحَمَّدٌ إِلَّا رَسُولٌ قَدْ خَلَتْ مِن قَبْلِهِ ٱلرُّسُلُ أَفَإِيْن مَّاتَ أَوْ قُتِلَ

ٱنقَلَبْتُمْ عَلَىٰٓ أَعْقَٰبِكُمْ   آل عمران ١٤٤

"ሙሐመድ እኮ ከነቢይ በቀር ሌላ አልነበረም ፤ ብዙዎች ነቢያት ከርሱ በፊት አልፈዋል ፤ ቢሞት ወይም ቢገደል ጀርባችሁን አዙራችሁ ትፈረጥጣላችሁን ?" -ም ፫ ቁጥር ፩፻፵፬)

ከዚህ የቁርአን አንቀጽ መድገም በኋላ በጣም ከፍ ባለ ድምፅ ሲገልጹ ፣ "ሙሐመድን ያመልኩ ለነበሩት ሙሐመድ አርፈዋል ፤ አላህን ለሚያመልኩ ግን አላህ ሕያው ነው ፣ አይሞትም ።" በማለት አስታወሱ ። በዚህ መልኩ ተገቢው ቅስቀሳ ከተደረገ በኋላ የሕዝቡ መንፈስ ሠላምን (እርጋታን) አገኘ ። ሆኖም አንዳንድ ሰዎች ከድንጋጤው በኋላ የማስተዋል ሕሊናቸው አልተመለሰላቸውም ። ለሁለትም ወገን ተከፈሉ ።

አንደኛው ወገን ከመስመር በመውጣት ከነቢዩ ሙሐመድ መሞት ጋር ተልዕኮው ያከተመ መስሉት በዛካት መልክ ይከፈል የነበረውን ምጽዋት ለማቋረጥ ፈለገ ። ሙሐመድ (ሰ.አ.ዓ.ወ) ከሞቱ ዛካቱን ለመሰብሰብ ማንም ሰው ስለማይተካቸው ዘካት መከፈል አይኖርም የሚል አቋም ወሰዱ ። አቡበከር (ረ.ዓ.) እነዚህን አፈንጋጮች ለመመለስ መልእክት ላኩባቸው ። ከፊሎቻቸው እንደ እነአብስ ፣ ቶብያን ፣ በኒ አሳድ ፣ እና ከናናህ ያሉት ዘካቱን ላለመከፈል ወስነው አቡበከርን (ረ.ዓ.) ለመዋጋት ተነሱ ። አቡበከርም (ረ.ዓ.)

እነሱን ለመዋጋት መሐላ ፈጸሙ ። አፈንጋጮቹም በምሽት ወደ መዲና ዘመቱ ፤ ግን ሙስሊሞች ሠበሩዋቸው ። ዕውነቱን ለማወቅ ለሚሻ አቡበከር (ረ.ዓ.) ይህንን ጦርነት (ውጊያ) እንዲያደርጉ ተገደው እንጂ አልቀሰቀሱም ።

ያንድ ሀገር መሪ ከተከታዮቹ አንዱ ወገን ተቃውሞት ቢነሳና የተገነባውንም ቤት በማፍረስ በምትኩ ከእስላም በፊት የነበረውን ዓይነት ፍትሕ የለሽ ጨለማ ሥርዓት መልሶ ለማቋቋም ቢሞክር ምን ያደርጻል ? የሀገሩን አንድነት ለማስከበርና አመፀኞቹን በመመለስ እስላምና ሙስሊሞችን ለመጠበቅ ጦር ከማንሳት በቀር አቡበከር (ረ.ዓ.) የተሻለ አማራጭ አልነበራቸውም ። የቀረው ሌላው አማራጭ በከሃዲዎች እጅ ሙስሊሞች እስኪደመሰሱ መጠበቅ ብቻ ነበር ።

አቡበከር (ረ.ዓ.) በከሃዲነታቸው የፀኑትን እስከ መግደል መብትና ሥልጣን ነበራቸው ። ይሄውም እስላምን ከተቀበሉ በኋላ በመካድ ትክክለኛውን ፈር ስለለቀቁ ብቻ ሳይሆን ፣ በሙስሊሞቹ በሙሉ ተቀባይነት ባገኘው መንግሥትና ሕግ ላይ በማመጻቸውም ጭምር ነው ።

## ሙስሊሞች መቼ ነው የሚዋጉት ?

ሰዎች እስላምን በሚገባ በመረዳት የሠላም ሃይማኖት መሆኑን ፣ በሰዎች ላይ ያልተጫነና ያለ ፍላጎታቸው እንዲቀበሉትም ያልተገደዱ መሆኑን እንዲያውቁት ለዚህ ጥያቄ መልሱን ለ"እስላም" ዲን መሠረት (ምንጭ) ከሆነው ቁርዓን መጥቀሱ ይረዳል ። አላህ እንዲህ ይላል ፤

قُلْ يَـٰٓأَيُّهَا ٱلْكَـٰفِرُونَ ﴿١﴾ لَآ أَعْبُدُ مَا تَعْبُدُونَ ﴿٢﴾
وَلَآ أَنتُمْ عَـٰبِدُونَ مَآ أَعْبُدُ ﴿٣﴾ وَلَآ أَنَا۠ عَابِدٌ مَّا عَبَدتُّمْ ﴿٤﴾
وَلَآ أَنتُمْ عَـٰبِدُونَ مَآ أَعْبُدُ ﴿٥﴾ لَكُمْ دِينُكُمْ وَلِىَ دِينِ ﴿٦﴾

الكافرون ١-٦

"በላቸው ፤ እላንተ ከሐዲዎች ሆይ ፣ ያንን የምትገዙትን (ጣኦት አሁን) አልገዛም ። እናንተም እኔ የምገዛውን (አምላክ አሁን) ተገገርዎች አይደላችሁም ፣ እኔም ያንን የተገዛችሁትን (ወደፊት) ተገገር አይደለሁም ፣ ለናንተ ሃይማኖታችሁ አላችሁ ፤ ለኔም ሃይማኖቴ አለኝ ።" (ም ፩፻፱ ቁጥር ፩-፮)

እኛ ሙስሊሞች በአላህ (ሱ ወ) አንድ መሆን እናምናለን ፤ እነርሱ (ከሐዲዎች) ግን ይህን ይክዳሉ ። ይህ ሃይማኖታቸን ነው ፤ ያ ደግሞ የእነርሱ እምነት ነው ። እያንዳንዳችን የተስማማንን እምነት የመከተል ነፃነት አለን ። አላህ (ሱ.ወ.) በካፊሮች የተሳሳተ እምነት አይጎዳም ፤ አላህ (ሱ.ወ.) ቢፈልግ ኖሮ በምድር ያሉት ሕዝቦች በሙሉ በእርሱ ባመኑ ነበር ።

ሙስሊሞች ጥቃት ካልደረሰባቸው በቀር እንዳይዋጉ ታዘዋል ። ይህ የግለሰቦች ሃሳብ ሳይሆን በአላህ (ሱ ወ) የተጠሰ ትእዛዝ ነው ። አላህ እንዲህ ይላል ፤

أُذِنَ لِلَّذِينَ يُقَـٰتَلُونَ بِأَنَّهُمْ ظُلِمُوا۟ ۚ وَإِنَّ ٱللَّهَ عَلَىٰ نَصْرِهِمْ لَقَدِيرٌ ﴿٣٩﴾
ٱلَّذِينَ أُخْرِجُوا۟ مِن دِيَـٰرِهِم بِغَيْرِ حَقٍّ إِلَّآ أَن يَقُولُوا۟ رَبُّنَا ٱللَّهُ الحج ٣٩-٤٠

"ለነዚያ ለሚገደሉት (ምዕመናን) እነርሱ የተበደሉ በመሆናቸው (መጋደል) ተፈቀደላቸው ፤ አላህም እነርሱን በመርዳት ላይ በእርግጥ ቻይ ነው ። ለነዚያ ጌታችን አላህ ነው ከማለታቸው በስተቀር ያለ አግባብ ከአገራቸው የተባረሩ ለሆኑት ፣ (ተፈቀደ) ፤" (ም ፳፪ ቁጥር ፴፱-፵)

አላህ (ሱ ወ) ሁሉን ዓዋቂና የሁሉም ነገር ግንዛቤ ያለው ጌታ ካፊሮች ሙስሊሞችን ከእምነታቸው ለመመለስ የቻሉትን ሁሉ ያደርጋሉ ብሎ ማለቱን ቀደም ሲል የተመለከትን ሲሆን ይበልጥ ለመረዳት እንዲያስችል እንደገ መጥለን ፤

وَلَا يَزَالُونَ يُقَٰتِلُونَكُمْ حَتَّىٰ يَرُدُّوكُمْ عَن دِينِكُمْ إِنِ ٱسْتَطَٰعُوا۟ ۚ

البقرة ٢١٧

"- - -(ከካፊሮች) ቢችሉ ከሃይማኖታችሁ እስኪመልሱዋችሁ ድረስ የሚዋጉዋችሁ ከመሆን አይቦዝኑም - - -" (ም ፪ ቁጥር ፪፻፲፯)
ቀጥሉም በሌላ አንቀጽ አላህ (ሱ ወ) እንዲህ ይላል ፤

وَقَٰتِلُوا۟ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ ٱلَّذِينَ يُقَٰتِلُونَكُمْ وَلَا تَعْتَدُوٓا۟ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ

لَا يُحِبُّ ٱلْمُعْتَدِينَ البقرة ١٩٠

"እነዚያን የሚጋደሉዋችሁን (ከሐዲዎች) ፣ በአላህ መንገድ ተጋደሉ ፤ ወሰን ንንም አትለፉ ፤ አላህ ወሰን አላፊዎችን አይወድምና ።" (ም ፪ ቁ ፩፻፺)
ከእነዚህ የቁእርአን አንቀጾች በእስላም ማስገደድም ሆነ ማጥቃት ተከልክሉ የነበረ መሆኑንና ሙስሊሞች ሊጋደሉ የተፈቀደላቸው የሚጎነትሉዋቸውና በውጊያ የሚያጠቁዋቸውን መሆኑን እንገነዘባለን ። ለእስላሞች ተጋድሉ የተፈቀደው ራሳቸውን እንዲከላከሉ ብቻ መሆኑንና ወሰን አልፈው ሌላውን እንዳይበድሉ መታዘዛቸውንም ጭምር እንረዳለን ።

ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ምዕራፎች አምስቱን የእስላም መሠረታዊ ሕጎች ለማቅረብ ይሞከራል ።

## <u>አምስቱ መሠረታዊ የእስላም ሕጎች</u>

ምዕራፍ ፩ ሥር ስለ እስላም ምንነት ገለጻ በተደረገበት ትምህርት ውስጥ አምስቱ መሠረታዊ የእስላም ሕጎች ጠቅለል ባለ መልክ ተገልጸው መጠነኛ ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል ።

አምስቱ መሠረታዊ የእስላም ሕጎች ፤

፩/ የአላህን አንድ መሆን ከልብ አምኖ በቃልም መመስከርና ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን መመስከር ፤

፪/ ሠላትን ሥርዓቱን ጠብቆ በወቅቱ መስገድ ፤

፫/ ዘካትን ሥርዓቱን ጠብቆ በትክክል ማውጣት (መስጠት) ፤

፬/ ጾምን ሥርዓቱን ጠብቆ በአግባቡ መጾም ፤

፭/ ችሎታ ያለው ሰው ሥርዓቱን ጠብቆ ሐጅ ማድረግ ናቸው ።

የመጀመሪያውን መሠረታዊ ሕግ በሚመለከት ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁ ትና ሶስት ሥር ሠፊና አጠቃላይ ማብራሪያ የተሰጠበት ቢሆንም ለማጠቃ ልና እንባቢም በአጭሩ አስተሳሰቡን ለመጨበጥ እንዲችል ቀጥሎ በአጭ ለማስፈር እንሞክራለን ።

## ምዕራፍ ፯

### 7.1. የአላህን አንድነትና የሙሐመድን መልዕክተኛነት መመስከር ፤

በሙሐመድ አማካኝነት የመጣው የእስላም ዲን ከርሱ በፊት የመካና የአካባቢው ዓረቦች እንዲሁም በዘመኑ የነበሩት ዓረብ ያልሆኑትም ሕዝቦች ከአላህ በቀር በተጨማሪ የተለያዩ አማልክትን የማምለካቸው ልምድ ትክክለኛ አለመሆኑን በይፋ አሳውቆ የአላህን አንድ ብቻ መሆን አረጋገጠ ። ቁርአንም ይህን ዕውነታ ሲያስተምር እንዲህ ይላል ፤

وَإِلَٰهُكُمْ إِلَٰهٌ وَاحِدٌ لَّا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ الرَّحْمَٰنُ الرَّحِيمُ

البقرة ١٦٣

"አምላካችሁም አንድ አምላክ ብቻ ነው ፤ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም ፤ (እርሱ) እጅግ በጣም ርህሩህ አዛኝ ነው ።" (ም ፪ ቁ ፩፻፷፫)

እንግዲህ የአላህን አንድ መሆን መመስከር ግንባር ቀደሙ መሠረታዊ የእስላም ሕግ ስለሆነ ሙስሊም ነኝ የሚል ማንኛውም ሰው በልቡ ሊያምንበት ይገባል ። በቃሉም (በአንደበቱም) ይህንኑ ማረጋገጥ ይኖርበታል ። የምስክርነት ቃሉም ፤ أشهد أن لا إله إلا الله የሚል ነው ። ይህ የምስክርነት ቃል "ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩን እመሰክራለሁ ። " ብሎ ማረጋገጥን የሚመለከት ነው ። ይህ ቃል መስካሪው ሰው ለእርሱ ፈቃድ ተገዥ በመሆን ዒባዳ ሊደረግ የሚገባው ከአንድ አላህ በቀር ሌላ አለመኖሩን በልቡ አምኖ በቃሉ ከመሰከረ በኋላ ለአላህ ፈቃድ ራሱን ለማስገዛት ያዘዘውን ለመፈጸም የከለከለውን ለመከልከል በቁርጠኝነት ራሱን ማሠለፉን በይፋ የሚገልጽበት (ከሊማህ) ቃል ነው ።

የአላህን አንድ መሆን መመስከር ማለት ሠፊ ይዘት ያለው ሲሆን በአጭሩ ከእርሱ ሌላ የሚመለክ ፣ ከእርሱ ሌላ ኃያል ሆኖ የሚያድን ፣ የሚገድል ፤ የዕለት ጉርስን የሚሰጥ (የሚረዝቅ) ፣ የሚረዳ (ናፌዕ) ፣ የሌለ መሆኑን አምኖ መቀበል ማለትን የሚያጠቃልል ስለሆነ በዚህ የፀና እምነት ያለው ሰው ሙሉ የነፃነትና በራስ የመተማመን ስሜት በሰውነቱ ውስጥ ይሠርጻል ። ለማንም ተገዥ የመሆንና የጥገኝነት ስሜት ከርሱ ጨርሶ ይጠፋል ። በራሱና ፈጣሪ ጌታው በሆነው አላህ ለመተማመን ስሜቱ ይዳብራል ።

ከላይ እንደተገለጸው ስለ አላህ ባሕርይ ﴿صفات﴾ ጠንቅቆ በማወቅ ፣ የአላህን አንድ መሆን አምኖ ምስክርነቱን የሚሰጥ ሙስሊም አመለካከቱ ፍጹም ይለወጣል ። በቁርአን የወረዱት ማሳሰቢያዎች ከዚህ በታች የምንጠቅሳቸውና ሌሎችም አንቀጾች እምነቱን በማጠንከር ቀራጥና በዲኑ ፅኑ ያደርጉታል ፤

ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን አምና መመስከር የምስክርነት ቃሉ ሙሐመድን ከአላህ ዘንድ ቁርአንን ያመጡ መልዕክተኛ መሆናቸውን ፣ ቁርአን የአላህ መልዕክት መሆኑን አምና መቀበልን ፣ ባዘዘው መታዘዝን ፣ በከለከለው መከልከልን የሚያጠቃልል ነው ። በተጨማሪም የምስክርነቱ ቃል ከቁርአን ሌላ ሙሐመድ ላዘዙት ሁሉ መታዘዝን ፣ ለከለከሉት ሁሉ መከልከልን ቁርአን ራሱ ስለሚያዝ ይህንንም አምና ተግባራዊ ማድረግን ያጠቃልላል ።

አላህ ክብሩ ይስፋና ስለዚሁ ሲናገር እንዲህ ይላል ፤

وَمَآ ءَاتَىٰكُمُ ٱلرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَىٰكُمْ عَنْهُ فَٱنتَهُوا۟ الحشر ٧

"መልዕክተኛውም የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት ። ከርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ ፤ - - -" (ም ፶፱ ቁ ፯)

ሙሐመድ የሚናገሩት ሁሉ በከንቱ አለመሆኑንና ከአላህ በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት መሆኑንም በማረጋገጥ ልንከተላቸው የሚገባ መሆኑን አላህ ሲገልጽ እንዲህ ይላል ፤

وَمَا يَنطِقُ عَنِ ٱلْهَوَىٰٓ ۝٣ إِنْ هُوَ إِلَّا وَحْىٌ يُوحَىٰ النجم ٣-٤

"ከልብ ወለድም አይናገርም ። እርሱ (ንግግሩ) የሚወርድ ራዕይ እንጂ ሌላ አይደለም ።" ( ም ፶፫ ቁ ፫-፬)

ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ የመጨረሻውም መልዕክተኛ ስለመሆናቸውም አላህ ራሱ ሲመሰክርላቸው እንዲህ ይላል ፤

مَّا كَانَ مُحَمَّدٌ أَبَآ أَحَدٍ مِّن رِّجَالِكُمْ وَلَٰكِن رَّسُولَ ٱللَّهِ وَخَاتَمَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ

الأحزاب ٤٠

"ሙሐመድ ከወንዶቻችሁ የማንም ሰው አባት አይደለም ፣ ግን የአላህ መልዕክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው ።" (ም ፴፫ ቁ ፵)

ከላይ እንደተገለጸው የአላህን አንድ መሆን አምና የተቀበለና የመሰከረ ፣ ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውንም አምና የተቀበለ ፤ ራሱን ለአላህ ፈቃድ ለማስገዛት የወሰነ መሆኑ ስለሚታወቅ "ሙስሊም" የሚል መጠሪያ ይሰጠዋል ።

ለአላህ ፈቃድ ራሱን ለማስገዛት የወሰነ ሰው የአላህን ፈቃድ ምን እንደሆነ የማወቅ ግዴታ ስለሚኖርበት የአላህ ፈቃድ የተገለጸበትን መጽሐፍ ፣ ቁርአንን አንብቦ ለመረዳት እንዲችል ማጥናት ግዴታው ይሆናል ። በተጨማሪም ቁርአንን ለሕዝብ እንዲያብራሩ በቁርአን በመታዘዛቸው ሙሐመድ ስለዲኑ ባጠቃላይ የሰጡትን ገለጻ "ሐዲስ"[1] ማጥናትና መመሪያነቱን ተቀብሎ መፈጸም ያስፈልጋል ።

[1] ነቢዩ ሙሐመድ የተናገሩት ፣ የሠሩትና ሌላው ሰው ሲሠራ ያጸደቁት ሐዲስ ይባላል ።

እዚህ ላይ ማስተዋል የሚገባን ቁም ነገር ቁርአንና ሐዲስን ጠንቅቆ የማወቅ ግዴታ የሙስሊሞች የጋራ ኃላፊነት ነው ። እያንዳንዱ ሰው ግን ሁሉንም ጠንቅቆ ሊያውቅ የማይችል በመሆኑ ከምዕመናን መሐል ከፊሉ ጠንቅቆ እስካወቃቸው ዓሊሞች (የዲን መምህራን) እስካሉ ድረስ የቀረው ሕዝብ መሠረታዊ የሆኑትን ሕጎች አውቆ እስከፈጸመና ለቀሩት የእስላም ሸሪዓዎች (ሕጎችና መመሪያዎች) ዓሊሞች በሚገልጹለት እስከተመራ ድረስ በቂ ይሆናል ።

ስለዚህ መሠረታዊ ስለሆኑት የእስላም ሕጎች አንባቢ ጠንቅቆ ለማወቅ እንዲችል ራሳቸውን በቻሉ ልዩ ልዩ ምዕራፎች ሥር ለማቅረብ እንሞክራለን ።

# ምዕራፍ ፰

## ሶላት[1]

አላህ ክብሩ ይስፋና ሰውን የፈጠረው እርሱን ዒባዳ እንዲያደርግ መሆኑን ሲገልጽ እንዲህ ይላል ፤

وَمَا خَلَقْتُ ٱلْجِنَّ وَٱلْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ الذاريات ٥٦

"ጋኔንና ሰውንም ሊገዙኝ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም ።" (ም ፶፩ ቁ ፶፮) የሰው ልጅ የተፈጠረው አላህን ዒባዳ ለማድረግ ከሆነ ሶላት ዋነኛው የዒባዳ ማድረጊያ ዘዴ ስለሆነ ሶላትን ጠንቅቆ ማወቅ ግዴታ ይሆናል ።

ስለዚህ በዚህ ምዕራፍ ሶላት ምን ማለት እንደሆነ ፣ ትርጉሙን ፣ ሶላት በእስላም ሃይማኖት ያለውን ቦታ ፣ ደረጃውን ፣ ሶላትን ግዴታ ለማድረግ ያስፈለገበት ምክንያት ፣ ሶላት ሊሰጠን የሚችለው ጥቅም ፣ ቀደም ባለ ጊዜ የመጡ የአላህ መልዕክተኞች በሕዝባቸው ላይ ሶላት ግዴታ የነበረ ስለመሆኑና ይዘቱ ፣ የሶላትን ዓይነቶች ከነዝርዝር ሁኔታቸውና የሶላትን ይዘት ለማየት እንሞክራለን ።

### 8.1. የሶላት ትርጉም ፤

የሙስሊሞችን "ሶላት" በየትኛውም ቋንቋ በአንድ ቃል ለመተርጎም በጣም አስቸጋሪ ነው ። የስግደት ፀሎት እንዳይባል ከማንኛውም ሃይማኖት ስግደትና ፀሎት ይዘቱ ፍጹም የተለየ በመሆኑ ትክክለኛ ትርጉም ሊሆነው አይችልም ። የሙስሊሞች የስግደት ፀሎት ተብሉ እንዳይተረጎምም ከሞላ ጎደል ትርጁን ይጠቁም እንደሆነ እንጂ ይዘቱን ስለማያመለክት በትክክል ሊገልጸው አይችልም ።

ስለዚህ በአንድ ዓረፍተ ነገር ከመተርጎም ይልቅ ሶላት ምንን እንደሚያትቱ በመጠቆም ምንነቱን መግለጽና ማስረዳት ለተሟላ ግንዛቤ ይረዳል ።

8.1.1. ሶላት ራስን ለዲሲፕሊን ተገዥና መንፈስ ቀራጥ ለማድረግ ማስተማሪያ ኃይል ወይም ትምህርት ነው ፤

8.1.2. ሶላት ፍጹም በሆነ ንቃት ስለአላህና ስለደግነቱም የዘወትር አስታዋሽ ነው ፤

8.1.3. ሶላት የመንፈሳዊነትና የጥሩ ሥነ ምግባር ዘር መዝሪያ መግሪያ ነው ፤

8.1.4. ሶላት ከልክስክስነትና ከክፋት ፣ እንዲሁም ከቀጥተኛው ጎዳና ከመውጣትና ከመደንበር የሚከላከል መግሪያ ነው ፤

8.1.5. ሶላት ዕውነተኛ እኩልነትን ፣ ጠንካራ አንድነትንና ወንድማማችነትን በተግባር ገላጭ ነው ፤

---

[1] ይህ ትምህርት የተወሰደባቸው መጽሐፎች ከምዕራፉ መጨረሻ ተዘርዝረዋል ።

8.1.6. ሶላት አላህን ማመስገኛና እርሱነቱንም ማወዳሻ መሣሪያ ነው ፤

8.1.7. ሶላት ለውስጣዊ ስሜት ሠላምና እርጋታ ሰጭ ነው ፤

8.1.8. ሶላት የማያልቅ ትዕግሥትና ድፍረት ፣ እንዲሁም በራስ የመተማመን እምነት ምንጭ ነው ፤

8.1.9. ሶላት ለአላህ እንዲሁም ለማንኛውም ክቡር ለሆኑና ዋጋ ላላቸው ዓላማዎች ራስን በፍጹምነት ለማሠለፍ መለማመጃ ዘዴ ነው ።

ሶላት ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ቁም ነገሮች የሚያጠቃልል ተግባር ነው ። ሶላት እነዚህን ቁም ነገሮች ለሰው ልጅ ያጎናጽፋል ። የዚህ አባባል ትክክ ለኛ ነት ጥሩ ምስክር ሊሆን የሚችለው ሶላቱን በሥርዓቱ መስገድና ሊሰጠን የሚችለውን መንፈሳዊ እርካታ መቅመስ ብቻ ነው ። የሶላትን መንፈሳዊ እርካታ የቀመሰ ሰው ብቻ ነው ሶላት በትክክል ምን እንደሆነ ሊገባው የሚ ችል ። ሶላት ከዕባዳ ዘዴዎች ዋነኛው ወይም ቁንጮው ነው ፤

የሚለውን አባባል በሚገባ የሚረዳው ሶላትን በአግባቡ የሰገደና ሌሎችንም ዒባዳዎች በመፈጸም ለማነጻጸር ያቻለ ሰው ብቻ ነው ።

8.2. ሶላት በእስላም ዲን ያለው ሥፍራ (ደረጃ) ፤

<u>ሶላት በሙስሊሞች ላይ ግዴታ (ዋጂብ) ሆኖ የወረደ የእስላም ዲን መሠረታዊ</u> ሕግ መሆኑን መቀበል ግዴታ ነው ። በሙስሊምነትና በካፊርነት መሐል ያለው አንዱ መለያ ሶላት ነው ። አላህ ከብሩ ይስፋና ይህን አባባል ሲያረጋግጥ እንዲህ ይላል ፤

وَأَقِيمُوا۟ ٱلصَّلَوٰةَ وَلَا تَكُونُوا۟ مِنَ ٱلْمُشْرِكِينَ الروم ٣١

"ከሙሽሪኮች (አጋር ከሚያደርጉት) እንዳትሆኑ ፣ ሠላትን አቁሙ ፣ (ስገዱ) ፣"[2] (ም ፴ ቁጥር ፴፩)

ሶላት ከገሃነም እሳት የሚያድነንና የእምነታችን ጠባቂ ነው ። ሶላት ቀናውን መንገድ ለመያዝና የአላህን ፍርሃት በልቦናችን የሚያሳድር መሆኑን አላህ ሲያስገነዝበን እንዲህ ይላል ፤

ٱلَّذِينَ يُؤْمِنُونَ بِٱلْغَيْبِ وَيُقِيمُونَ ٱلصَّلَوٰةَ وَمِمَّا رَزَقْنَٰهُمْ يُنفِقُونَ ﴿٣﴾ وَٱلَّذِينَ
يُؤْمِنُونَ بِمَآ أُنزِلَ إِلَيْكَ وَمَآ أُنزِلَ مِن قَبْلِكَ وَبِٱلْءَاخِرَةِ هُمْ يُوقِنُونَ ﴿٤﴾
أُو۟لَٰٓئِكَ عَلَىٰ هُدًى مِّن رَّبِّهِمْ ۖ وَأُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْمُفْلِحُونَ البقرة ٣-٥

"ለነዚያ በሩቅ ነገር የሚያምኑ ፣ ሶላትንም ደንቡን ጠብቀው የሚሰግዱ ከሰጠናቸውም ሲሳይ የሚቸሩ ለሆኑት ፣ - - - እነዚያ ከጌታቸው በመመራት ላይ ናቸው ፤ እነዚያም እነሱ ፍላጎታቸውን ያገኙ ናቸው ።" (ም ፪ ቁ ፫/፭)

قَدْ أَفْلَحَ مَن تَزَكَّىٰ ﴿١٤﴾ وَذَكَرَ ٱسْمَ رَبِّهِۦ فَصَلَّىٰ الأعلى ١٤-١٥

[2] እዘውትራችሁና ደንቡን እሟሏታችሁ ስገዱ ፤

“የተጥራራው ሰው በእርግጥ ዳነ፤ የጌታውንም ስም ያወሳና የሰገደ ።” (ም ፹፯ ቁ ፲፬-፲፭)

قَدْ أَفْلَحَ ٱلْمُؤْمِنُونَ ﴿١﴾ ٱلَّذِينَ هُمْ فِى صَلَاتِهِمْ خَـٰشِعُونَ    المؤمنون ١-٢

“ምዕመናን ፍላጎታቸውን ሁሉ በእርግጥ አገኙ (ዳኑ) ። እነዚያ እነሱ በስግደ ታቸው ውስጥ (አላህን) ፈሪዎች ።” (ም ፳፫ ቁ ፩-፪)

وَٱلَّذِينَ هُمْ عَلَىٰ صَلَوَٰتِهِمْ يُحَافِظُونَ ﴿٩﴾ أُو۟لَـٰٓئِكَ هُمُ ٱلْوَٰرِثُونَ ﴿١٠﴾
ٱلَّذِينَ يَرِثُونَ ٱلْفِرْدَوْسَ هُمْ فِيهَا خَـٰلِدُونَ    المؤمنون ٩-١١

“እነዚያም እነሱ በስግደቶቻቸው ላይ የሚጠባበቁ ፣ የሆኑት (አገኙ)፤ እነዚያ ወራሾች እነርሱ ናቸው ፤ እነዚያ ፊርደውስን (ላዕላይ ገነትን) ፣ የሚወርሱ ናቸው ።” (ም ፳፫ ቁ ፱-፲፩)

مَا سَلَكَكُمْ فِى سَقَرَ ﴿٤٢﴾ قَالُوا۟ لَمْ نَكُ مِنَ ٱلْمُصَلِّينَ    المدثر ٤٢-٤٣

“(ይሉዋቸዋልም)፤ በስተቀር ውስጥ ምን አገባችሁ ? (እነርሱም) ይላሉ ከሰጋ ጆቹ አልነበርንም ።” (ም ፸፬ ቁ ፵፪-፵፫)

እነዚህ የቁርአን አንቀጾች ፈተናን ለማለፍ ፣ በአኺራ (በመጨረሻው ዓለም) የተመኘነውን ለማግኘትና ከሲኦል ለመዳን ሶላትን ደንቡን ጠብቆ መስገድ የሚረዳ መሆኑና ፣ ሶላትን የማይሰግዱት ከሲኦልም በጣም አደገኛው ወደ ሆነው ወደ “ሰቀር” የሚወርዱ መሆኑን ያስገነዝባሉ ። ሶላት በየቀኑ የሚሰ ገድ በአጠቃላይ ሁሉም ሰው ላይ (ዋጂብ) ግዴታ የሆነ የአላህ መመሪያ ነው ። ሶላት ጌታና ባሪያን ፣ ሀብታምና ድሀን ፣ ጤናማና ሕመምተኛን ነዋሪና እንግ ዳን የማይለይ ሁሉም ሰው ላይ ተፈጻሚነት ያለው ግዳጅ ነው ።

ሶላት የማይቀር ግዴታ ስለመሆኑ በጦር ሜዳ ውጊያ ላይም እያለ ቢሆን አንድ ሙስሊም የጦር ሜዳ የአሰጋገድን ሥርዓት ጠብቆ እንዲሰግድ የታዘዘበት የማይቀር ግዴታ ነው ።

በሐዲስ እንደተነገረውም ፣ ኡባዳህ ቢኒ ሣሚት የተባሉት (አላህ ይታረቃቸው) ነቢዩ እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ ብለዋል ፤

﴿ خمس صلوات كتبهن الله على العباد في اليوم والليلة فمن حافظ عليهن
كان له عهد عند الله أن يدخله الجنة ، ومن لم يحافظ عليهن لم يكن له عند
الله عهد ، إن شاء عذبه ، وإن شاء غفر له ﴾ حديث شريف

"አላህ በቀንና ሌሊት አምስት ሶላቶችን ባሮቹ ላይ ግዴጅ አደረገ ፤ ለጠቢቃ
ቸው አላህ ገነት ሊያስገባው ቃል ኪዳን ገብቶዋል ፤ ላልጠበቃቸው ግን አላህ
ዘንድ ምንም ቃል ኪዳን የለውም ፤ ከፈለገ ያቃጥለዋል ፤ ከፈለገም ይቅር
ይለዋል ።"

እዚህ ላይ አንባቢ እንዲያስተውለው የምንፈልገው ነጥብ ፣ ማንም "ሶላት
ምን ይጠቅማል" በሚል ስሜት መስገዱን የተወ ሰው ካፊር የሚሆን መሆኑን
ነው ። ዳሩ ግን ሶላትን በንዝህላልነት ወይም በስንፍና የተወ ሰው ለሶስት
ጊዜ አላህን ይቅርታ የመጠየቅ (ተውባ የማለት) ዕድል ይኖረዋል ፤ ከዚያ
በኋላ ቅጣቱ ሞት ነው ፤ የማለት የኢማሞች (የሃይማኖት መሪዎች) አቋም
ስለአለ መጠንቀቅ ያስፈልጋል ። ምንም እንኳ እንደ ሕብረተሰቡ የፖለቲካ
አስተዳደር ሁኔታ የሞት ቅጣቱ ተፈጻሚ ባይሆንም የጥፋቱን ከባድነት በመ
ረዳት መጠንቀቅ ያስፈልጋል ።

ከዚህ የምንረዳው ሶላት በእስላም መሠረታዊ ቦታ መያዙን ብቻ ሳይሆን
አለመስገድ ከሞት ቅጣት እስከ ካፊርነት የሚያደርስ በደል ስለሆነ ሶላት
ለእስላምነት ወሳኝ መሆኑን ነው ።

## 8.3. ሶላትን መስገድ ለምን አስፈለገ ?

ሶላት ከእስላም ዲን መሠረታዊ ሕጎች አንዱ መሆኑንና አለመስገድ ከባድ
ኃጢአት መሆኑን ከላይ ተመልክተናል ። ሶላት አለመስገድ በጣም ከባድ
በደል ነው የሚባልበት ምክንያት ፣ የአላህን ፈቃድ አለመፈጸም ከመሆኑም
በላይ ከሰው ልጅ የተፈጥሮ ባሕሪይ ውጭ በመሆኑም ጭምር ነው ። ከፍጡሮች
ታላቅነት ያላቸውን በአክብሮት የማድነቅና ለታላላቅ ዓላማዎችና ግቦች
መጓጓት የሰው ልጅ የተፈጥሮ ባሕሪይ ነው ። ከሁሉም በላይ ታላቅና ከዓላማ
ዎችና ግቦች ሁሉም ከቡር የሆነው ሁሉንም ነገር የፈጠረ አላህ ነው ። ስለዚህ
የአላህን ፈቃድ መፈጸም የሰው ልጅ የተፈጥሮ ባሕሪይ ስለሆነ የሚጓጓለትና
እንደ ታላቅ ዓላማው የሚቀጥረው ነው ። አላህም ከብሩ ይስፋና የሰውን ልጅ
የፈጠረው ፈቃዱን እንዲፈጽም ፣ እርሱን እንዲያመልክና እንዲገዛ ለመሆኑ
ሲያረጋግጥ እንዲህ ይላል ፤

وَمَا خَلَقْتُ ٱلْجِنَّ وَٱلْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ    الذاريات ٥٦

"ጋኔንና ሰውንም ሊገዙኝ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም ።" (ም ፶፩ ቁ ፶፮)
የሰው ልጅ የተፈጠረለትንና የሚጓጓለትን ዓላማ እንዴት ሊፈጽም ይችላል ?
የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም ። መልሱም ፣ የሰውን ልጅ ተፈጥሮ በተሟላ
ሁኔታ ለማነፅና የሚጓጓላቸውንም ታላላቅ ዓላማዎች በእድገቱ ሂደት ለማሟ
ላት የሚችልበት ዋናው ዘዴ ሶላት ነው ።

ሶላትን መተው ወይም ለሶላት ዝቅተኛ ግምት መስጠት የሰውን ልጅ ተፈጥሮ
አዊ መልካም ሥነ ምግባር መጫን ከመሆኑም በላይ ያለ በቂ ምክንያት በአን
ክሮ የማድነቅና የመውደድ መብቱን መንፈግ ይሆናል ። እንዲሁም የሰውን
ልጅ ለትላልቅ ዓላማዎች መጓጓትና እየተሻሻለ የመሄድ መብት ፣ በበጎ
ሥነ ምግባር በልጦ የመገኘት መብትና የተከበሩና የተወደዱ ሥራዎችን የመ
ሥራት መብት እንዳይኖረው ማድረግ ይሆናል ። እንዲህ ያለውም ተፅዕኖ

የሶላትን ምንነት የተነተነና ልዩ ባሕሪውንም ያጠና ሰው ባዶ የሰውነት እንቅስቃሴ ፡ ወይም የቁርአንን አንቀጾችን መድገም ብቻ አለመሆኑን ይገነዘባል ። ሶላት ተወዳዳሪና ከዚህ ቀደም አምሳያ ያልተገኘለት በአእምሮ የማሰብን ፡ በመንፈስ ፍጹም ሆኖ መቅረብን ፡ በሥነ ምግባር (ሞራል) ልቆ መገኘትንና በንቃት ሰውነትን የማንቃንት ተግባርን በሙሉ ያጠቃለለ ነው ፤ እያንዳንዱ የሰውነት ክፍል ጡንቻውን ከመንፈሱና አእምሮው ጋር በማቀናጀትና በማዋሐድ አላህን ዒባዳ ለማድረግና እርሱንም ለማምገስ የሰው ልጅ የሚቀርብበት ሶላትብቻ ነው ።

## 8.5. "<u>ከእስላም" በፊት በነበሩት</u> ሃይማኖቶች ዘንድ የሶላት ሁኔታ እንዴት እንደ ነበረ አንዳንድ ምሳሌዎችን በመውሰድ ለማቅረብ እንሞክራለን ።

ሶላት ማለት የቋንቋ ትርጉሙ ዒባዳ ማድረግ ማለት ስለሆነና ፡ በእምነት ላይ የተመሠረተ አምልኮት ካለም ዒባዳ ማድረግ ስለማይቀር በሌሎች ሃይማኖቶችም ሶላት የነበረ ለመሆኑ አያከራክርም ።

ከዚህ ቀጥሎ "የእስላም" ዲን ስለሶላት ያለውን ይዘት ከቅድመ ዝግጅቱ ሶላትን ሰግዶ እስኪወጣ ድረስ አንድ ሰው ምን ማድረግ ፡ ምን ማንበብ ወዘተ - - እንዳለበት በዝርዝር ለማቅረብ ይሞከራል ። የሚነበቡ ፀሎቶች ለዛቸው እንዳይጠፋ ሳይተረጐሙ በአረብኛ ይቀርቡና አጠቃላይ መልዕክታቸው ለአንባቢ እንዲደርስ በአማርኛ ይቀርባል ።

## 8.6. <u>የሶላት ዓይነቶች በእስላም ዘንድ</u>

በእስላም ዲን ሶላት ፈርድ (ግዴታ) የሆነና ፡ ሱናህ ወይም ተጠውዕ (ለተጨማሪ ወሮታ በራስ ፍላጎት የሚሰገድ) ተብሎ በሁለት ይከፈላል ።

### 8.6.1. ፈርድ የሆነውም ሶላት በሁለት ይከፈላል ።

<u>ፈርድ ዓይን</u> ፤ እያንዳንዱ ሰው ሊሰግደው ግዴታ የሆነ ሶላት ነው ። እርሱም በየቀኑ የሚሰገድ የአምስት ጊዜያት[3] ሶላትን ይመለከታል ፤

<u>ፈርድ ኪፋያህ</u> ፤ የእስላሙ ሕብረተሰብ የጋራ ግዴታ ሆኖ ከፊሉ እስከ ሰገደው ድረስ ለቀረው ክፍል ግዴታው የሚወርድ ሶላት ነው ።

እርሱም የሁለቱ ዒዶች (ዒደል ፍጥር እና ዒደል አድሃ) ሶላትና ፡ ሶላቱል ጀናዛ (ሬሣ ላይ የሚሰገድ) ናቸው ።

### 8.6.2. ሡናህ የሆኑት ሶላቶች ብዛት ያላቸው ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ፤

፩/ ከአምስቱ የፈርድ ሶላቶች ጋር የሚሰገዱ የሱናህ ሶላቶች ፤

-ከሶላተልፈጅር ከመሰገዱ በፊት የሚሰገድ ሁለት ረከዓ ሶላት ፡

[3] ሱብሖ (ፈጅር) የማለዳ ሶላት
ዙሕር ፡ የእኩለ ቀን ሶላት
ዓስር ፡ ወደ አሥር ሰዓት የሚሰገድ ሶላት
መግሪብ ፡ ፀሐይ እንደጠለቀች የሚሰገድ ሶላት
ዒሻእ ፡ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አካባቢ የሚሰገድ ሶላት

መዳሰስ ፤ እንገትንም በእርጥብ እጅ መዳሰስና ሁለት እግሮችን እስከ ቁርጭምጭሚት መታጠብን ይመለከታል ። ውዱዕ የሚያደርግ ሰው የተጠቀሱትን የሰውነት ክፍሎች ለሶላት የሚታጠባቸው መሆኑን መወሰን ፣ (ኒያህ ከልቡ ማድረግ) ይኖርበታል ። ውዱዕ ሲያደርግ በቃሉ የሚደግግቸውን ቃላት በስተመጨረሻው በአረብኛ እናሰፍራለን አጠቃላይ መልዕክቱንም በአማርኛ እንሰጣለን ።

ውኃ በሌለበት ጊዜ ፣ ወይም በውኃ መጠቀም ጤንነቱ ላይ ጉዳት ማድ ረሱን የተጠራጠረ ሰው በውዱዕ ምትክ "ተየሙም" (በንፁሕ አፈር ሁለት እጆቹን እየመታ አፈሩን ካራገፈ በኋላ አንድ ጊዜ ፊቱን መዳሰስ ፣ እንደገናም አፈሩን በሁለት እጁ ከመታ በኋላ በግራ እጁ ቀኝ እጁን እስከነክንዱ በሙሉ መዳሰስ ፣ በቀኝ እጁም ግራ እጁን እስከነክንዱ በሙሉ መዳሰስ) ለማድረግ ኒያህ (ከወሰነ) ካደረገ በኋላ በመፈጸም ሊዘጋጅ ይችላል ።

፪/ ሰውነታችን በሙሉ ከነጃሳ (እንደ ሽንት ሠገራ ወዘተ - -) የጠራ መሆን አለበት ፤ ሽንት ቤት ለመጸዳዳት የገባ ሰው የመጸዳጃ አካሉን መታጠብ አለበት ፤ የለበሰውም ልብስ ከነጃሣ የጠራ መሆን አለበት ። የሚሰገድ በት ቦታ ከነጃሣ የጡራ መሆን አለበት ።

፫/ መሸፈን የሚገባቸውን የሰውነት ክፍሎች ለወንድ ልጅ ከእንብርቱና ጉልበቱ ጭምር በመሐል ያለውን አካል መሸፈን ፣ ለሴት ልጅ ከፊቱዋና ከሁለት እጆችዋ (ከጣት እስከ መዳፍ ጭምር ያለው ክፍል) በቀር መላው ሰውነቱዋ በሚገባ በልብስ መሸፈን ፣ ለሶላት የሚቀርብ ሰው ሰውነቱን ሊያሳዩ ከሚችሉት የልብስ ዓይነቶች (ስስ ጨርቅ ወዘተ - - -) መል በስ መወገድ ይኖርበታል ።

፬/ በልብና በቃልም ለሶላት መወሰንን "ኒያህ" ማድረግን መግለጽ ያስ ፈልጋል ።

፭/ ለሶላት ሲቆም ግንባርን ወደ "ቂብላ" ማድረግ ፤ ይሄውም በመካ "ካዕባ" (ታላቁ መስጂድ) ወዳለበት አቅጣጫ ማዞር ያስፈልጋል ። "የቂብላ" አቅጣጫን ማወቂያ ብዙ ዘዴዎች አሉ ። ችግር ከገጠመ የሚሰግድ ሰው የራሱን ጥረት በማድረግ በግምት አቅጣጫውን ሊወስን ይችላል ። እነዚህን ሁኔታዎች ካሟላ አንድ ሰው ለመስገድ ዝግጁ ነው ለማለት ይቻላል ። እዚህ ላይ ማስታወስ የሚያስፈልገው ቁም ነገር አንድ ሰው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከፈጸመ ፣ ወይም በሕልሙም ይሁን በዕውኑ ዘሩ (መኒይ) ከብልቱ ከፈሰሰ ፣ ሴት ልጅ የወር አበባዋና የወሊድ ደሙዋ ሲቋረጥ መላ አካላቸውን ለመጸዳዳት አስበው በመወሰን እስካ ልታጠቡ ድረስ ውዱዕ በማድረግ ብቻ ጸድተው ለሶላት ሊቀርቡ አለመ ቻላቸውን ነው ። በተጨማሪም "ውዱዕ" ያደረገ ሰው "ውዱኡ"ን የሚያረክሱበትና እንደገና ውዱዕ ማድረግን ወይም መላ ሰውነትን መታጠብ የሚያስከትሉ ሁኔታዎችን መዘርዘር ያስፈልጋል ። መላ አካለትን መታጠብ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ከላይ የተገለጹ ሲሆን ፣ "ውዱዕን" የሚያፈርሱ ሁኔታዎች ፤

፮/ ሽንት መሽናት ፣ ሠገራ መውጣትና መፍሳት ፤

አስሶላቱ ኸይሩን ሚነን ነውም ፤ الصلاة خير من النوم

/ሶላት ከእንቅልፍ በላጭ ነው ፤) ካለ በኋላ የቀረውን መደበኛ አዛን ይቀጥላል ።

አዛን ከተደረገ በኋላ ምዕመናን ለሶላት ይሰበሰባሉ ። ሶላት ከመጀመራቸው በፊት "ኢቃማ" ይደረጋል ። "ኢቃማ" ከአዛን ጋር በጣም ሲመሳሰል ልዩነቱ ፤

፩/ በአዛን ከተራ ቁጥር ፩-፭ ያለው ቃል ግማሹ ብቻ ይገለጻል፤ ወይም ይነገራል ፤

፪/ ከተራ ቁጥር ፭ በኋላ ለጥቆ የሚነገር አለ ፤ እሱም "ቀድ ቃመት አሶላት" قد قامت الصلاة (مرتين)

(ሶላት ተጀመረ ።) (ቆመ) የሚል ቃል ለሁለት ጊዜ ይገለጻል ፤

፫/ ከዚያ በኋላ በተራ ቁጥር ፮ እና ሰባት ያለው እንዳለ ይነገራል ፤

፬/ ድምፅ እንደ አዛን ከፍ አይልም ፤ ይፈጥናልም ።

## 8.10. ሶላትን መስገድ ፤

ውዱዕ ተደርጎ አዛንና ኢቃማ ከተደረገ በኋላ ሶላት እንደሚከተለው ይጀመራል ።

### 8.10.1. የንጋት ሶላት ፤ "ሶላቱል ፈጅር ፤"

በንጋት ሶላት ሁለት "ረካዓ" "የሱና" (በራስ ፍላጎት በሚሰገድ) ሶላትና ቀጥሎ ሁለት ረከዓ "የፈርድ" የግዴታ ሶላት ይሰገዳል ። በመሠረቱ ሁለቱ የሚለዩት የሚሰግደው ሰው የትኛውን እንደሚሰግድ ወስኖ በቃሉ በሚገልጸው ነው ። የሱና ከሆነ "ነወይቱ ኡሰሊ ሱነቱል ሶላቱል ፈጅር" ይላል ፤ የፈርድ ከሆነ ደግሞ "ነወይቱ ኡሰሊ ፈርደ ሶላቱል ፈጅር" ይላል ። ይሆን ኒያሕ በልቡ ከያዘም በቃል መገለጹ ግዴታ ሳይሆን የተወደደ ነው ።

ሶላቱን ለመጀመር የሚቀርብ ሲጋጅ ፊቱን ወደ ቂብላ በማዞር በታላቅ ትሕትናና አክብሮት በፍርሃት በተቀጠ ስሜት ሁለት እጆቹን በጆሮው አቅጣጫ ከፍ ካደረገ በኋላ የትኛውን ሶላት ለመስገድ እንደ ወሰነ (ኒያውን) ገልጾ "አላሁ አክበር" በማለት ሁለት እጆቹን ዝቅ አድርጎ ከእንብርቱ በላይ ትንሽ ከፍ ብሎ በማኖር በቀኝ እጁ ግራ እጁን ይይዛል ።

ከዚያም እጅግ ዝቅ ባለ ድምጽ እንዲህ ይላል ፤

ሱብሃነከ አላሁምመ ወቢሀምዲካ ፤ سبحانك اللهم وبحمدك

ወተባረከ ስሙካ ፣ ወተዓላ ጀዱክ ፤ وتبارك إسمك ، وتعالى جدك

ወላ ኢላሃ ጊይሩክ ፤ ولا إله غيرك

አዑዙቢላሂ ሚነሸሸይጣኒር ረጂም ፤ أعوذ بالله من الشيطان الرجيم

ቢስሚልላሂ አርረሀማኒ አርረሂም ፤ بسم الله الرحمن الرحيم

ከዚህ በኋላ እንደገና ሱጁድ ላይ ለመሆን “አልላሁ አክበር” ብሎ ግንባሩን መሬት ላይ ደፍቶ ከላይ በዚህ ሁኔታ ሲኩን ይደግግል ተብሎ የተጻፈውን አሁንም እንደገና ይደግማል ። ከጨረሰ በኋላም “አልላሁ አክበር” በማለት ሁለተኛ ረከዓ ለመጀመር ቆሞ በመከፈቻ ምዕራፍ ንባብ ይጀምርና እንደ መጀመሪያው ሩኩዕ ቀጥሎ የማጎንበሱን (ሩኩዕ) ፤ የሱጁድና የጁሉስን ፤ ከዚያም የሱጁድን ሥርዓት ከሚደገመው ጸሎት ጭምር አጠናቆ ከጨረሰ በኋላ “አልላሁ አክበር” ብሎ (በጁሉስ መልክ) ይቀመጣል ። በዚህም ሁኔታ ቁጭ ብሎ የሚከተለውን <u>“የተሸህሁድ”</u> የመጀመሪያ ክፍል ይደግማል ።

| | |
|---|---|
| አትተሂያቱ አልሙባረካቱ አሠለዋቱ | التحيات المباركات الصلوات |
| አጥጠይባቱ ሊላህ ፤ አሰላሙ ዓለይካ | الطيبات لله السلام عليك |
| አዩሃንነቢዩ ወረህመቱልላሂ ወበረካቱሁ ፤ | أيها النبي ورحمة الله وبركاته |
| አሰሰላሙ ዓለይና ወዓላ ዒባድልላሂ ሰሳሊሂን ፤ | السلام علينا وعلى عباد الله |
| አሽሐዱ አን ላ ኢላሃ ኢለልላህ ፤ | الصالحين ، أشهد أن لا إله إلا الله |
| ዋህደሑ ላ ሸሪከ ለሁ ፤ | وحده لا شريك له ، وأشهد أن محمداً عبده |
| ወሽሰሐዱ አንነ ሙሐመደን ዓብዱሁ ወረሱሉሁ ፤ | ورسوله |

ይህን ካለ በኋላ ሶላቱ ባለ ሶስት ረከዓ (መግሪብ) ፀሐይ እንደጠለቀች የሚሰገድ ሶላት ከሆነ አንድ ረካዓ ለመጨመር ፣ ሶላቱ ባለ አራት ረካዓ እንደ (ዙሑር) የእኩለ ቀን ሶላት ፣ እንደ (ዓስሪ) የአሥር ሰዓት አካባቢ ሶላት ፣ ወይም እንደ ዒሻኢ) ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አካባቢ ሶላት ፤ ሁለት ረከዓ ለመጨመር አላሁ አክበር ብሎ ተነስቶ አንድ ወይም ሁለት ረከዓ ካጠናቀቀ በኋላ እንደገና “ለተሸሁድ” ተቀምጦ ጸሎት ይደግግል ። ከአተሂያቱ ጀምሮ በመቀጠል ከላይ የተጻፈውን ከጨረሰ በኋላ በሁለት ረከዓ ለሚያልቀውም ሆነ በሶስት ረከዓ ወይም በአራት ረከዓ ለሚያልቅ ፈርድ ሶላት ከዚህ በታች ያለውን በመጨመር <u>“አትተሸሁድን”</u> ያጠናቅቃል ።

| | |
|---|---|
| አልላሁምመ ሰሊ ዓላ ሙሐመድ ፤ | اللهم صل على محمد |
| ወዓላ አሊ ሙሐመድ | وعلى آل محمد |
| ከማ ሰለይታ ዓላ ኢብራሂም | كما صليت على إبراهيم |
| ወዓላ አሊ ኢብራሂም | وعلى آل إبراهيم |
| ወባረክ ዓላ ሙሐመድ | وبارك على محمد |
| ወዓላ አሊ ሙሐመድ | وعلى آل محمد |
| ከማ ባረከተ ዓላ ኢብራሂም | كما باركت على إبراهيم |
| ወዓላ አሊ ኢብራሂም | وعلى آل إبراهيم |
| ፊል ዓለሚነ ኢንነካ ሀሚዱን መጂድ | في العالمين إنك حميد مجيد |

ከዚህ ሌላ ተጨማሪ ጸሎት ማድረግ የተወደደ ስለሆነ ጸሎቱን በስተመጨረሻ እናቀርባለን ።

ጋርም እርዳኝ) ፤ በሰጠኸኝ ሲሳይ ውስጥም በረከት አድርግልኝ ፤ በገደልከኝ ጊዜም እዘንልኝ ፤ አንተ ብቻኸው ፈራጅ ስትሆን ባንተ ላይ አይፈረድምና (ፈራጅ የለምና) አንተ ያከበርከው (አንተ ረዳት የሆንክለት ሰው) አይዋረድም ፤ አንተ የጠላኸው ሰውም በምንም ዓይነት አይከበርም ፣ ጌታዬ ሆይ ! አንተ ከጉድለት ሁሉ የጠራህና የልዕልና ባለቤት ነህ ፤ ለወሰንከው መልካም ነገር ሁሉ ምስጋና ይድረስህ ፡ ምሕረት እለምንሃለሁ ፣ ወዳንተም እመለሳለሁ (ከጥፋቴ) ፤

አልላህ ሆይ ! ለነቢይህ ሙሐመድ ፣ ለቤተሰባቸውና ለባልደረቦቻቸው ሁሉ የአክብሮት እዝነትና ሠላም አድርስላቸው ።

### 3.10.2. ሶላቱ "አዙሕር" (የእኩለ ቀን ሶላት)

ይህ ሶላት ፀሐይ ከእኩለ ቀን ሥፍራዋ ትንሽ ስታልፍ የሚሰገድ ነው ። ሶላቱ አራት ረከዓ ሲሆን በ"ኒያ" ተጀምሮ ከሁለት ረከዓ በኋላ ለመጀመሪያው ተሸሁድ ተቀምጦ ይደገማል ፤ ቀጥሎም ሁለት ረከዓ ከተሰገደ በኋላ ለመጨረሻው "ተሸሁድ" ተቀምጦ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ያለውን የ"ተሸሁድ" ፀሎት ደግሞ በ"አሰላሙ ዓለይኩም" ያልቃል ።

ዓርብ ዕለት የሚሰገደው የዙሕር ሶላት በሁለት ረከዓ ብቻ የሚያበቃበት ሁኔታ አለ ። ይሄውም ሶላቱን በመስጊድ ተገኝቶ በወቅቱ ኢማሙ (መሪው) የጁምዓ ኹጥባ (ስበካ) ካሰሙ በኋላ ሲሰገድ ብቻ ነው ። ወቅቱ ካለፈ ፣ ወይም ከመስጊድ ውጭ "ኹጥባ" ሳይደረግ ከተሰገደ አራት ረከዓ መስገድ ያስፈልጋል ፤ (ግዴታ ነው ።)

### 3.10.3. ሶላቱ "አልዓስሪ" (ቀኑ ሲገፋ የሚሰገድ)

ይህ ሶላት የሚሰገደው ቀኑ ገፋ ብሎ ጥላችን ከእኛ ቁመት ሁለት ያህል ሲሆን ነው ። አብዛኛውን ጊዜ ከዘጠኝ ተኩል እስከ አስር ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ይሆናል ። ሶላቱ አራት ረካዓ ያለው ሆኖ እንደ ዙሕር ሶላት ይሰገዳል ።

### 8.10.4. ሶላቱ "አልመግሪብ" (ፀሐይ ስትጠልቅ የሚሰገድ)

ይህ ሶላት ፀሐይ ጠልቃ ካበቃች በኋላ ወጋገኑዋ በሚታይበት ጊዜ የሚሰገድ ሲሆን ሶስት ረከዓ ያለው ነው ። የመጀመሪያው ሁለት ረከዓ እንተደሰገደ ለመጀመሪያው "ተሸሁድ" ተቀምጦ የመጀመሪያው "የተሸሁድ" ክፍል ይደገማል ፤ ከዚያም ሶስተኛው ረከዓ ተሰግዶ የመጨረሻው ተሸሁድ እንደ "ዙሕሩ" ሶላት ተደግሞ ያበቃል ።

### 81.0.5. ሶላቱ "አልዒሻዕ" በእራት ሰዓት የሚሰገድ)

ይህ ሶላት ፀሐይ ጠልቃ በዓመዛኝ አንድ ሰዓት ያህል ከቆየች በኋላ የሚሰገድ ሲሆን አራት ረከዓ አለው ። የሚሰገደውም እንደ ዙሕርና ዓስሪ ሶላት ነው ።

ማስታወስ የሚገባን የፈጅር ፣ የመግሪብና የዒሻ ፈርድ ሶላቶች በወቅታቸው ሲሰገዱ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ረከዓቶች "የመከፈቻው" ምዕራፍና ሌላ በተጨማሪ የሚነበበው ምዕራፍ ወይም አንቀጽ ጎላ ባለ ድምጽ የሚነበብ መሆኑን ነው ። እንዲሁም የጁምዓ ሶላት ሲሰገድ ኢማሙ (መሪው) ጎላ ባለ ድምጽ የመከፈቻውን ምዕራፍና የሚጨመረውን ምዕራፍ ወይም አንቀጽ ያነባል ።

### 8.10.6. ከነዚህ ከአምስቱ "ፈርድ ዓይን" ከሆኑ ሶላቶች ሌላ "በፈርድ ኪፋያ" ሥር የተመለከቱት የሁለቱ ዒዶች ሶላት አሰጋገድ ፤

በመሠረቱ እንደ ዓርቡ ዕለት ሶላት ሕዝብ በተሰበሰበበት የሚሰገድ ሲሆን ልዩነቱ ሶላቱ ከመጀመሩ በፊት "ተክቢር" መደረጉና ለሶላት በሚቆምበት ጊዜ "ኒያ" ከተደረገ በኋላ "አልላሁ አክበር" የሚለው ቃል በሁለቱም ረከዓቶች ላይ በመጀመሪያው ሰባት ጊዜ ፣ በሁለተኛው ረከዓ ስድስት ጊዜ መድገሙ ብቻ ነው ።
የ"ተክቢሩ" ቃል የሚከተለው ነው ፤

አልላሁ አክበር ፤ አልላሁ አክበር ፤ አልላሁ አክበር ፤

الله أكبر الله أكبر الله أكبر

ላኢላሀ ኢላ አላሀ ፤ አላሁ አክበር ፤ — لا إله إلا الله الله أكبر

አልላሁ አክበር ፤ ወሊላሂል ሐምድ ፤ — الله أكبر ولله الحمد

አልላሁ አክበር ከቢራ ፤ ወልሀምድ ሊላሂ ከሲራ ፤

الله أكبر كبيراً والحمد لله كثيراً

ወሱብሃን አልላሂ ቡክረተን ወአሲላ ፤ — وسبحان الله بكرة وأصيلاً

ላኢላሀ ኢልላ አላሀ ወሀደሁ ፤ ሰደቀ ወዕደሁ ፤ — لا إله إلا الله وحده، صدق وعده

ወነሰረ ዓብደሁ ፤ ወአዓዛ ጁንደሁ ፤ — ونصر عبده، وأعز جنده

| | |
|---|---|
| ወሐዘመል አህዛብ ወህደሁ ፡ | وهزم الأحزاب وحده |
| ላኢላሀ ኢላ አልላሁ ወላ ነዕቡዱ ኢላ እያሁ | لا إله إلا الله ، ولا نعبد إلا إياه |
| ሙኽሊሲነ ለሁ አድዲነ ወለው ከሪሐል ካፊሩን ፡ | مخلصين له الدين ولو كره الكافرون |
| አልላሁመ ሰሊ ዓላ ሰይድና ሙሐመድ ፡ | اللهم صل على سيدنا محمد |
| ወዓላ አሊ ሠይድና ሙሐመድ ፡ | وعلى آل سيدنا محمد |
| ወዓላ አስሐቢ ሰይድና ሙሐመድ ፡ | وعلى أصحاب سيدنا محمد |
| ወዓላ አንሳሪ ሰይድና ሙሐመድ ፡ | وعلى أنصار سيدنا محمد |
| ወዓላ አዝዋጂ ሰይድና ሙሐመድ ፡ | وعلى أزواج سيدنا محمد |
| ወሰሊም ተስሊማን ከሲራ ፡ | وسلم تسليماً كثيراً |

## የዚህ የ"ተክቢር" መልዕክት ባጭሩ

አላህ ታላቅ ነው ፡ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም ፡ ለአላህ ምስጋና ይግባው ፡
የአላህን ታላቅነት የማስተጋባት ፣ ለእርሱ በብዛት ምስጋና ማቅረብና እጅግ
ከፍ ያለ ጌታ መሆኑን ነጋ ጠባ እናስተጋባለን ፡ ከአላህ በቀር አምላክ የለም ፡
ብቻውን ነው ፡ ቃል ኪዳኑን አከበረ ፡ ድል ለባሪያው እንዲሆን ፣ አደረገ ፡
ሠራዊቱን የድል ባለቤት አደረገ ፡ (ካፊር) ሕዝቦችን ብቻውን ድል ነሣ ፡
ያለ እርሱ አምላክ አለመኖሩን ተቀበልን ፡ ካፊሮች ቢጠሉም ለእርሱ ብቻ
ዲንን አጥርተን እንገዛለን ። አላህ ሆይ ! ለመሪያችን ሙሐመድና ለቤተሰባ
ባቸው እንዲሁም ለነቢዩ ሙሐመድ ተከታዮች ፣ ጓደኞች ፣ ደጋፊዎች (አንሳ

ሚን ዓዛቢከ ሀታ ተብዐሰሁ
ኢላ ጀነቲከ ቢራሀመቲከ
ያአርሃመራሂሚን ።”

مـــن عـــذابك حـــتى تبعثـه
إلــى جنّتــــك بـرحمتـك
يـــــاأرحـــم الـــــرّاحمـــين

<u>ትርጉሙ ፤</u>

“ጌታዬ ሆይ ይህ አገልጋይህ ነው ፤ የአገልጋይህም ልጅ ነው ፤ ከዚች ዓለም አየርና ነፋስ ወጥቷል ፤ ከሚወዳቸውና ከሚወዱትም ተለያይቶ ሥራውን ወደሚያገኝበት ወደ መቃብር ጨለማ ተጓዘ ፤ በዚህች ዓለም በሚኖርበት ጊዜ “ካንተ በስተቀር አምላክ የለም ፤ ሙሐመድም አገልጋይ መላዕክተኛ ነው” ብሎ ይመሰክር ነበር ፤ ሆኖም ስለእርሱ አንተ ከኛ የበለጠ ታውቃለህና ጌታዬ እሱ ወደአንተ መጣ ፤ አንተ ደግሞ ከማንም የበለጠ አስተናጋጅ ነህ ወደ አዝነትህም ከጃይ ሆነ አንተም እሱን ከማሰቃየት ታጋሽ ነህና እኛም ምሕረ ትን ታወርድለት ዘንድ እነሆ በአማላጅነት ልንለምንህ መጥተናል ፤ ጌታዬ በጎ አድራጊ ከነበረም ምንዳውን ጨምርለት ፤ ከፉ አድራጊ ከነበረም እለፈው ፤ ማረውም ፤ መሐሪ ነህና ወደ ገነትም እስከምትቀሰቅሰው ድረስ ርሀራሄና ደህንነትን ስጠው አንተ ሆይ ከአዛኞች የበለጠ አዛኝ ነህና ።” ማለት ይሆናል ፤

ከዚህ በኋላ አሁንም ለአራተኛው ተክቢር “አላሁ አክበር” ይላል ። እንደ መደበኛ ሶላት “አሠላሙ ዓለይኩም ወረህመቱላህ” በማለት ወደ ቀኝና ግራ ዞሮ ሶላቱን ያጠቃልላል ። ምዕመናኑም ኢማሙን ይከተላሉ ።

ከዚህ በላይ የቀረበው ከሶላት መሠረታዊ የሆኑትን ሕግጋት በአጭሩ ለአንባቢ ለማስተዋወቅ ነው ። በሰፊው ለማወቅ ለሚሻ አያሌ የፊቅሕ መጽሐፎች የተጻ ፉለት ስለሆነ እነርሱን ማንበብ ይጠቅማል ።

ይህን ምዕራፍ ከማጠቃለላችን በፊት ለሶላት መግቢያ ፀሎት ከቀረበው “ሱብሃነከ አላሁማ ወቢሐምዲከ” ከሚለው ፀሎት ለመግቢያ ምዕመናን በብዛት የሚጠቀሙበት ፀሎት መኖሩን ፣ እሱም ፤

ወጀሕቱ ወጅሒ ሊለዚ ፈጠረ ሰማዋት
ወልአርደ ሀኒፉን ሙስሊመን ወማ አና
ምነል ሙሽሪኪን ፤
እንነ ሰላቲ ወኑሱኪ ወመህያያ ወመማቲ
ሊላሂ ረቢል ዓለሚን
ላ ሸሪከ ለሁ ወቢዛሊከ ኡሚርቱ
ወአና ሚነል ሙስሊሚን

وجهت وجهي للذي فطر السموات
والأرض حنيفاً مسلماً وما أنا
من المشركين
إن صلاتي ونسكي ومحياي ومماتي
لله رب العالمين
لا شريك له وبذلك أمرت
وأنا من المسلمين.

እንዲሁም ,የሁለተኛው ክፍል “ተሸሁድ” እንንከ ሀሚዱን መጂድ ብሎ ካለቀ በኋላ ሶላቱን በ“አስላሙ ዓለይኩም” ከመጨረሱ በፊት የሚደረግ ፀሎት መኖሩን መጥቀሱና ማቅረቡ ይረዳል ፤ እርሱም ፤

አላሁማ ኢግፊርሊ ማ ቀደምቱ ወማ አኸርቱ
ወማ አስረርቱ ወማ አዕለንቱ ፤ ወማ አንተ

اللهم اغفر لي ما قدمت وما أخرت
وما أسررت وما أعلنت وما أنت

وَلَا تَلْبِسُوا۟ ٱلْحَقَّ بِٱلْبَٰطِلِ وَتَكْتُمُوا۟ ٱلْحَقَّ وَأَنتُمْ تَعْلَمُونَ
وَأَقِيمُوا۟ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتُوا۟ ٱلزَّكَوٰةَ وَٱرْكَعُوا۟ مَعَ ٱلرَّٰكِعِينَ

البقرة ٤١-٤٢

"እውነትንም በውሸት አትቀላቅሉ ፣ እናንተም የምታውቁ ስትሆኑ እውነትን አትደብቁ ። ሶላትንም ደንቡን ጠብቃችሁ ስገዱ ፤ ዘካትንም (ግዴታ ምጽዋትን) ስጡ ፤ (ለጌታችሁ) ከአጎንባሾች ጋርም አጎንብሱ ።" (ም ፪ ቁ ፵፪-፵፫)

እንዲሁም አላህ ክብሩ ይስፋና ፤ ሰይዱና ዒሣ (እየሱስ) በሕይወታቸው ሳሉ ሶላትና ዘካን አደራ ያላቸው ስለመሆኑ በሱረቱል መርየም አንቀጽ ፴ እና ፴፩ እንዲህ ይላል ።

قَالَ إِنِّى عَبْدُ ٱللَّهِ ءَاتَىٰنِىَ ٱلْكِتَٰبَ وَجَعَلَنِى نَبِيًّا ﴿٣٠﴾ وَجَعَلَنِى مُبَارَكًا أَيْنَ مَا
كُنتُ وَأَوْصَٰنِى بِٱلصَّلَوٰةِ وَٱلزَّكَوٰةِ مَا دُمْتُ حَيًّا

مريم ٣٠-٣١

"(ሕፃኑም) አለ ፣ እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ ፤ መጽሐፍን ሰጥቶኛል ፤ ነቢይም አድርጎኛል ። በየትም ሥፍራ ብሆን ብሩክ አድርጎኛል ፤ በሕይወትም እስከ አለሁ ሶላትን በመስገድ ፣ ዘካንም በመስጠት አዞኛል ።" (ም ፲፱ ቁ ፴-፴፩)

9.2.2. ቀደም ሲል በመጡት ዲኖች ስለዘካት ጠለቅ ባለ መልክ ለማጥናት ለሚፈልግ ሰው ችግር ይኖራል ። ይሄውም ዘካት በማን ላይና በምን ላይ ግዴታ እንደሆነ ፡ ከአንድ ነገር በምን መጠን ዘካት መከፈል እንዳለበት ፤ ከመቶ ስንት ወይም ምን ያህል መውጣት እንዳለበት ፤ ዘካቱ በእንዴት ያለ መልክ መከፋፈል እንዳለበት ፣ ተጠቃሚዎቹ እነማን እንደሆኑ ፣ በእስላም ሃይማኖት ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ እንደሚገኘው በሌሎች ቀደም ያሉ ሃይማኖቶች መልስ ለማግኘት እንደሚያስቸግር ይነገራል ። ስለዚህም የእስላም ሃይማኖትና ሌሎቹን ዘካትን አስመልክቶ አወዳድሮ ለማቅረብ በጣም ያስቸግራል ።

## 9.3. በእስላም ዲን ዘካት ያለው ደረጃ (ማዕረግ)

ዘካት ከአምስቱ መሠረታዊ የእስላም ዲን ሕጎች (አርካኖች) አንዱ በመሆኑ አላህ ክብሩ ይስፋና ፈርድ አድርጎት ሙስሊሞች እንዲወጡት በብዙ የቁርአን አንቀጾች አዞዋል ።

ዘካት በቁርአን አንቀጾች ከሠላሳ ጊዜ በላይ የተደጋገመና ግዴታውም ከሶላት ጋር በጥምር በአብዛኛው አንቀጾች የቀረበ መሆኑ የዘካት ግዴታ ከሶላት ግዴታ ተመጣጣኝ ክብደት የተሰጠው መሆኑን ያሳያል ።

ሶላትና ዘካት አብረው ከቀረቡባቸው የቁርአን አንቀጾች ጥቂቱን ለምሳሌ ያህል እንመልከት ፤

ከበግና ፍየል ዘካት መክፈል ግዴታ የሚሆነው ቁጥራቸው አርባን ካለፈ ነው ።

ለ፵ በግ/ፍየል አንድ በግ/ፍየል እንደዓይነቱ ይሰጣል ፣

ከ፩፻፳፩ በግ/ፍየል ሁለት በግ/ፍየል እንደዓይነቱ ይሰጣል ፣

ለ፪፻፩ በግ/ፍየል ሶስት በግ/ፍየል እንደዓይነቱ ይሰጣይል ፣

ከ፫፻፩ በግና ፍየል በላይ ከሆነ በየመቶው በግ/ፍየል አንድ በግ/ፍየል እንደ ዓይነቱ ይሰጣል ።

ከላይ የተመለከተው በአጭሩ እንስሳትን የሚመለከት ዘካ ቁጥራቸው ስንት ሲደርስ ግዴታ የሚኖርብን መሆኑን ለማሳየትና የሚሰጠው መጠንም ምን እንደሆነ ለማሳየት ተሞክሮአል ። ቀጥሎ ከማዕድናች የሚሰጥ ዘካቱ አልማ ልን በሚመለከት ማብራሪያ ይሰጣል ።

9.5.2.2 ዘካቱ አልማል ዋጅብ የሚሆንባቸው የማዕድን ዓይነቶች ወርቅና ብር ናቸው ። ወርቅም ሆነ ብር በባለቤቱ እጅ ዓመት ሙሉ ከቆየና ለአገልግሎት ወይም ለመጋጌጥ ካልዋለ ፣ እንዲሁም ብዛቱ ዘካት ዋጂብ የሚሆንበት መጠን ከሆነ ዘካ ይወጣበታል ። ዘካት ዋጂብ የሚሆንበት መጠን ሃያ ሚስቃል[1] ሲሆን ዋጋው በግብጽ ፓውንድ ወርቁ ፲፪ ፣ ብሩ ፮ ፓውንድ የሚያወጣ ሲሆን ነው ። ይህም $20 \times 3.88 = 77.60$ ግራም ነው ።

ወርቅና ብር በኢማም አቡ ሃኒፉ መዝሐብ ለአገልግሎት ከዋለም ዘካት ይከፈ ልበታል ። ዘካት የሚከፈለውም ከመጠናቸው ወይም በጊዜው ዋጋቸው 2.5% ነው ።

9.5.2.3 ሶስተኛው ዘካቱ አልማል ዋጂብ የሚሆንበት ሀብት የእርሻ ሰብልና ፍራፍሬ ነው ። ዘካቱ ዋጂብ የሚሆነው መጠኑ አምስት ኩንታልን ሲያልፍ ሆኖ የሚ ሰጠውም ሰብሉ ሲታጨድ ወይም ፍሬው ሲሰበሰብ ነው ። መሬቱ ያለ ብዙ ውጣ ውረድና ድካም በዝናብ የሚጠጣ ከሆነ ከታጨደው ወይም ከተሰበሰበው 10% ለዘካት ወጭ ይሆናል ። በድካምና በብዙ ወጭ የሚታረስና የሚ ጠጣ ከሆነ 5% ለዘካት ይሰጣል ።

9.5.2.4 ዘካቱ አልማል ከምንጠቀምባቸው (ከምንገለገልባቸው) እንስሳት ከምንኖር በት ቤት ፣ ከምንለብሰው ልብስ ፣ ለጌጥ ከምንጠቀምባቸው የከበሩ ማዕድናች ፣ ከመጻሕፍት ፣ ለሥራ ከምንገለገልባቸው መሣሪያዎች ወዘተ -- ለንግድ ካልቀ ረቡ በቀር ዘካት ዋጂብ አይሆንባቸውም ። ለንግድ ከቀረቡ ግን ዓመት በባለ ቤቱ እጅ እስከ ቆዩ ድረስ ከዋጋቸው 2.5% ዘካት መክፈል ግዴታ ይሆናል ።

9.5.3. ከላይ በየዓይነቱ የተመለከተው የዘካት መጠን አላህ ገዳጅ አርጎ ያዘዘን ነው ። የአላህን ፈቃድ ለመፈጸም ቃል የገባ ሙስሊም የሆነ ሰው ሁሉ ይህን ገዳጅ የመወጣት ኃላፊነት አለበት ። ባለሀብቱ ራሱ አውቆ መጠኑንም በትክክል

[1] አንድ ሚስ ቃል 3.88 ግራም ነው ።

ወስና የማውጣት ኃላፊነት የተጣለበት ስለሆነ ተቆጣጣሪው አላህ ራሱ መሆኑን ተገንዝቦ ዘካትን በትክክል ማውጣቱን ማረጋገጥና በራሱ መተማመን ይኖርበታል ። አላህ በሚስጥር የያዝነውን ፣ በልባችን ደብቃን ለማንም ሳንናገር ያቆየነውንና በግልጽ የፈጸምነውን ሁሉ የሚያውቅ ጌታ በመሆኑ ራሳችንን ካልሆነ በቀር እርሱን ለማታለል ስለማንችል መጠንቀቅ ይኖርብናል ። ስለ መጠኑ ወይም ዓይነቱ ጥርጣሬ በሚያድርብን ወቅት አስበልጠንና ከጥሩው ዓይነት መርጠን መስጠቱ በአንድ በኩል ግዴታችንን የመወጣቱ ጉዳይ ላይ የመንፈስ እርካታን ሊሰጠን የሚችል ሲሆን ፣ የግዴታ መስጠት ከሚገባን መጠን አሳልፈን ከሰጠንም በዚያው መጠን አሥር እጥፍ ወሮታ (አጅር) ስለምናገኝበት አሳልፎ መስጠቱ ይመረጣል ። ነቢዩ ሙሐመድ (ዓለይ ሂ ሶላቱ ወሰላም) " الحسنة بعشر أمثالها " "መልካም ችሮታ ከእምሳያዋ አሥር እጥፍ (ትሆናለች) ፤" ብለዋል ። የግዴታ መስጠት ከሚገባን አሳንሰን ከሰጠን ግን የምንጠየቅበትና ለፍርድም የምንቀርብበት ፣ ለቅጣትም የምንበቃበት ስለሚሆን መጠንቀቅ የግዴታ ያስፈልጋል ።

ስለዚህ ጉዳይ የሚያስታውሱን አያሌ የቁርአን አንቀጾች አሉ ። ጥቂቶቹን ከዚህ በታች እንጠቅሳለን ።

وَنَضَعُ ٱلْمَوَٰزِينَ ٱلْقِسْطَ لِيَوْمِ ٱلْقِيَـٰمَةِ فَلَا تُظْلَمُ نَفْسٌ شَيْـًٔا ۖ وَإِن كَانَ
مِثْقَالَ حَبَّةٍ مِّنْ خَرْدَلٍ أَتَيْنَا بِهَا ۗ وَكَفَىٰ بِنَا حَـٰسِبِينَ الأنبياء ٤٧

፩/ "በትንሣኤም ቀን ፣ ትክክለኛ ሚዛናችን እናቆማለን ፤ ማንኛይቱም ነፍስ ማንንም አትበድልም ፤ (ሥራው) የሰናፍጭ ቅንጣት ያክል ቢሆንም እርስዋን እናመጣታለን ፤ ተቆጣጣሪዎችም በኛ በቃ ።" (ም ፳፩ ቁጥር ፵፯)

ثُمَّ رُدُّوٓا۟ إِلَى ٱللَّهِ مَوْلَىٰهُمُ ٱلْحَقِّ ۚ أَلَا لَهُ ٱلْحُكْمُ وَهُوَ أَسْرَعُ ٱلْحَـٰسِبِينَ •
الأنعام ٦٢

፪/ "ከዚያም ዕውነተኛ ወደ ሆነው ጌታቸው ወደ አላህ ይመለሳሉ ፤ ንቁ ፣ ፍርዱ ለርሱ ብቻ ነው ። እርሱም ከተቆጣጣሪዎች ሁሉ ይበልጥ ፈጣን ነው ።" (ም ፮ ቁጥር ፷፪)

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ أَنفِقُوا۟ مِن طَيِّبَـٰتِ مَا كَسَبْتُمْ وَمِمَّآ أَخْرَجْنَا
لَكُم مِّنَ ٱلْأَرْضِ ۖ وَلَا تَيَمَّمُوا۟ ٱلْخَبِيثَ مِنْهُ تُنفِقُونَ وَلَسْتُم بِـَٔاخِذِيهِ
إِلَّآ أَن تُغْمِضُوا۟ فِيهِ ۚ وَٱعْلَمُوٓا۟ أَنَّ ٱللَّهَ غَنِىٌّ حَمِيدٌ البقرة ٢٦٧

፫/ "እናንተ ያመናችሁ ሆይ ! ካፈራችሁትና ከዚያም ለናንተ ከምድር ካወጣንላችሁ ከመልካሙ ለግሱ ፤ መጥፎውንም ለመስጠት አታስቡ ፤ በርሱ ዓይናቻችሁን ጨፍናችሁ እንጂ የማትወስዱት ስትሆኑ ከርሱ

(ከመጥፎው) ትስጣላችሁን ? አላህም ተብቃቂ ምስጉን መሆኑን እወቁ ።" (ም ፱ ቁጥር ፻፬)

9.5.4. ዘካት መቀበል ስለሚገባው ሰው ሃሙዳ አብዱልዓጢ የተባሉት የእስላም ዲን ምሁር "እስላም ኢን ፎከስ" በተባለው መጽሐፋቸው ሲያብራሩ መሠረታዊ ፍላጎቱን ለማሟላት ምንም የሌለው ፣ ወይም በዓመቱ መጨረሻ በገምት ከ፲፭ የአሜሪካ ብር ፣ (የኢት ብር 31.5 መሆኑ ነው) በታች ያለው ሰው ነው ብለዋል ።

በዓመቱ መጨረሻ ላይ አንድ ሰው መሠረታዊ ፍላጎቱን አሟልቶ ከብር 31.5 በላይ በእጁ የቀረው ከሆነ ከብር ፴፩፡፭ በላይ ያለውን ለሌላው ችግረኛ አሳልፎ የመስጠትና ሌላ ተጨማሪ ዘካት እንዳይቀበል ግዴታ አለበት ።

9.5.5. ዘካትን በቁርአን ለተጠቀሱት ባለመብቶች በቀጥታ ለመስጠት ይቻላል ፤ ወይም የተጠቀሱትን ችግረኞች ጉዳይ ለሚከታተሉ በጎ አድራጊ ድርጅቶች ለመስጠት ይቻላል ። ምናልባትም በጣም ጎበዝና ታታሪ ለሆኑት የሙስሊም ተማሪዎችም በእስኮላርሺፕ መልክ በቀጥታ ለመስጠት ወይም ተመሳሳይ ዓላማ ላላቸው በጎ አድራጊ ድርጅቶችም ለመስጠት ይቻላል ።

ዘካት በሚሰጥበት ጊዜ አካለ ስንኩል ወይም የጤና ጉድለት ላለበት ሙስሊም ጤናማ ከሆኑት ቅድሚያ መስጠት ይገባል ። ዘካት ሰጭው የራሱን የሕሊና ዳኝነት በመጠቀም ይበልጥ ለሚገባው ችግረኛ መስጠት ይኖርበታል ።

9.5.6. ለመንግሥት በአሁኑ ዘመን የሚከፈለው ግብር ወይም ታክስ ዘካትን ሊተካ የማይችልና ለመንግሥት የሚከፈለው ተከፍሎ ከተጣራው ንብረት ወይም ሀብት የሚወጣ መሆኑ መታወቅ አለበት ።

ዘካት ለጉራና ለዝና ፍለጋ የሚሰጥ ሳይሆን የራስን ግዴታ በመወጣት የአላህን ፈቃድ ለመፈጸም የሚወጣ ስለሆነ ሰጭው ስሜቱን በማጥራት በንጹሕ ልቦናው ለአላህ ብሎ መስጠት ይኖርበታል ።

እንዲገምትና እንዲረዳ ያደርገዋል ፤ በእጦት ምክንያት ለቀናት ፣ ለሳምንታት እና ለወራት ተመሳሳይ ወይም የባሰና እጅግ የከፋ ችግር ላይ የሚወድቁ መሆኑን ሊገነዘብ ያስችለዋል ። ይህ ልምድ ለማህበራዊ ችግርና ለሰው ልጅ ስቃይ በመራራት አንጻር ከማንም የበለጠ ለወገኖቹ አዛኝና ለችግራቸውም ደራሽ ያደርገዋል ።

ጾም ራስን ለመቆጣጠርና ስሜትን ለመግዛት ፍቱን የሆነ ዘዴ ነው ፤ ጾምን ሥርዓቱን ተከትሎ የሚጾም ሰው በእርግጥ ስሜታዊ ፍላጎቱን የሚቆጣጠርና ሥጋዊ አቋሙን ለመንፈሳዊ አቋሙ የሚያስገዛ ነው ። ቆርራጥና መንፈስ ጠንካራም ያደርገዋል ።

ጾም የተረጋጋ መንፈስን ፣ ሠላም የሠፈነበት አእምሮን በቀላሉ ለማንቀሳቀስ የምንችለውና ጤናማ የሆነ አካልን ሊያስገኝልን ይችላል ። ይህ አባባል ዕውነት መሆኑን የሕክምና ባለሙያዎች ፣ የባዮሎጂ ሕግጋትና በልምድ ላይ የተመሠረቱ የምርምር ውጤቶች ሁሉ ያረጋግጣሉ ።

ጾም በጀትን ለማስተካከልም አስተዋጽኦ ያደርጋል ።

ጾም የተለመደ የአኗኗር ሁኔታን እንድንቀይር በማስገደዱ በአዲስ ሥርዓት እንድንመራ ስለሚያደርግ የችግር ጊዜ ቢመጣም በቀላሉ እንድንቋቋም የሚያስችል ልምድ ይሰጠናል ።

ጾም በምዕመናኑ መሐል ዕውነተኛ የሆነ የመንፈስ አንድነትና የወንድማማችነት ስሜት እንዲዳብር ያደርጋል ፤ አንድ ሙስሊም የሆነ ግለሰብ ሲጾም ከመላው የእስላም ኅብረተሰብ እንደ አንድ አካል ሆኖ መጾሙ የሚሰማው ከመሆኑም በላይ የመጾም ግዴታ ለሙስሊሞች በሙሉ ለአንድ ዓላማ በአንድ ወቅት በመውደቁ በአላህ ፊትና በእስላም ሕግ ከሌሎች ሙስሊሞች ጋር ያለውን የእኩልነት ስሜቱን ያዳብራል ።

ጾም ከሁሉም በላይ የሰው ልጅ በራሱ የመተማመን ስሜቱን ለማጠናከርና ራሱን ለመቆጣጠር እንዲችል ፣ የሰውን ልጅ ክብርና ነፃነት ለመጠበቅና ለድልና ሰላም እንዲበቃ በአላህ የተደነገገ ነው ። ይህ ሐቅ ጾምን በትክክል አውቀው በሚጾሙት ሰዎች ልብ ሕያው ሆኖ ይከሰታል ። አንድ ሰው በትክክል ሲጾም ራሱን ሙሉ በሙሉ ይቆጣጠራል ፤ ስሜቱን ያዛል ፤ ፍላጎቱን ይገታል ፤ እርኩስ የሆኑ ነገሮች እንዳያገኙት ይቋቋማል ፤ እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ ውስጣዊ ሰላምን ተጎናጸፈ ማለት ነው ። ይህም ሁኔታ ከአላህ ጋር ዘለቄታ ያለው ሰላም እንዲኖረው በር ከፋች ነው ። ከአላህ ጋር ሰላም የሆነ ሰው ከመላው ዓለም ጋር ሰላም ይሆናል ።

ጾም ከላይ የተዘረዘሩትን ዓይነት ጥቅሞች የሚያስገኝ በመሆኑና ይህም አላህን እንድንፈራ የሚያደርገና ለፈቃዱም ይበልጥ እንድንገዛ የሚያደርግ በመሆኑ አላህ (ሱብሃነሁ ወተዓላ) የፈጠረንም ለእርሱ እንድንገዛ ስለሆነ ጾምን ግዴታ ሊያደርግብን ችሎዋል ብሎ ለማለት ይቻላል ። ለዚህም አባባል ማስረጃ የሚሆን የቁርአን አንቀጽን ለመጥቀስ ይቻላል ፤

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ كُتِبَ عَلَيْكُمُ ٱلصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن
قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ البقرة ١٨٣

“እናንተ ያመናችሁ ሆይ ! ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደተጻፈ ፣ በናንተም ላይ ተጻፈ ፤ (ተደነባ) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና ።”
(ም ፪ ቁጥር ፩፻፹፫)

ከዚህ የምንረዳው ጾም ግዴታ የሆነብን አላህን በመፍራት የሰው ልጅ ተል ካሻና ፀያፍ ወደ ሆኑ ተግባራት ስሜቱ እንዳያዘነብል እንዲጠነቀቅ ለማድረግ መሆኑን ነው ።

## የእስላም ጾም ከሌሎች ጾም አንጻር

ጾም በሌሎች እምነቶች ከተወሰነ የምግብ ዓይነት ብቻ መቆጠብን የሚጠይቅ ሲሆን ፣ በእስላም ሃይማኖት የንጋት ወጋገን ከመታየቱ በፊት አንስቶ መሽቶ የፀሐይ ብርሃን እስክትጠፋ ድረስ ከማናቸውም ምግብ ፣ መጠጥና ጭስ መቆ ጠብን ይጠይቃል ።

ጾም በእስላም ሃይማኖት የመንፈሳዊ ፣ የሥጋዊና የሥነ አእምሮ ዓላማዎችን ቀደም ሲል በተራ ቁጥር 10.3 ሥር ከተጠቀሱት ዓላማዎች ጋር በማጠቃለል ሰፋ ያለ ዓላማና ጥቅም አለው ።

ጾም በእስላም ሃይማኖት ከምን ጊዜም የበለጠ ፀሎት ማድረስን ፣ ከሰው መጣ ባባትና ትሑት መሆንን ፣ ለቁም ነገር መሰለፍን ፣ መመጽወትን ፣ ቁርዓን ማጥ ናትና ማንበብን ፣ ራስን መግዛትና ሕሊናን ማንቃትን ይጠይቃል ። በመሆኑም ሙስሊም ሲጾም ልዩ ሰው የመሆን ስሜት ያድርበታል ፤ ውስጣዊ ስሜቱና በግልጽ የሚታየው ተግባሩም ብሩህና ንጹሕ በመሆኑና መንፈሱ የጠራና ወደ አላህ እየቀረበ በመምጣቱ የፍጹምነት ስሜቱ እየዳበረ ይመጣል ።

10.4.5 ጾም በእስላም ሃይማኖት ከዓለማዊ ተግባር መለየትን ሳይጠይቅ ሁለ ቱንም አስተባብርና አቀነባብር መራመድን ይጠይቃል ። የዕለት ተዕለት ሥራና መንፈሳዊ ተግባራት በእስላም ጾም የሚለያዩ ሳይሆኑ አብረው የሚጓዙ ናቸው ። ጾም በእስላም በዘመን ውስጥ በተወሰነ ጊዜ በበጋ ወይም በክረምት ወዘተ - - የሚመጣ ሳይሆን የጨረቃን ወር ተከትሎ በተለያዩ ጊዜያት ፣ አንዴ በክረምት፣ ሌላ ጊዜ በበጋ ወዘተ - - - የሚመጣ ነው ። በሌላ አነጋገር ዘንድሮ በግንቦት ከዋለ በሌላ ጊዜ በመስከረም ሊውል ይችላል ። ይህም ለምዕመናኑ ጾምን በዋ ቃት ወይም በቀዝቃዛ ጊዜ እንዲጾሙ ዕድል ስለሚሰጥ የተለያየ ልምድና ለተለዋዋጭ ሁኔታዎች ራሳቸውን ለማዘጋጀት ይረዳቸዋል ።

እስካሁን ስለ ጾም ከቀረበው አጠቃላይ ማብራሪያ የጾምን ምንነት አውቀን ግዴ ታችንን በመወጣት በዚህ ዓለም ሳለን የምናገኘውን ጥቅም ተመልክተናል ። የአላህን ፈቃድ በመፈጸማችን ደግሞ ከአላህ ቃል የተገባልን ወርታ የሚጠ ብቀን መሆኑንም ተገንዝበናል ። ታዲያ ለመጾም ሥርዓቱንና ደንቡን ጠንቅቆ በማወቅ ግዴታን ለመወጣት ተገቢው ጥረት ካልተደረገ በቀር ከምግብና መጠጥ በመቆጠብ ብቻ በእስላም ዲን መሠረት ጾም የተሟላ ስለማይሆን ድካማችን ፋይዳ ቢስ እንዳይሆን ልንጠነቀቅ ይገባል ። ነቢዩ ሙሐመድ (ሰላ አላሁ ዓለይሂ ወሰላም) እንዲህ ብለዋል ፤

﴿ من لم يدع قول الزور والعمل به فليس لله حاجة في أن يدع طعامه وشرابه ﴾

(رواه البخاري)

10.12.5 የጾመ ሰው "ሲዋክ" የማድረግ (በመፋቂያ ጥርስንና አፉን የማጽዳት) ዲስፕሊንን ማክበር ይኖርበታል ፤ "ሲዋክ" ከሰዓት በፊትና በኋላም ሊደረግ ይችላል ።

10.12.6 የጾመ ሰው በተለይም በረመዳን ወር ይበልጥ ቸር እንዲሆንና ይበልጥ ቁርአን እንዲያነብም ይጠበቅበታል ።

10.12.7 የጾመ ሰው በመጨረሻዎቹ አሥር የረመዳን ቀናት ከምን ጊዜም የበለጠ "ዒባዳህ" (ፀሎት) ላይ እንዲበረታ ያስፈልጋል ። (ይህም ከአንድ ሺህ ወራት የበለጠ ማዕረግ ያለባት አንድ ሌሊት "ሌይለቱል ቀድር" በዚህ ጊዜያት ውስጥ ስለምትገኝ ዕለቱ ሊገጥመው ስለሚችል እንዲጠቀም ተብሎ ነው ።)

## 10.13. "መብጢላቱ አሲያም" (ጾምን የሚያፈርሱ ነገሮች)

10.13.1 ከአፍ ወደ ሆድ የሚገቡትን ነገሮች ፣ ከአየር በስተቀር ፣ እያወቁ መብላት ፣ መጠጣት ፣ ማጨስ ፣ ወዘተ - - ጾምን ያፈርሳሉ ። ጾም መሆኑን ዘንግቶ(ረስቶ) የበላ ሰው ጾመኛ መሆኑ ትዝ እንዳለው ከአፉ የሚገኘውን በመትፋት ካጸረጠና ጾሙን ከቀጠለ ጾሙ ይጸናል ፤ (አይፈርስም) ። ለዚህም ማስረጃው አቡሁረይራ ከነቢዩ ሙሐመድ ሰ.አ.ወ. ሰማሁ ብለው ያወሩት ሐዲስ ነው ፤ እንዲህ ይላል ፤

﴿ من أفطر في رمضان ناسياً فلا قضاء عليه ولا كفارة ﴾

ትርጉሙ ፤ "በረመዳን ረስቶ ያፈጠረ (ጾሙን የፈታ) ሰው ምትክ መጾም የለበትም ፤ "ከፋረህ" ማውጣትም (ለንሰሐ ድሀ ማብላትም) የለበትም ።" ማለት ነው ።

10.13.2 ከቁጥጥር ውጭ ራሱ ገፍቶ ካልወጣ በቀር ፣ የተባለውን ወይም የተጠጣውን ማስመለስ ጾምን ያፈርሳል ፤ አውቆ ያስመለሰ ሰው ምትኩን ሌላ ቀን ይጾማል ።

10.13.3 የሴት ልጅ የወር አበባዋ ወይም የወሊድ ደሙዋ መምጣት ጾምን ያፈርሳል ። ቀኑን በጾም ውላ በመጨረሻይቱ የፀሐይ መግቢያ ጊዜ ላይ እንኳ የወር አበባዋ ወይም የወሊድ ደሙዋ ቢታይ ጾሙ ይፈርሳል ።

10.13.4 ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ውጭ ሴትን በማቀፍና በማጫወት ፣ ወይም በእጅ ብልትን በመነካካት "መኒይ" የሰው ዘር ከፈሰሰ ጾም ይፈርሳል ። ዳሩ ግን በዓይን ሴትን ልጅ በማየት ምክንያት ፣ ወይም ቀን በሕልም ምክንያት ከፈሰሰ ጾም አይፈርስም ። እንዲሁም ከብልት የሚፈስ ፈሳሽ (መዝይ ወይም ወድይ) ጾምን አያፈርስም ።

10.13.5 ጾመኛ የሆነ ሰው ጾሙን ለመፍታት ከወሰነ (ኒያህ ካደረገ) ምግብ ባይበላና ባይጠጣም ጾሙ ይፈርሳል ።

10.13.6 ፀሐይ የገባች መስሎት ጾም የፈታ ሰው ፣ ከዚያ በኋላ ያልገባች መሆኑ ከተረጋገጠ ጾሙ ይፈርሳል ። በዚህ ነጥብ ላይ አራቱ "ኢማሞች" (መዝሐቦች)

## 2 ሀጅ በሕይወት አንዴ ብቻ ግዴታ ስለመሆኑ ፣

2.1 የእስላም ዲን ምሁራን ሀጅ በሕይወት ከአንድ ጊዜ በላይ ግዴታ አይሆንም በሚል አቋም ተስማምተዋል ። ዳሩ ግን አንድ ሰው በራሱ ፈቃድ ተጨማሪ ጊዜ ሀጅ ለማድረግ ቃል ኪዳን ከገባ ቃል ኪዳኑን የማክበር ግዴታ ይይዘዋል ። ቃል ኪዳን ሳይገባ ከአንድ ጊዜ በላይ የሚደረግ ሀጅ "ተጠውዕ" ነው ። ይህም በራስ ፈቃድ የሚደረግ ፣ ከአላህ ወሮታ የሚከፈልበት ተግባር ነው ። የሀጅ ግዴታ አንድ ጊዜ ብቻ ለመሆኑ የቀረበው የሐዲስ ማስረጃ እንዲህ የሚል ነው።

﴿ عن ابن عباس رضي الله عنهما قال : خطبنا رسول الله صلى الله عليه وسلم ، فقال : يا أيها الناس كتب عليكم الحج . فقام الأقرع ابن حابس فقال : أفي كل عام يا رسول الله ؟ فقال : لو قلتها لوجبت ، ولو وجبت لم تعملوها ، ولم تستطيعوا الحج مرة فمن زاد فهو تطوع ﴾ (رواه أحمد وأبو داوود والنسائي والحاكم وصححه)

ትርጉሙ ፤ "ኢብኒ ዓባስ (የአላህ ውዴታ ይሁንላቸው) እንዳሉት ፤ ረሱል (ሰላ አላሁ ዓለይሂ ወሠለም) ንግግር አድርገውልን እንዲህ አሉ ፤ "ሰዎች ሆይ ! ሀጅ ግዴታ ሆነባችሁ ፤" አቅረዕ ኢብኒ ሃቢስ ተነስተው ሲጠይቁ ፤ "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ! በየዓመቱ ?" ነቢዩ (ሰ አ ዓ ወ)ሲመልሱ "አዎን ብል ኖሮ ግዴታ በሆነባችሁ ነበር ፤ ግዴታ ቢሆንባችሁም አትሠሩበትም ፤ አትችሉም ፤ ሀጅ አንዴ ብቻ ነው ፤ ከዚያ በላይ ከተጨመረ "ተጠውዕ" ነው ። "ይህንን አህመድ አቡ ዳውድ አነሣኢ እና ሃኪም አውርተውታል ፤ ታርመዋልም ፤ (አረጋግጠ ውታልም)

2.2. ሀጅ የማድረግ ግዴታ በሕይወት አንድ ጊዜ ብቻ መሆኑ ሲረጋገጥ በሕይወት ውስጥ መቼ መደረግ እንዳለበት የእስላም ዲን ምሁራን የተለያየ አቋም ወስደዋል ። እንደ ኢማም ሻፊዒ ያሉት ሀጅ ግዴታ መሆን የሚጀምረው አንድ ሰው ለአቅመ አዳም ሲደርስ ነው ፤ የመጨረሻ የግዴታው ጊዜም ከሞት በፊት ያለው ወቅት ነው ፤ ከግለታቸውም በላይ በዚህ ጊዜ ውስጥ ግዴታውን እስከተወጣ ድረስ በደል እንደፈጸመ አይቆጠርም ፤ ጥያቄም የለበትም ፤ ብለዋል ። እነ ኢማም አቡ ሀኒፋ ፣ ማሊክ ፣ አህመድና ጥቂት የኢማም ሻፊዒ ተከታዮችና ሌሎችም ሀጅን ሳይዘገዩ ሁኔታው እንደፈቀደ በአስቸኳይ ማድረግ ያስፈልጋል የሚል አቋም ወስደዋል ።

እነ ኢማም ሻፊዒ ሁኔታው እንደፈቀደ ሀጅ ማድረግ ይመረጣል እንጂ ግዴታ አይደለም ቢሉም ችሎታ ላለው ሰው ከሞት በፊት ማድረግ ያለበት መሆኑን ገልጸዋል ። ዳሩ ግን አንድ ሰው ችሎታው በነበረው ወቅት ሳይፈጽም ካዘገየውና ወደኋላ በሕመም ፣ በገንዘብ እጦት ወዘተ - - ሳይፈጽም ከቀረና ከሞተ ከተጠያቂነት ስለማይድን ለችሎታው መኖር ሲከሰት ሳይዘገይ አፋጥኖ ማድረግ ያስፈልጋል ።

## 3 "ፈዳኢሉ አልሀጅ" (የሀጅ ደረጃው ፣ /ግዕረጉ)

ሀጅ ከዒባዳህ (ፀሎት) አምልኮት) ሥራዎች የላቀ ሥፍራ ከያዙት መሐል ስለ መሆኑ ፣ ሀጅ እንደ ጂሓድ የሚቆጠር ስለመሆኑ ፣ ሀጅ በደልን /ሐጢአትን ይቅር የሚያስኝ ስለመሆኑ ፣ ሀጅ ወሮታው ገነት ስለመሆኑ ፣ አያሌ ከነቢዩ (ሰ.ዓ.አ.ወ) የተነገሩ ሐዲሶች አሉ ። ጥቂቶቹን እንጠቅሳለን ፤

﴿ عن أبي هريرة رضي الله عنه قال : سئل رسول الله صلى الله عليه وسلم : أي الأعمال أفضل ؟ قال : إيمان بالله ورسوله ، قيل : ثم أي ؟ قال : جهاد في سبيل الله ، قيل : ثم أي ؟ قال : حج مبرور ﴾

ትርጉሙ ፤ በጥቅል ሲታይ ፤ "የአላህ መልዕክተኛው ከሥራ የትኛው ያ.በል ጣል ተብለው ሲጠየቁ በሰጡት መልስ ፣ "በአላህና በመልዕክተኛው ክልብ ግመን ፣ ቀጥሉ ለአላህ መንገድ መታገል ፤ ከዚ.ያም "ሀጅን መብሩር ነጡ" ብሉዋል ሲሉ አቡ ሑሬይራ አወሩ ። "ሀጅን መብሩር" የሚባለው ከሐጢአት ጋር ያልተደባለቀ ፣ ወይም ዓለማዊውን ነገር ችላ ብሉ የአኺራን ፍለጋ ስሚት በመያዝ ከሀጅ ሥርዓት መመለስ ፣ መሆኑን ያመለክታል ይባላል ።

﴿ عن أبي هريرة رضي الله عنه أن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال : جهاد الكبير والصغير والضعيف والمرأة الحج والعمرة ﴾

ትርጉሙ ፤ "የአላህ መልዕክተኛው (.ሰዓ.አ.ወ) "የሽማግሌዎች ፣ የሕፃናቶች የደካሞችና የሴቶች "ጂሓድ" (ትግል) ሀጅና ዑምራ ነው ብሉዋል ።

﴿ عن أبي هريرة رضي الله عنه أن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال : الحجاج والعمار وفد الله ، إن دعوه أجابهم ، وإن استغفروه غفر لهم ﴾

ትርጉሙ ፤ በጥቅሉ ፤ የአላህ መልዕክተኛው (ሰ አ ዓ ወ) ሀጅ የሚያደርጉና ዑምራ የሚያደርጉ (ምዕመናን) የአላህ መልዕክተኞች (እንግዶች) በመሆና ቸው ከለመኑት (ከጠየቁት) መልስ ይሰጣል ፤ ይቅርታ ከጠየቁትም ይቅር ይላቸዋል" ሲሉ ተናግረዋል ሲሉ አቡ ሑሬይራ አውርተዋል ።

﴿ عن أبي هريرة رضي الله عنه أن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال : العمرة إلى العمرة كفارة لما بينهما ، والحج المبرور ليس له جزاء إلا الجنة ﴾

ትርጉሙ ፤ አቡ ሑሬይራ እንዳወሩት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ አ ዓ ወ) ዑምራ ግድረግ "ከዑምራሕ እስከ ዑምራሕ ያለውን ጊዜ ጥፋት (በደል ያሠርያል) ያሠርዛል ። (ከጥፋት) ከበደል ጋር ያልተቀላቀለ የሀጅ ሥርዓትን ማከናወን ወሮታው ገነት ብቻ ነው" ብለዋል ።

## 4 <u>ሀጅ ግዴታ የሆነበት ምክንያት ከሚሰጠው ጥቅም አንፃር ፤</u>

የሀጅ ሥርዓት ሌላው የእስላም ዲን መለያ ነጥብ ሆኖዋል ። ሀጅ በአላህ ከተደ ነገጉባቸው ምክንያቶች መሐል የሚከተሉት ይገኙበታል ፤

4.1. "ሳላቱ አልጀማዓሕ" (አብሮ መስገድ) በየቀኑ ምዕመናን የሚገናኙበት ፣ ሶላቱ አልጁምዓሕ (የዓርብ ቀን ሶላት) ፤ ሶላቱል ዒደይን (በዓመት ሁለት ጊዜ በዓመት በዓል ቀን ተሰብስቦ በጌዳ የሚሰገድ) ፤ በመንደርና በአንድ ከተማ የሚገኙ ሙስሊሞች በየጊዜው እንዲሰበሰቡ ዕድል የሚሰጡ ሲሆኑ ፣ ሀጅ ከእነዚህ ሁሉ እጅግ የሰፋና በዓለም አካባቢ ያሉ ሙስሊሞች ተሰብስበው እርስ በእርሳቸው ለመተዋወቅና የጋራ ጉዳያቸውን ለመወያየት ፣ እንዲሁም የጋራ ጥቅማቸውን ለማራመድ ዕድል የሚሰጥ መድረክ ነው ። የሰው ልጅ ታሪክ ከሚያውቃቸው የሠላም ስብሰባዎች ሁሉ ሀጅ ዘወትር ጊዜውን ጠብቆ የሚ ካሄድና እጅግ ከፍተኛ የሆነ የሰላም ስብሰባ ነው ። በሀጅ ሥርዓት ውስጥ ጎልቶ የሚታየው ዓላማ ሰላም ነው ። ሰላም ከፈጣሪ ጋር ፣ ሰላም ከመንፈሳችን ጋር ሰላም እርስ በእርሳችን ፣ ሰላም ከእንስሳት ጋር ፣ ሰላም ከአዕዋፍና ከጥቃ ቅን ነፍሳት ጋር ይጠበቃል ። ግንኙነቱንም ፍጡር በግንኙነቱም ዓይነት ዘዴ ሰላም መንሳት አጥብቆ የተከለከለ ነው ።

4.1 ሀጅ የእስላም ዲን ዓለም አቀፋዊ መሆኑንና የሙስሊሞች ወንድማማችነትና እኩልነት ፣ በፍጹም የሚያመለክት መገለጫ ነው ። ተበታትነው የሚገኙት ልዩ ልዩ ሕዝቦች ፣ በየሙያው የተሠማሩና በየሕብረተሰባቸው የተለያየ መደብ ላይ የሚገኙት በሙስሊምነታቸው የአላህን ጥሪ በማክበር ምላሽ ለመስጠት መካ ላይ ይሰበሰባሉ ። ሁሉም ቀለል ባለ መንገድ አንድ ዓይነት ቀለም ያለው አንድ ዓይነት ልብስ ይለብሳሉ ፤ አንድ ዓይነት ደንብ ያከብራሉ ፤ አንድ ዓይነት ፀሎት ፣ በአንድ ወቅት ፣ በአንድ ሥርዓት ፣ ለአንድ ዓላማ ያቀ ርባሉ ። ሁሉም ከልቡ በመነጨ ፍጹምነት በትህትና ለአላህ ታማኝነቱን የሚገልጽበት ፤ አንዱ በሌላው ላይ ልዕልናውንና የበላይነቱን የማያንፀባርቅ በት ፣ እኩል ሆነው የሚታዩበት መድረክ ነው ።

4.3. ሀጅ ሙስሊሞች ለአላህ የገቡትን ቃል ኪዳን የሚያድሱበትና እርሱን ለማገል ገል ቁሳዊ ጥቅማቸውንም ለመተው ዝግጁ መሆናቸውን የሚያረጋግጡበት ነው ።

4.4. ሀጅ ነቢዩ ኢብራሂምና ልጃቸው ነቢዩ ኢስማዒል (የአላህ ምህረት ለሁለቱም ይድረስና) በመሬት ላይ አላህን ለማምለክ የመጀመሪያው ቤት ወደ ሆነው "ካዕባ" ለመጀመሪያ ጊዜ ተጉዘው በመድረስ ከአላህ ታዘው ያደረሱትን ፀሎት ማስታወሻና አጋጣሚውን የምናከብርበት ነው ።

4.5. ሀጅ ሰዎች በሙሉ በእኩልነት ፈጣሪያቸው ፊት በመቆም የመጨረሻ ውሳኔ ያቸውን የሚጠባበቁበትን ፣ ሰዎች በዘር ፣ በነገድና በጎሣ ለመበላለጥ የማይ ቃጡበትን ፣ በቂያማሕ (በምፅዓት) ቀን የሚደረገውን ታላቅ ስብሰባ የሚያስ ታውስ ነው ። እንዲሁም ሀጅ በዓለም ከሚገኙ ሥፍራዎች በሙሉ ፣ ከነቢዩ ኢብራሂም (ዓለይሂ አሰላም) ጊዜ ጀምሮ መካሕ ብቻ የአንድ አላህ ማምለኪያ ማዕከል እንድትሆን መመረጡዋንና የአንድ አላህ ማምለኪያ ንጹሕ የሆነ

ዲን የእስላም ማዕከል ሆና እስከ ዓለም ፍጻሜ የምትቀጥል መሆኑዋን አስተ ዋሽ ነው ።

4.5. የሀጅን ሥርዓት በማከናወን በቀላሉ ሊታዩ የሚችሉት ፍሬ ነገሮች እንኳ ቢጠቀሱ ፣ ሥርዓቱ መንፈሳዊ ብልጽግናን ፣ በሞራል እንደገና መታጠትን ፣ ለአላህ የሚኖረን ፍጹምነትና ለሥነ ሥርዓት የመገዛት ልምዳችን እጅግ የሚዳብርበት ፣ ስለ ሰው ልጆች ደህንነት ያለን ሰብአዊ ስሜት የሚቀሰቀስበት ፣ ከአላህ የሚሰጥ የንቃት ትምህርት የሚገበይበት ፣ እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉት ቁም ነገሮች በሙሉ ከእስላም ዲን መሠረታዊ ሕጎች አንዱ ከሆነው በሀጅ ሥር ተጠቃለው ይገኛሉ ።

4.7. ሀጅ ሌሎች ዒባዳዎች ጠቅልለው ያልያዙትን ቁም ነገር ይዞዋል ። በመሠረቱ ማንኛውም ዒባዳ ግዴታ የሚሆንበት ምክንያት ፣ ወይ ለሚመለከው ፈጣሪ ጌታ መብቱ በመሆኑ ከእርሱ በመታዘዙ ምክንያት ፣ ወይ ፈጣሪ ለሰጠው ፀጋ ምስጋና ለማድረስ ነው ። የሀጅ ሥርዓት ሁለቱንም ምክንያቶች ያጠቃለለ ነው ። ሀጅ ምዕመናኑ ከመዘባነንና የበላይነት ስሜታቸውን ከማንፀባረቅ ስሜታቸው ተወግደው ትሕትናን እንዲያሳዩ ፣ የታዘዙበትን "ኢሀራም" (ከወገብ በታች የሚሸረጥና ከወገብ በላይ እንደ ነጠላ የሚደረብ ያልተሰፋ ሁለት ብትን ነጭ ጨርቅ ነው ፤) ሲለብሱ ፍጹም በሆነ ታዛዥነትና የበታችነት ስሜት እንዲገኙ ያደርጋል ። እንዲሁም ሌሎች የዒባዳ ዘፍፎች ወይ በግለሰቡ አካል ወይ በገንዘቡ የሚወጡ ግዴታዎች ሲሆኑ ሀጅ ግን ሁለቱንም ያጠቃልላል ። ይሄውም ሀጅ ግዴታ የሚሆነው ጤናማ የሆነና ለአቅመ አዳም የደረሰ ሰው ገንዘብ ሲያገኝ ብቻ ነው ። እነዚህ ሁኔታዎች ሲሟሉ ለሀጅ የተነሳው ምዕመን ሙሉ ጤንነትን ለመሰለ ፀጋና ለተሰጠውም የሀብት ፀጋ አላህን ለማመስገን ወደ መካሕ ተጉዞ የሀጅን ሥርዓት በመከተል ልባዊ ምስጋናውን የሚያቀርብበት መድረክ መሆኑ ነው ።

## 5. <u>የሀጅ ወራትና ሀጅ ግዴታ የሚሆንባቸው ሁኔታዎች ፤</u>

5.1 የሀጅ ወራት ፣ (አሽሑሩል ሀጅ) "ሸዋል ፣ ዙልቂዕዳሕ ፣ ዙል ሂጃሕ" የሚባሉት ወራት ናቸው በሚል የዲኑ ምሁራን በሙሉ የተስማሙ ሲሆን ፣ ኢማም ማሊክና ጥቂት ዓሊሞች የ"ዙልሒጃሕ" ወር በሙሉ "አሽሐሩል ሀጅ" ነው ሲሉ ፣ ኢብኒ ዑመር ፣ ኢብኒ ዓባስ ፣ ኢብኒ መስዑድ ፣ ኢማም አቡ ሀኒፋ ፣ ሻፌዒና አሀመድ ከ"ዙልሂጃሕ" የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ብቻ ነው ብለዋል ።

5.2 የእስላም ዲን ምሁራን "ሸሩጡ ወጂቢ አልሀጅ" (ሀጅ ግዴታ የሚሆንባቸው ቅድመ ሁኔታዎች) የሚከተሉት ናቸው ብለዋል ፤

5.2.1 ሙስሊም መሆን ፤

5.2.2 ለአቅመ አዳም መድረስ ፤

5.2.3 የአእምሮ ጤንነት መሟላት ፤ (እብድ ፣ ንክ አለመሆን) ፤

### 5.2.4 ነጻ መሆን ፥ (ለሰው ባሪያ አለመሆን) ፥

### 5.2.5 የችሎታ መኖር ፥ (የገንዘብና ፥ የጤንነት ችሎታ)

እነዚህ አምስት ሁኔታዎች ተሟልተው እስካልተገኙ ድረስ በአንድ ሰው ላይ ሀጅ ግዴታ አይሆንም ። ከአምስቱ ሁኔታዎች ውስጥ የመጀመሪያዎቹ ሶስቱ ሁኔታዎች ለማንኛውም የዒባዳ ዘርፎች ግዴታነት ቅድመ ሁኔታ ናቸው ። የሀጅ ጉዞና ሥርዓት ፥ ጊዜን የሚጠይቅ በመሆኑና በባርነት ያለ ሰው ጊዜውን ለጌታው ከማዋል ሊወጣ ስለማይችል የሀጅ ግዴታ አይኖርበትም ። የችሎታው መኖር ደግሞ ለጉዞው ስንቅና የመጓጓዣ ወጭ ፥ ከሀጅ እስኪመለስም ለቤተሰቡ (ለሚስቱና ለልጆቹ) የቀለብ ግዴታ ስላለበት የቀለብ ወጭን ፥ ጉዞውንና የሀጅ ን ሥርዓት ለመከታተልም የአካል ብቃትን ፥ ስለሚጠይቅ ፥ ለሀጅ ጉዞ መንገዱ ከአደጋ ነጻና አስተማማኝ መሆን ስላለበት ፥ የችሎታ መኖር እነዚህን ሁኔታዎች በሙሉ የሚያጠቃልል ስለሆነ እስካልተሟሉ ድረስ የሀጅ ግዴታ አይኖርም ።

## 6. “እርካኑ አልሀጅ” የሀጅ መሠረታዊ ግዴታዎች

ሀጅ ከመሠረታዊ የእስላም ሕጎች አንዱ በመሆኑ ሁኔታዎች በመሟላታቸው ግዴታው ከወደቀበት በኋላ ግዴታውን ባለመቀበል የማይፈጽም ሰው ሙስሊም ሊሆን እንደማይችል ሁሉ ፥ የሀጅን ግዴታ ለመወጣት የሚነሳም ሰው መሠረታዊ የሆኑትን የሀጅ ግዴታዎች “አርካኑል ሀጅን” አውቆ እስካልተወጣ ድረስ የሀጅን ሥርዓት እንደፈጸመ አይቆጠርም ።

“አርካኑል ሀጅ” የሀጅ መሠረታዊ ግዴታዎች አምስት ናቸው ፤ እነሱም ፤

ሀ/ “አልኢህራሙ ሚኒል ሚቃት ፤” ይህም ማለት በሀጅ ወራት ለሀጅ ጉዞ የተነሣ ሰው ለሀጅ ሥርዓት መነሻ ሆነው የተወሰኑት ሥፍራዎች ላይ ሲደርስ ለሀጅ ሥርዓት የተወሰኑ “የኢህራም” ልብሶችን መልበስ ፤

ለ/ ከዕባን “ጠዋፍ” ማድረግ ፤ ይህም ሥርዓቱን ጠብቆ ቤቱን ለሰባት ጊዜ መዞር ማለት ነው ፤

ሐ/ “ሰፋ እና መርዋህ” በተባሉት ኮረብታዎች መሐል “ሠዕይ” ማድረግ ፥ ይህም ሥርዓቱን ጠብቆ እንደሁኔታው በተወሰኑ ሥፍራዎች እርምጃን በማንሣት መጓዝ ፥ ምልክት በተደረገላቸው ሥፍራዎች መሐል ደግሞ ከሩጫ መልስ ፥ ፈጠን ባለ መልክ መጓዝን ያመለክታል ፤

መ/ ዓረፋህ በሚባል ጋራ ላይ “የውቁፍን” ሥርዓት ማሟላት ፤ (ይህም በጋራው ላይ ተገኝቶ ቆሞ የተወሰነ ሥርዓትን ጠብቆ መጸለይን ያመለክታል) ፤

ሠ/ “ፀጉርን የመላጨት ወይም የማሣጠር” ሥርዓትን ማሟላት ናቸው ። እነዚህ የሀጅ መሠረታዊ ግዴታዎች ስለሆኑ በትክክል እስካልተፈጸሙ ድረስ ድካሙ ከንቱ ይሆናል ። ስለዚህ ዝርዝር ሁኔታዎችን በተቻለ መጠን አሳጥረን በማቅረብ አንባቢ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ እንሞክራለን ። ዳሩ ግን በየደረጃውና በየሥፍራው መደረግ የሚገባቸው ምርጥ “ዱዓአች”

ትርጉም ፥ (አቤት ! ጌታዬ ሆይ አቤት ! አቤት አጋር የሌለህ ጌታ ነህና አቤት ! ምስጋና ላንተ ይገባል ፤ ፀጋም ያንተ ናት ፤ መንግሥት/ንግሥና ፤ ያንተ ናት አጋርም የለህ !) እንደ ማለት ነው ።

6.1.4. "ኢህራም" ያደረገ ሰው ከሴት ለግብረ ሥጋ ከመገናኘት ፥ ሽቶ ከመቀባት ፥ የተሰፋ ልብስን ከመልበስ ፥ ጥፍርን ከመቁረጥ ፥ ፀጉርን ከመላጨት ከማሳጠር፡ ወይም ከመንቀል ፥ የምድር እራዊትና አዕዋፍን ከማደን ፥ ከፀያፍ አነጋገር ፥ አላሕ (ሱብሃነሁ ወተዓላ) የከለከላቸውን ወሰኖች ከማለፍ ፥ ከጭቅጭቅ ከንትርክና ከፀብ እንዲወገድ የግዴታ ያስፈልጋል ።

6.1.5. "ኢህራም" ላደረገ ሰው ከጊዜ ወደ ጊ ዜ "ተልቢያ" አቤት ጌታዬ ሆይ ! የማለቱን ሥርዓት ማደስና መደጋገሙ እጅግ ያመረጣል ፤ በተለይም ከጓደኞቹ ጋር ሲገናኝ ፥ ለሶላት ሲነሳ ፥ ሁኔታዎች ሲለዋወጡ (ለምሳሌ ሲነጋና ሲመሽ ፥ ንፋስ ሲነፍስ ወዘተ - -) ድምጽን ከፍ በማድረግ "ተልቢያህ" ማድረግ ይመረጣል ።

6.1.6. አንድ ጊዜ ለ"ኢህራም" ኒያህ ከተደረገ (ከተወሰነ) ለዚያ ውሳኔ መገዛት ያስፈልጋል ።

(እዚህ ላይ መብራራት ያለበት ጉዳይ ለ"ኢህራም" ኒያህ" ሲደረግ በተናጠል ወይም በአንድነት ለማድረግ ይቻላል ተብሎ ከላይ የተጠቀሰው ነጥብ ነው ። ኢህራም በሶስት ዓይነት ኒያህ ተደርጎለት ሊታሰር ይችላል ።

፩ኛ/ "አልኢፍራድ" ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን ፥ ይህም ለሀጅ ብቻ ኢህራም ማድረገን ያመለክታል ፤

፪ኛ/ "አትተመቱዕ" በመባል ይታወቃል ፤ ይህም በቅድሚያ ለዑምራህ ኢህራም በማድረግ ሥርዓቱን ካጠናቀቁ በኋላ የሀጅ ወራት ሲገባ ለ"ሀጅ" ለብቻው ኢህራም ማድረገን ያመለክታል ።

፫ኛ/ "አልቂራን" በመባል የሚታወቅ ሲሆን ፥ ይህም ለ"ሀጅና" ለ"ዑምራህ" (በአንድነት "ኢህራም" ማድረገን ያመለክታል ።) ከነዚህ ሶስት አማራጮች የሚሆነውን መርጦ የወሰነና "ኢህራም" ያደረገ ሰው በውሳኔው መጽናት ይኖርበታል ።

ዳሩ ግን በተለያዩ ምክንያቶች ውሳኔውን ለመለወጥ ከፈለገ የሚከተለውን ገደብ ማስታወስ አለበት ።

6.1.6.1 ኢህራሙን በ"አትተመቱዕ" አድርጎ ያለ ሰው አሁን ለዑምራና ለሀጅ አብሮ በ"አልቂራን" ኢህራም ለማድረግ ከፈለገ የጠዋፍ ሥርዓትን ከመጀመሩ በፊት ለመለወጥ ይችላል ፤

6.1.6.2 በ"አትተመቱዕ" ኢህራም ያደረገ ሰው "በአልኢፍራድ" ኢህራም ለማድረግ ከፈለገ ፥ ወይም "በአልኢፍራድ" ኢህራም ያደረገ ሰው "በአትተመቱዕ" ኢህራም ለማድረግ ከፈለገ ፥ ወይም "በአልቂራን" ኢህራም ያደረገ ሰው ነጣጥሎ ኢህራም ለማድረግ ከፈለገ አይችልም ።

## 6.2. ከዕባን "ጠዋፍ" የማድረግ ግዴታ

ይህን የሀጅ ሁለተኛ መሠረታዊ ግዴታ ለመወጣት የተነሳ ሰው "ከዕባን" ጠዋፍ አደርጋለሁ ብሎ ኒያህ በማድረግ ከ"ሀጀሩል አስወድ" (ከዕባ ላይ ከሚገኘው ጥቁር ድንጋይ ሥፍራ) በመነሳት "ከዕባን" ለሰባት ጊዜ ለመዞር ሥርዓቱን አውቆ መዘጋጀት ይኖርበታል ። ከሥርዓቱ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ፤

6.2.1. ለጠዋፍ የተነሳ ሰው ከትንሹና ከትልቁ "ሐደስ" (የንዕሕና ማጣት ሁኔታ) የጠራ መሆን ፣ ሰውነቱና ልብሱ ከ"ነጃሳ" (ከሽንትና ሠገራ ወዘተ - - ንክኪት) የጠራ መሆን ፣ ከሰውነቱ ክፍል መሸፈን የሚገባውን መሸፈን ፣ በቂ ምክን ያት ከሌለው በቀር በእግሩ መጓዝ ፣ እያንዳንዱን የጠዋፍ ዙር ጉዞ ከ"ሀጀሩል አስወድ" ሥፍራ መጀመር ፣ ጉዞውን ሲጀምር ሁለት እጆቹን አለማነባበር ፣ ወንዱ የመጀመሪያዎቹን የከዕባሀ ሶስት የግድግዳ ዙር ከሩጫ መለስ ባለ ፍጥነት መጓዝ ፣ የሚያስፈልግ መሆኑን አውቆ መፈጸም አለበት ፤

6.2.2. ለጠዋፍ ጉዞ የተዘጋጀ ሰው ለጠዋፉ "ኒያህ" ውሳኔ ማድረግ አሶበት ። እርሱም

| | |
|---|---|
| አልላሁምማ ኢንኒ ኡሪዱ ጠዋፍ | اللهـم إني أريد طواف |
| ቤይቲካ ፈየሲርሑ ሊ ወተቀበልሁ | بيتك ، فيسره لي وتقبله |
| ሚንኒ ፣ ሱብዓተ አሽዋጢ ጠዋፍ አልሀጅ | مني ، سبعة أشواط طواف |
| አውል ዑመምረቲ ፤ አዊል ዊዳዕ | الحج أو العمرة أو الوداع |

ትርጉም ፣ /ጌታ ሆይ እኔ ቤትህን ለ"ሀጅ" ወይም እንደ ሁኔታው ለ"ዑምራህ" ወይም ለ"መሰነባበት" ለጠዋፍ ሰባቴ ለመዞር እፈልጋለሁና አቅልልኝ ፤ ከእኔም ተቀበለው ፤) ማለት ይሆናል ።

"ኒያህ" (ውሳኔውን) በዚህ መልክ ካደረግህ በኋላ ከቻልክ "ሀጀሩል አስወድን" ጠጋ ብለህ ሳም ፤ ካልቻልክም በእጅህ ወደ እሱ በማመልከት እጅህን መልሰህ ሳም ፤ ከዚያም የሚከተለውን በቃል ድገም ፤

| | |
|---|---|
| "ቢስሚልላሂ ወላሁ አክበር | بسـم الله والله أكبر |
| ወሊላሂል ሀምድ ፤ አልላሁማ ኢማነን ቢክ ፤ | ولله الحمد ، اللهـم إيمانا بك |
| ወተሰዲቀን ቢኪታቢክ ፤ | وتصديقا بكتابك ، |
| ወወፋአን ቢዓህዲክ ፤ | ووفاءا بعهدك |
| ወትቲባዓን ሊሱነቲ ነቢይካ ሙሐመድ ፤ | واتباعا لسنة نبيك محمد ، |
| ሰለ አላሁ ዓለይሀ ወሠለም ። | صلى الله عليه وسلـم |

የፀሎቱ መልዕክት ሲተረጐም ፣ "በአላህ ስም እጀምራለሁ ፤ አላህ ታላቅ የሆነ ጌታ ነው ፤ ምስጋናም ለአላህ ይገባል ፤ ጌታዬ ፤ በአንተ ባለኝ ፍጹም እምነት የወረደውን መጽሐፍ ዕውነተኛነት በማረጋገጥ ፣ ላንተ የገባሁትን ቃል ኪዳን ለማክበር ፣ የአንተ ነቢይ የሆኑት ሙሐመድን (ሰ አ ዓ ወ) ምሳሌነት ለመከተል ነው ፤ ማለት ይሆናል ።

6.4.1. “ዑምራን” በማጠናቀቁ ከ“ኢህራሙ” የወጣ ሰው የሀጅን ሥርዓት ለመጀመር ወደ ዓረፋሕ ከመጓዙ በፊት ኢህራሙን ማደስ ይኖርበታል ።

6.4.2. ለሀጅ ኒያህ በማድረግ ኢህራም ከተደረገ በኋላ በዙልሂጃሕ ወር ፰ኛ ቀን ከፈጅር ሶላት በኋላ ወደ ሚና ጉዞ ተጀምሮ ከዓስር ሶላት በፊት ሚና ተገብቶ ይታደራል ። በማግስቱ ፀሐይ ከመውጣቱዋ በፊት የሚከተለው ፀሎት እየተደረገ ወደ ዓረፋሕጋራ ጉዞ ይጀመራል ።

| | |
|---|---|
| “አልላሁምመ ኢለይካ ተወጅጀሕቱ ፣ | اللهم إليك توجهت |
| ወኢላ ወጅሒከል ከሪሚ አረድቱ ፣ | والى وجهك الكريم أردت |
| ፈጅዓል ዘንቢ መግፉራ ፣ | فاجعل ذنبي مغفورا |
| ወሀጅጂ መብሩራ ፣ | وحجي مبرورا |
| ወርዙቅኒ ወላ ቱኸይብኒ | وارزقني ولا تخيبني |
| ኢንነከ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲር ። | إنك على كل شيء قدير |

የመልዕክቱ ትርጉም “ጌታዬ ሆይ ! ፊቴን ወዳንተ አዞርኩ ፣ ለጋስ የሆነ ገጽታህንም ፈለግሁ ፣ (ተመኘሁ) ኃጢአቴን የሚሠረዝ (ይቅር የሚባል) አድርግልኝ ፣ የሀጅ ሥራዬንም ተቀባይነት ያለው አድርግልኝ ፣ ከልግስናህ (የዕለቱ ጉርሴን) ስጠኝ ፣ አትመልሰኝ ፣ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነህና ።” ማለት ይሆናል ።

ወደ ዓረፋሕ ጋራ የሚጓዝ ምዕመን “ነሚራሕ” የምትባል ሥፍራ ላይ ሲደርስ እስከ ዙሕር ሶላት ጊዜ ያርፋል ። ከዚያም ለ“ዓረፋሕ” ውቁፍ” ይታጠባል ፣ ወደ መስጂድ በመሄድ የዙሕርና የዓስርን ሶላት ለመስገድ በኢማም እየተመራ ዓስርን ከጊዜው በማስቀደም በዙሕር ጊዜ ሁለቱንም በሁለት በሁለት ረከዓ አሳጥሮ ይሰግዳል ። ከዚያ በኋላ ወደ “ዓረፋሕ” ጋራ ጉዞውን በመቀጠል “ጀበል አልረህማሕ” የምትባል ጋራ መታየት ስትጀምር የሚከተለውን ፀሎት ያደርጋል ፣

| | |
|---|---|
| “አልላሁምመ አግፍርሊ ወቱበ ዓሌይ ፣ | اللهم اغفر لي وتب عليّ |
| ወአዕጢኒ ሱእሊ ፣ ወወጅሕ ሊየል ኸይር ፣ | واعطني سؤالي ووجه لي الخير |
| አይነማ ተወጀሕቱ ፣ ሱብሃን ልላህ | أينما توجهت، سبحان الله |
| ወልሀምዱ ሊላህ ፣ ወላ ኢላሃ ኢልላልላሕ ፣ | والحمد لله ولا إله إلا الله |
| ወልላሁ አክበር ፣ | والله أكبر |

መልዕክቱ ፣ ጌታዬ ሆይ ! ራራልኝ ፣ ይቅር በለኝ ፣ የጠየቅሁትን ስጠኝ ፣ ወደትም ዞርኩ መልካሙን ነገር ወደኔ ምራልኝ ፣ የጠራህና ምስጋና የሚገባህ አላህ ነህና ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም ፣ አላህ ታላቅ ነው ።” ማለት ይሆናል ።

ከዚህ ሥፍራ ጀምሮ ፀሎትን ሳይሰለቹ ማብዛት ያስፈልጋል ። “ተልቢያህ” “ተሕሊል” “እስትግፋር” “ተክቢር” የመሳሰሉትን በተቻለ መጠን አለማቋረጥ ይጠቅማል ፣ በተለይም በ“ዓረፋሕ” ጋራ ላይ ከቆሙ በኋላ የሚከተለውን ፀሎት ማድረግ ይመረጣል ።

| | |
|---|---|
| “አልላሁምመ አቲና ፊ አዱንያ ሀሰነሕ ፣ | ربنا آتنا في الدنيا حسنة |
| ወፊ አልአኺረቲ ሀሰነሕ ፣ | وفي الآخرة حسنة |
| ወቂና አዛበ አንናር ፣ | وقنا عذاب النار |
| አልላሁምመ ኢንኒ ዘለምቱ ነፍሲ ፣ | اللهم إني ظلمت نفسي |
| ዙልመን ከሢረን ከቢራ ፣ | ظلماً كثيراً كبيراً |
| ወላ የግፊሩ ዝዙኑበ ኢልላ አንተ ፣ | ولا يغفر الذنوب إلا أنت |
| ፈግፍርሊ መግፊረተን ሚን ዒንዲከ ፣ | فاغفر لي مغفرة من عندك |
| ወርሀምኒ ረሀመተን አስዓዱ ቢሓ ፣ | وارحمني رحمة أسعد بها |
| ፊ ድዳሬይን ፣ ወቱብ ዓሌየ ፣ | في الدارين ، وتب علىّ |
| ተውበተን ነሱሆን ላ አንኩስሓ አበዳ ፣ | توبة نصوحاً لا أنكثها أبداً |
| ወአልዚምኒ ሰቢለል ኢስቲቃመሕ ፣ | وألزمني سبيل الإستقامة |
| ላ አዚጉ ዓንሓ አበዳ ፣ | لا أزيغ عنها أبدا |

መልዕክቱ ፣ “ጌታዬ ሆይ ! በዚህ ዓለምና በመጭውም ዓለም መልካሙን ነገር ስጠን ፣ ከገሐነም እሳት ሰውረን ፣ ጌታዬ ሆይ ! ራሴን ብዛትና ክብደት ያለው በደል በድያለሁ ፣ ይሁንና በደሌን ካንተ በቀር ይቅር የሚል የለም ፣ ካንተ ዘንድ በርህራሄህ ይቅር በለኝ ፣ በሁለቱም ዓለም ደስታ የማገኝበትን ምህረት ማረኝ ፣ ወደ ቀናው መንገድ በጸጸት እንድመለስና ዘለዓለም ጸጸቴን እንዳላፈርስ እርዳኝ ።” ማለት ይሆናል ።

በዓረፋሕ ጋራ ላይ ቆሞ የመፀለዩ ሥርዓት በዙልሂጃሕ ዘጠነኛ ቀን ከሰዓት በኋላ ልክ ፀሐይ ማዘንበል ስትጀምር ተጀምሮ በማግሥቱ ፀሐይ መውጫ ሰዓት ላይ ያበቃል ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ለውቁፍ “ዓረፋሕ” ጋራ ላልደረሰ ሰው ግዴታው አይወርድለትም ።

በዓረፋ ጋራ ላይ ከቆሙ በኋላ ሳይታክቱ ቆሞ ያለማቋረጥ ፀሎት ማድረስ ያስፈልጋል ። ለዚህ የተመረጠው ፀሎት በጣም ረዥም ሲሆን ፣ ከመጽሐፍ ለማግኘት ይቻላል ።

6.4.3. የዓረፋሕ ፀሎት እንዳበቃ መግሪብ ሳይሰገድ ወደ ኋላ በማዘግየት ወደ “ሙዝደልፋሕ” የመልስ ጉዞ ይደረጋል ። “ሙዝደልፋሕ” በ‘ዓረፋሕና’ በ“ሚና” መሐል ያለች ለጥ ያለች ሜዳ ስትሆን በውስጡዋ “መሽዓረል ሀራም” ከተባለው መስጊድ ሌላ ምንም ቤት የለም ።

“ሙዝደሊፋሕ” እንደተደረሰ የመግሪብና ዒሻእ ሶላት በአንድ ወቅት የዒሻእ ሶላት አራት ረከዓትን ወደ ሁለት ረከዓሕ በማሳጠር ይሰገዳል ።

በ“ሙዝደሊፋሕ” ትናንሽ የባቄላ ፍሬ የሚያካክሉ ጠጠሮች በብዛት ስለሚገኙ በ“ሚና” ለሚካሄደው የድንጋይ ጠጠር ውርወራ ሥርዓት አራት ቀን ለሚቆይ ፸ ጠጠር ፣ ሶስት ቀን ለሚቆይ ፵፱ ጠጠር ፣ የሚያስፈልግ ስለሆነ ከዚሁ ሥፍራ ይሰበሰባል ፣ ከዚህ ሥፍራ ጠጠር ይዞ ለመሄድ ለማይፈልግ ለመጀመሪያው ቀን ጠጠር ውርወራ (ለጀምረቱ አልዓቀባሕ አልኩብራ)

"በጀምረቱል ዓቀባ" ሰባቱን ጠጠር ከወረወሩ በኋላ "ተልቢያሕ" ማድረግ ይቋረጣል ። ከዚያም "ሐድይ" (ወደ አላህ ለመቅረብ የሚታረድ የበሬ ፣ የበግ ወዘተ - - ምጽዋት) ይታረዳል ። ኢማም ሻፊዒ አህመድ በተጨማሪም ለ"ኡድሂያ" (ለአረፋሕ በዓል ማስታወሻ ለመስዋዕትነት የሚታረድ በግ ወዘተ የሚታረደው ይታረዳል ።

7. <u>ፀጉርን የመላጨት ወይም የማሳጠር ግዴታ</u>

ከእርዱ ሥርዓት በኋላ ፀጉርን መላጨት ወይም ማሳጠር አምስተኛው የሀጅ መሠረታዊ ግዴታ ነው ። የሀጅን ሥርዓት የሚያከናውን ሰው ሌሎችን ሥርዓቶች ካጠናቀቀ በኋላ ጊዜውን ጠብቆ ፀጉሩን የመላጨት ወይም የማሳጠር ግዴታ አለበት ።

ኢማም ማሊክ በኢህራም ምክንያት የተከለከሉ ነገሮች በሙሉ ከሴትና አደን በስተቀር የጀምረቱል ዓቀባሕ የጠጠር ውርወራው ሥርዓት ሲያበቃ ይፈቀዳል ሲሉ ፣

"ኢማም አቡ ሀኒፋ ግን የፀጉር መላጨት ወይም ማሳጠር ሥርዓት ሲጠናቀቅ ነው የሚፈቀደው ይላሉ ፣

ኢማም ሻፊዒና አህመድ ግን ከሚከተሉት ሶስት ሥርዓቶች ሲጠናቀቁ ብቻ ነው የሚፈቀደው ይላሉ ። ሶስቱ ሥርዓቶች ፣

፩/ የጀምረቱል ዓቀባሕ የጠጠር ውርወራ ሥርዓት ሲጠናቀቅ ፣

፪/ የፀጉር መላጨት ወይም ማሳጠር ሥርዓት ሲጠናቀቅ ፣

፫/ "ጠዋፈል ኢፋዳሕ" (ጠዋፈ አዞያራሕ) ሲደረግ ።

8. የሀጅን ሥራ የሚከታተል ሰው በዒድ ቀን የሚከተሉት ተግባራት መፈጸም ያለባቸው መሆኑን ያስታውስ ፣

፩/ ከንጋት በኋላ በጀምረቱል ዓቀባሕ ሰባት ጠጠሮችን መወርወር ፣

፪/ "ፈድየሕ" ማረድ ፣

፫/ ፀጉርን መላጨት ወይም ማሳጠር ፣

፬/ ከተቻለ ወደ መካሕ ተጉዞ "ጠዋፈል ኢፋደህ ወይም ጠዋፈ አዚያረሕ" ተብሎ የሚጠራውን ካዕባን መዞር ፣

፭/ ወደ ሚና ለአዳር ተመልሶ ካልቸኮሉ ለአያሙ ተሽሪቅ (ከዒድ በኋላ ያሉትን ሶስት ቀናት) መቆየት ፣ ከቸኮሉም ሁለት ቀናት መቆየት ፣

ሁለት ቀን ለሚቆዩም ሆነ ሶስት ቀን በሚና ጠጠር ለመወርወር የሚቆዩት የአወራወሩ ሥርዓት እንደ መጀመሪያው ቀን ሆኖ ውርወራው የሚጀመረው ከቀትር በኋላ ይሆናል ፣ በየቀኑ የመጀመሪያው ሰባት ጠጠር እንደተወረወረ ፊትን ወደ ከዕባህ አቅጣጫ በማዞር "አልሀምዱ ሊላህ ፣ አላሁ አክበር ፣ ላኢላሃ እልላ ልላህ ፣ አልላሁምመ ሰልሊ ዓላ ሰይድና መሀመድ" እያለ የፈለገውን ፀሎት ያደርሳል ። የዚህ ፀሎት ጊዜ "የበቀራሕ ምዕራፍ በማንበብ የሚፈጀውን ያህል " በግምት አንድ ሰዓት ያሕል መሆን ይኖርበታል ።

ሁለተኛውም ሰባት ጠጠር ሲወረወር ይሄንኑ ያህል በመቆም ከላይ እንደ
ተገለጸው ይፀለያል ፤ ከሶስተኛው ሰባት ጠጠር ውርወራ በኋላ የትም ለመ
ሄድ ይቻላል ።

በዚህ ዓይነት በሁለቱ ወይም በሶስቱ ቀናት የሚወረወረው ጠጠር ተወርውሮ
ካበቃ በኋላ "ኢህራም" ለሀጅና ለዑምራህ አብረው ያደረጉ ፣ ወይም መጀ
መሪያ ለዑምራህ ብቻ አርገው ፣ ዑምራን ከጨረሱ በኋላ ለሀጅ ያደረጉት
እዚህ ላይ የሀጅና ኡምራህ ግዴታቸውን ይወጣሉ ። ለ"ሀጅ" ብቻ "ኢህ
ራም" በማድረግ የ"ዑምራን" ሥርዓት ያቆዩት ግን ከዚህ በኋላ "ለዑምራ
ራሕ" እንደገና "ኢህራም" በማድረግ የ"ዑምራን" ሥርዓት ማጠናቀቅ
ይኖርባቸዋል ።

የዑምራሕ ሥርዓት "ኢህራም" <u>ጀዕራነሕ</u> በምትባል ሥፍራ በማድረግ
ሰባት ጊዜ "ጠዋፍና" ሰባት ጊዜ "በሰፋና መርዋሕ" መሐል "ሠዕይ"
(መጓዝን) ያጠቃልላል ።

ከሀጅና ዑምራህ ሥርዓት በኋላ ወደ መዲና በመጓዝ የነቢዩን መሐመድ
መስጅድና መቃብር መጎብኘት (ዚያራሕ) ማድረግ በጣም የተወደደ ተግባር
በመሆኑ የሀጅን ሥርዓት ያጠናቀቁ ሁሉ ወደዚያ በማምራት ፀሎት ያደርሳሉ ።

ግብራሪያና ተግባራዊ ምሳሌነትን (ሀዲስን) ያጠቃልላል ። አላህ (ሱ ወ) ነቢያችን (ሰ አ ዓ ወ) ለፍጥረታት ሁሉ ምሳሌነት ያላቸው መሆኑን ሲመሰክር ላቸው እንዲህ ይላል ።

وَإِنَّكَ لَعَلَىٰ خُلُقٍ عَظِيمٍ القلم ٤

"አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ ።" (ም ፷፰ ቁጥር ፬)

እንዲሁም ሙሐመድ (ሰ አ ዓ ወ) የሚናገሩት እንዲሁ በዘፈቀደ የመጣላቸውን ሳይሆን በአላህ (ሱ ወ) እየተመሩ መሆኑን ሲያረጋግጥላቸው እንዲህ ብሎኋል ፤

وَمَا يَنطِقُ عَنِ ٱلْهَوَىٰٓ ۝٣ إِنْ هُوَ إِلَّا وَحْىٌ يُوحَىٰ النجم ٣-٤

"ከልብ ወለድም አይናገርም ። እርሱ (ንግግሩ) የሚወርድ ራእይ እንጂ ሌላ አይደለም ።" (ም ፶፫ ቁጥር ፫-፬)

ስለዚህ ነው ነቢያችን (ሰ አ ዓ ወ) ያዘዙትን መቀበልና መፈጸም ፤ ከከለከሉትም መከልከል አለብን የሚባለው አላህ (ሱ ወ) በግልጽ በቁርአን እንዲህ ሲል ደንግጎኋል ። "መልዕክተኛውም የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት ፤ ከርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ - - -" (ም ፶፱ ቁጥር ፯)

وَمَآ ءَاتَىٰكُمُ ٱلرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَىٰكُمْ عَنْهُ فَٱنتَهُوا۟ الحشر ٧

ከላይ እንደተገለጸው በቁርዓንና በሀዲስ አስከተመራን ድረስ ግራኪና እጅግ የሚያስቀና የእስላም አኗኗርን ለመኖር እንችላለን ። ዓለማዊና መንፈሳዊ ሕይ ወታችንም እድገት እንደሚያገኝና የተሳካ እንደሚሆንም ዋስትና ይኖረናል ። ታዲያ ይህን ዋስትና ለማግኘት የምንችለው የዲኑን መመሪያ በከፊል ተቀብለን ሥራ ላይ በማዋል ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ተቀብለን ስንገለገልበት መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል ። ስለዚሁ ነጥብ አላህ ሲያስታውሰን እንዲህ ይላል ።

أَفَتُؤْمِنُونَ بِبَعْضِ ٱلْكِتَٰبِ وَتَكْفُرُونَ بِبَعْضٍ ۚ فَمَا جَزَآءُ مَن
يَفْعَلُ ذَٰلِكَ مِنكُمْ إِلَّا خِزْىٌ فِى ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا ۖ وَيَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ
يُرَدُّونَ إِلَىٰٓ أَشَدِّ ٱلْعَذَابِ ۗ البقرة ٨٥

"- - በመጽሐፉ ከፊል ታምናላችሁን ? በከፊሉም ትክዳላችሁን ? ከናንተም ይህንን የሚሠራ ሰው ቅጣት በቅርቢቱ ሕይወት ውርደት እንጂ ሌላ አይደለም፤ በትንሣኤ ቀንም ወደ ብርቱ ቅጣት ይመለሳሉ ፤ - - -" (ም ፪ ቁጥር ፹፭)

## 3.2 የግልና የጋራ ጥረትን ማቀናጀት ማስፈለጉ

በእስላም ዲን ተመርቶ ውጤትን ለማግኘት የግልና የጋራ ጥረት ይጠይቃል ። አንድ ሰው በግሉ በሚያደርገው ጥረት የተወሰነ ውጤት እንደሚያገኝ አያጠያ ይቅም ። አላህ (ሱ ወ) ግንም ኅብረተሰብ ደግ ሥራ እስከሠራ ድረስ ወሮታ የሚ ያገኝበት መሆኑን ሲያረጋግጥ ትንዲህ ይላል ፤

مَنْ عَمِلَ صَٰلِحًا مِّن ذَكَرٍ أَوْ أُنثَىٰ وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَلَنُحْيِيَنَّهُۥ حَيَوٰةً طَيِّبَةً
وَلَنَجْزِيَنَّهُمْ أَجْرَهُم بِأَحْسَنِ مَا كَانُوا۟ يَعْمَلُونَ النحل ٩٧

በእርግጥ ሰውን ወደ ቀናው መንገድ ለመምራት በቅድሚያ ዲኑን ማወቅ ያስፈልጋል ። ለዚህም ነው ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.አ.ዓ.ወ.)የሚከተለውን የተናገሩት፣

﴿ طلب العلم واجب على كل مسلم ومسلمة ﴾

ትርጉሙ ፤ "የዲን ትምህርት መማር የእያንዳንዱ ወንድና ሴት ግዴታ ነው ።" ማለት ይሆናል ። ዳሩ ግን ሁሉም ሰው የዲንን ትምህርት አጠቃሉ ለማወቅ አይችልም ። እያንዳንዱ ሰው መሠረታዊ ሕጎችን አውቆ በተግባር ላይ ለማዋል የሚያስችለው ያህል ዕውቀት ካለው ለቀረው የዲን ትምህርት የተወሰኑ ምሁራን ኃላፊነቱን ከወሰዱለት ኃላፊነቱ ከእርሱ ይወድቃል ። የተወሰነ ነገር ስለዲኑ በማወቁ ምክንያት ብቻ ከጥሪ ተግባር ኃላፊነት ሊሸሽ አይችልም። የሚያውቀውን ያህል የማሳወቅ ግዴታ አለበት ።

የዚህ ጽሑፍ አንዱ ዓላማም አንባቢ ከጽሑፉ ያነበበውን በተራው ለሌላው እንዲያስተላልፍ ጥሪ ማድረግ ነው ። አንባቢ በቁጭት ሊገነዘበው የሚገባ ቁም ነገር ፤ ዝርዝሩን የዲን መመሪያ ቀርቶ ፣ መሠረታዊ የሆኑ የእስላም ሕጎችን ባለማወቅ የእስላምነት ግዴታቸውን እንኳ ለመወጣት ያልቻሉ ብዙዎች መኖራቸውን ነው ።

ዲንን ማወቅ ግዴታ ነው ሲባል ለማወቅ ያህል ብቻ ሳይሆን በተግባር ተርጉመን ውጤት ስናገኝበት ነው ። ዲኑን ያወቀ ሰው ምስጉንና ጠቃሚ የሆነውን ተግባር ከእርኩሱና ጎጂ ከሆነው ተግባር ስለሚለይ ለራሱም ተጠቅሞበት ሌሎችንም በዚሁ ለመምራት ይችላል ። የሙስሊምን ሕብረተሰብ ከሌላው የተለየ የሚያደርገውም አንዱ ቁም ነገር ይህን ኃላፊነት ለመወጣት መቻሉ ነው ። አላህ (ሱ ወ) እንዲህ ይላል ፤

كُنتُمْ خَيْرَ أُمَّةٍ أُخْرِجَتْ لِلنَّاسِ تَأْمُرُونَ بِٱلْمَعْرُوفِ وَتَنْهَوْنَ عَنِ
ٱلْمُنكَرِ وَتُؤْمِنُونَ بِٱللَّهِ ۗ آل عمران ١١٠

"ለሰዎች ከተገለጸች ሕዝብ ሁሉ ፣ በላጭ ሆናችሁ ፣ በጽድቅ ነገር ታዛላችሁ ፤ ከመጥፎም ነገር ትከለክላላችሁ ፤ በአላህም (አንድነት) ታምናላችሁ ፤" (ም ፫ ቁ ፻፲)

እንዲሁም በሌላ አንቀጽ አላህ (ሱ ወ) እንዲህ ይላል ፤

وَٱلْمُؤْمِنُونَ وَٱلْمُؤْمِنَٰتُ بَعْضُهُمْ أَوْلِيَآءُ بَعْضٍ ۚ يَأْمُرُونَ بِٱلْمَعْرُوفِ
وَيَنْهَوْنَ عَنِ ٱلْمُنكَرِ وَيُقِيمُونَ ٱلصَّلَوٰةَ وَيُؤْتُونَ ٱلزَّكَوٰةَ
وَيُطِيعُونَ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥٓ ۚ أُو۟لَٰٓئِكَ سَيَرْحَمُهُمُ ٱللَّهُ التوبة ٧١

"ምዕመናንና ምዕመናትም ከፊሎቻቸው ለከፊሉ ረዳቶች ናቸው ፤ በደግ ነገር ያዛሉ ፣ ከክፉም ይከለክላሉ ፤ ሶላትንም ይሰግዳሉ ፣ ዘካንም ይሰጣሉ ፤ አላህንና መልዕክተኛውንም ይታዘዛሉ ፤ እነዚያን አላህ በእርግጥ ያዝንላቸዋል ፤" (ም ፱ ቁጥር ፸፩)

የአንድ ምዕመን የእምነት ጥንካሬ የሚለካው በዲን የተከለከለውን እንዳይፈጽም ፣ የታዘዘውን ደግሞ ተግባር ላይ እንዲውል በሚያደርገው የትግል መጠን ነው ። ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ ዐ ዓ ወ) እንደ ተናገሩት "እርኩስ ነገር ሲሠራ ያየ በእጁ መከልከል አለበት ፤ ካልቻለ በቃሉ ፣ ይህንንም ካልቻለ በልቡ ያን ተግባር ማውገዝ አለበት ፤ ይህም (በማውገዝ ብቻ መወሰን) ፤ ደካማ የሆነ እምነት ነው ።"

ስለ መከልከልና 'ነዘዝ ሲነገር የአቀራረቡ ሁኔታ ወሳኝ ነው ። በቅድሚያ ያለ ክርክርና ተቃውሞ ተቀባይነት በሚያገኙ ጉዳዮች መጀመር ይጠቅማል ። ከፍተኛ የኃጢአት (የበደል) ዓይነቶችን ለመከልከልና ልንዘላቸው የማንችል ገጼታዎችን ለማስፈጸም በቅድሚያ መታገል ያስፈልጋል ። የሚያከራክሩ ነጥቦች ላይ ሃሳብ በመለዋወጥ ያለ ብዙ ጭቅጭቅ ሊፈጸሙ የሚችሉበት ሁኔታ ላይ ለመድረስ ለጊዜው ንትርኩን ማስወገድ ይበጃል ።

በግለሰብ ደረጃ ሊሠሩ የሚችሉ ብዙ ሥራዎችና ቁም ነገሮች ቢኖሩም የሰውን ልጅ ወደ ትክክለኛው ጎዳና የመምራት ሥራ ለግለሰቦች የሚተው ቀላል ተግባር አለመሆኑ ግልጽ ነው ። ሥራው የጋራ ጥረትን ይጠይቃል ። አላህ (ሰ ወ) በዚህ ተግባር መተጋገዝ የሚያስፈልግ መሆኑን ሲገልጽ እንዲህ ብሎ ያዛል ።

"በበጎ ነገርና አላህን በመፍራ ትም ተረዳዱ ፤ ግን በኃጢአትና ወሰንን በማለፍ አትረዳዱ ፤ አላህንም ፍሩ ፤ - - -" (ም ፭ ቁጥር ፪)

የጋራ ጥረትና ትብብርን ማግኘት የሚያስፈልገውን ያህል የመተባበሩንና የመተጋገዙን ስሜት ለመፍጠር በቅድሚያ በምዕመናን መሐል የፍቅርና የወንድማማችነት መንፈስ ሊፈጠር ይገባል ። አላህ (ሱ ወ) ምዕመናን ወንድማማቾች ናቸው ብሎ ያለውን በተግባር መተርጎም ያስፈልጋል ። የቁርአንን አንቀጽ እንጠቅሳለን ፤

إِنَّمَا ٱلْمُؤْمِنُونَ إِخْوَةٌ فَأَصْلِحُوا۟ بَيْنَ أَخَوَيْكُمْ ۚ وَٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ لَعَلَّكُمْ تُرْحَمُونَ

الحجرات ١٠

"ምዕመናኖች ወንድማማቾች ናቸው ፤ በሁለት ወንድሞቻችሁም መካከል አስታርቁ ፤ ይታዘንላችሁም ዘንድ አላህን ፍሩ ።" (ም ፵፱ ቁጥር ፲)

ይህን የወንድማማችነት ስሜት ለመፍጠር ፣ ለማስፋፋትና ለማጠናከር እርስ በእርሳችን መረዳዳትና ማናችንም የሌላውን ምዕመን ክብርና መብት ላለማስደፈር ዝግጁ ሆነን መገኘት ይኖርብናል ። ይህ ለምዕመናን ሕብረተሰብ ልዕልና ወሳኝ ጉዳይ ነው ። ይህንን በጎ መንፈስና ተግባር ለማጠንከር በምናደርገው ጥረት መጠን በአላህ ገመድ የመተሳሰር ዕድላችን ይጠናከራል ። በአፋጣኝም የተስተካከለ ሕይወት ለመምራት እንችላለን ። አላሕ (ሱ ወ) ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ሲያዝን እንዲህ ይላል ።

وَٱعْتَصِمُوا۟ بِحَبْلِ ٱللَّهِ جَمِيعًا وَلَا تَفَرَّقُوا۟ ۚ وَٱذْكُرُوا۟ نِعْمَتَ ٱللَّهِ عَلَيْكُمْ إِذْ كُنتُمْ
أَعْدَآءً فَأَلَّفَ بَيْنَ قُلُوبِكُمْ فَأَصْبَحْتُم بِنِعْمَتِهِۦٓ إِخْوَٰنًا آل عمران ١٠٣

“የአላህንም (የግመን) ገመድ፡ ሁላችሁም ያዙ ፡ አትለያዩም ፣ ጠበኞችም በነበራችሁ ጊዜ በናንተ ላይ (ያዋለውን) የአላህን ፀጋ አስታውሱ ፣ በልቦቻችሁም መካከል አስማማ ፣ በጸጋወም ወንድማማቾች ሆናችሁ ፣” (ም ፫ ቁጥር ፩፻፫)

በአንጻሩ ደግሞ በአላህ የአንድ ዓላማ ገመድ መተሳሰር ድልን የሚያጎናጽፈንን ያህል ፣ በግለኝነት ስሜት ተገፋፍተን አንዳችን ከሌላው የበላይነት ስሜቱን ለማንጸባረቅ የምናደርገው መሽቀዳደምና የምናስከትለው ግጭት አለመግባባትና ጥልን በመሃላችን ፈጥር ሊያዳክመንና ሊበታትነን መቻሉን ማስተዋል ያስፈልጋል ። ይህንንም ሐቅ ሁሉን አዋቂ የሆነ አላህ (ሱ ወ) እንዲህ ሲል አስገንዝቦናል ።

وَأَطِيعُواْ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ وَلَا تَنَـٰزَعُواْ فَتَفْشَلُواْ وَتَذْهَبَ رِيحُكُمْ ۖ وَٱصْبِرُوٓاْ ۚ إِنَّ
ٱللَّهَ مَعَ ٱلصَّـٰبِرِينَ الأنفال ٤٦

“አላህንና መልዕክተኛውንም ታዘዙ ፣ አትጨቃጨቁም ፣ ትፈራላችሁና ፣ ኃይላችሁም ትሄዳለችና ፣ ታገሱም ፣ አላህ ከትዕግሥተኞች ጋር ነውና ።” (ም ፰ ቁጥር ፵፮)

## 3.3 ከፈጣሪ ጋር በጥብቅ መተሳሰር የድል በር መክፈቻ ቁልፍ ነው

ምዕመናን በፍቅር ላይ በተመሠረተ መተባበርና መተጋገዝ የግልና የጋራ ጥረታችንን በማቀናጀት በአላህ (ሱ ወ) የተጣለብንን ኃላፊነት መወጣት የሚገባን መሆኑ ተገልጾዋል ። ዳሩ ግን ምዕመናን በመሐላችን ፍቅርን ልንመሠርት እንዴት እንችላለን ? እንዴትስ እርስ በእርስ የመረዳዳትና የግል ጥረታችንን ከጋራ ጥረታችን ጋር ለማቀናጀት እንችላለን ? የሚሉ ጥያቄዎች መነሳታቸው ስለማይቀር መልስ መስጠት ያስፈልጋል ።

ለዚህና መሰል ጥያቄዎች መልስ የሚሆን ከነቢዩ ሙሐመድና (ሰ አ ዓ ወ) በአካባቢያቸው የነበሩት ምዕመናን (ረ ዓ) አኗኗር የተወሰደ ፣ ለጋራ ድል የሚያስፈልጉ ነጥቦችን ያቀፈና የግለሰቡንም ድል ያልረሳ ! ፕሮግራም በመውላና መህመድ ኢልያስ ፣ (ረ ዓ) የቀረበ ስለሆነ አንባቢ እንዲያጤነው ከዚህ በታች እናሠፍራለን ።

3.3.1 እውነተኛና ከሁሉም በላይ የሆነ ታላቅ ጌታ አላህ (ሱ ወ) ብቻ ነው ። እኛ የእርሱ ባሪያዎች ፣ ተገዢዎችና አገልጋዮች ነን ።

“ላ ኢላሕ እልላ አላህ ፣” لا إله إلا الله

ሙሐመድ ረሱለ አላህ ፣ محمد رسول الله

የሚለው “ከሊማሕ” (ቃል) ይህንኑ ሃሳብ የሚያንፀባርቅ ነው ። ስለዚህ መንፈሳችን በቃሉ ተሞልቶ ተግባራችንም ሙሉ በሙሉ ለአላህ (ሱ ወ) ፈቃድ በመገዛት እስኪመራ ድረስ ቃሉን በአንደበታችን መደጋገም ፣ በጆሮዎቻችን መስማት በልባችን ማጽናት አለብን ።

3.3.2 ሶላትን መንፈሳዊ ግዴታችንን ለመወጣት ብቻ ሳይሆን ሕይወታችንን በሙሉ እንዲለውጠንና ከእርኩስና ፀያፍ ተግባር ሁሉ እንዲከለክለን ወቅቱን ጠብቀን በሙሉ ስሜት መፈጸም አለብን ። በሙሉ ስሜት የሚሰገድ ሶላት ከመጥፎ ተግባር የመሠወርና የመጠበቅ ኃይል ያለው ስለመሆኑ አላህ (ሱ ወ) ሲያረጋግጥ እንዲህ ይላል ።

إِنَّ ٱلصَّلَوٰةَ تَنْهَىٰ عَنِ ٱلْفَحْشَآءِ وَٱلْمُنكَرِ

العنكبوت ٤٥

"- - ሶላት ከመጥፎና ከሚጠላ ነገር ሁሉ ትከለክላለችና ፣ (ም ፳፱ ቁጥር ፵፭)

ለአላህ (ሱ ወ) ፈቃድ ራሳችንን ለማስገዛትና በታዛዥነት ለመሰለፍ የሚያበቃን ሌላው ዓቢይ ተግባር የረመዳንን ጾም በሥርዓቱ መጾምና በግል ፈቃድ የሚጾሙትንም መከታተልና መጾም ነው ።

በራሳችን ጥረትና ድካም በሐቅ ያገኘነውን ሀብት ልኩ (ሂሳብ) ሲደርስ አላህ (ሱ ወ) ግዴታ ያደረገውን (ዘካት) ምጽዋት ለባለ መብቱ መስጠትና በዘካትም ብቻ ሳንወሰን አቅማችን በፈቀደ መጠን ለችግረኛው መመጽወት ንብረታችንን ለአላህ ግልጋሎት ማዋያ ዘዴ ነው ።

ሀጅ ማድረግና ለአላህ (ሱ.ወ.) መንገድ "ለጂሃድ" (ለትግል) መሠለፍም ሰውነታችንና ሀብታችንም ለአላህ (ሱ. ወ.) ግልጋሎት የምናውልበት ሌላው ዘዴ ነው ።

3.3.3 የመጨረሻውን የአላህ (ሱ ወ) መልዕክት ያቀፈና ሕይወታችንን ልንመራበት የተሰጠን የተሟላ መጽሐፍ ቁርአን በመሆኑ በየቀኑ በሙሉ ፍቅርና አክብሮት ማንበብ አለብን ። ስሜትን የሚቀሰቀስ መልዕክቱ በመላ አካላችን ሠርጾ እንዲገባና በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ሕይወታችንን እንድንመራ ስሜቱ በውስጣችን ገንፍሉ እስኪወጣ ድረስ ንባቡን መቀጠል አለብን ። ከንባቡም ላይ ስመ ጥሩ የሆኑ የእስላም ምሁራን ስለቁርአን ትርጉምና ተግባራዊ ስለማድረጉም የጻፉዋቸውን ማጥናት ይናርብናል ። አላህ (ሱ. ወ.) ቁርአንን በማንበብ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረን ማስፈለጉን ሲገልጽ እንዲህ ይላል ።

وَلَقَدْ يَسَّرْنَا ٱلْقُرْءَانَ لِلذِّكْرِ فَهَلْ مِن مُّدَّكِرٍ    القمر ٤٠

"ቁርአንንም ለመገንዘብ በእርግጥ አገራነው ፤ ተገሣጭም አለን ?" (ም ፶፬ ቁጥር ፵)

3.3.4 የአላህ (ሱ.ወ.) ታላቅነት ከምናስበውና ከምንገምተው በላይ ነው ። ልዕልናውን ለማየት የምንችለው በሰጠን ፀጋዎች አማካኝነት ብቻ ነው ። ስለዚህ በቀን ውስጥ የአላህን (ሱ ወ) ታላቅነት የምናስታውስበት ጊዜ ሊኖረን ይገባል ። አላህን (ሱ ወ) ለማስታወስ በምንወስንበት ጊዜ ውስጥ ለምሳሌ ያህል ፤

"ሱብሃነ አላሒ ፤ ወልሀምዱ ሊላሒ ፤ — سبحان الله والحمد لله

ወላ ኢላሐ እልላ አላሁ ፤ ወልላሑ አክበር ፤ — ولا إله إلا الله ، والله أكبر

ወላ ሀውላ ወላ ቁወታ ኢልላ ቢልላሒ — ولا حول ولا قوة إلا بالله

አልዓልዩል ዓዚም ፤" (ከሊመቱ ተምጂድ) العلي العظيم (كلمة التمجيد)

ይህ ቃል ከሊማቱ ተምጂድ አላህን (ሱ.ወ.)ለማሞገስ የተመረጠ ቃል ስላሆነ በቀን አንድ መቶ ያህል ጊዜ ቢደገም ፤

"አስተግፊሩ አላሓ አልዓዚም — استغفر الله العظيم

አልለዚ ላ ኢላሐ እልላ ሑዋ — الذي لا إله إلا هو

አልሀዩ አልቀዩም ወአቱቡ ኢሌይሒ" — الحي القيوم وأتوب إليه

ይህ ቃል (ከሊመቱ አልኢስቲግፋር) ለበደላችን ተጸጽተን የአላህን እዝነት የምንጠይቅበት ምርጥ ቃል ስለሆነ በቀን ለአንድ መቶ ጊዜ ያህል መድገም ፤

"አልላሁማ ሰሊ ወሠሊም ዓላ ሠይድና — اللهم صل وسلم على سيدنا

ሙሐመድ ፤ ወዓላ አሊ ሠይድና ሙሐመድ ፤ — محمد وعلى آل سيدنا محمد

ይህ ቃል ለነቢያችን ሙሐመድ (ሰ.አ.ዓ.ወ.) አላህን (ሱ.ወ.) የምንለምንበት ቃል በመሆኑ በቀን ለአንድ መቶ ጊዜ ያህል መድገም ፤

እነዚህንና ሌሎችንም የአላህና የነቢያችንን ስም ለማስታወስ የሚረዱ ምርጥ ቃሎችን በቅን ልቦና ፤መድገም ባሕልን ፈጥረን ማዳበር አለብን ።

3.3.5 የእስላምን ዲን በመቀበል ለአላህ (ሱ ወ) ተገዥና አገልጋይ ለመሆን ለወሰኑ ሰዎች ርህራሄና አክብሮት ማሳየት ይኖርብናል ። ለእነርሱ የሚገባውን መስ ጠትና ከሚጎዳቸውም መቆጠብ ያስፈልጋል ። ከሌላው ይልቅ ለእነርሱ ቅድ ሚያ መስጠት ይገባል ።

ወደ አላህ(ሱ.ወ.)ለቀረቡና የዲኑ ዕውቀትና ጥበብ ባለቤት ለሆኑት ፤ እንዲሁም የአላህን አደራ ተቀብለው ለሚጠብቁት ልዩ ፍቅርና ጥልቀት ያለው አክብ ሮት ማሳየት ይኖርብናል ።

ነቢያችን ሙሐመድ (ሰ.አ.ዓ.ወ.) ይህን ነጥብ አስመልክተው ሲያስጠነቅቁ ፤ "ለታናሾቹ የማይራራና ታላቆቹንም የማያከብር ከእኛ ጉራ አይደለም፤እንዲ ሁም እኛን ለማታለልና ለማጭበርበር የሚፈልግም ከእኛ ጉራ አይደለም ፤ አንድ ሙስሊም ለራሱ የሚወደውን ለወንድሙ እስካልወደደ ድረስ (ከምዕ መናን ጉራ) (ሙዕሚን) ሊሆን አይችልም" ብለዋል ።

ስለዚህ ግንም ሰው ከላይ የተዘረዘሩትን ነጥቦች አጥብቆ እስኪያዘና እስከሠራ ባቸው ድረስ "የድል በሩን መክፈቻ ቁልፍ" ሊጨብጥ ይችላል ። አንባቢም በቅን መንፈስ በመነሳት ይህንኑ ሞክሮ ለማረጋገጥ ይችላል ። ከዚህ የተሻለ መንገድ ቢገኝ ኖሮ በዚያው መንገድ በመጓዝ ውጤቱን ለማየት በተቻለ ነበር ፤ ግን ስለሌለ አልተቻለም ።

## 3.4 ለጥሪ ተግባር ዝግጅት

በአካባቢያችን በሰፈነው ድክመት ምክንያት በግል ውጤት ማግኘት ብቻ በቂ አይሆንም ። ነቢዩ ሙሐመድና (ሰ.አ.ዓ.ወ.) በአካባቢያቸው የነበሩት ምዕመናን (ረ ዓ) እንዳደረጉት ሁሉ የአላህን (ሱ ወ) መመሪያ በተግባር ላይ

እያዋልን ሌላውን ሕዝብ ወደ አላህ (ሱ ወ) መመሪያ “ከመጥራት ተግባር” ጋር በማዋሐድ ድክመቱን ለማስወገድ ያላሰለሰ ጥረት ያስፈልጋል ።

ይህን ተግባር በጋራ ተነስተን ከፈጸምን ለሕብረተሰቡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ውጤት ለማስገኘት እንችላለን ። ምክንያቱም አላህ (ሱ ወ) ለዚህ ተግባር እስከተሰለፍን ድረስ እንዲህ ሲል ቃል ገብቶዋል ።

وَٱلَّذِينَ جَٰهَدُواْ فِينَا لَنَهْدِيَنَّهُمْ سُبُلَنَاۚ وَإِنَّ ٱللَّهَ لَمَعَ ٱلْمُحْسِنِينَ

العنكبوت ٦٩

“እነዚያም በኛ መንገድ የታገሉ መንገዳችንን በእርግጥ እንመራቸዋለን ፣ አላህም በእርግጥ ከበጎ ሠሪዎች ጋር ነው ።” (ም ፳፱ ቁጥር ፷፱)

ደዕዋ በቅድሚያ ራሱን ወደ ቀናው መንገድ መመለስ መሆኑን ተገንዝቦ የሚከተሉትን መፈጸም ይጠይቃል —

3.5.4.3 ባጠቃላይ ለምዕመናን ትሁት መሆን ፣ በአክብሮትና ለዘብ ባለ ቃል ማነጋገር ፣ እንዳቸውንም በንቀት አለመመልከት ፤ ለቁርአንና ሀዲስ ማሳየት የሚገባንን አክብሮት የቁርአንና የሀዲስ ዕውቀት ባለቤት ለሆኑት የእስላም ዲን ምሁራን (ዓሊሞች) ማሳየት ፤ አለብን ። (ዓሊሞችን መናቅና ማቃለል ሃይማኖቱን እንደመናቅ ስለሚቆጠር የአላህን (ሱ.ወ.) ቁጣ ሊያስከትል ይችላል ።)

3.5.4.4 ጊዜን ሐሰት በማውራት ፣ በሐሜት ፣ በጠብ ፍለጋና ሌሎች ፋይዳ ቢስ በሆኑት ጉዳዮች ላይ ከማጥፋት ይልቅ የሃይማኖት መጽሐፍትን በማጥናት የራስን ዕውቀት ከቀን ወደ ቀን ማዳበርና ለአላህ (ሱ.ወ.) አገልግሎት በተሠማሩበት ወቅት ራስን ጠብቆ ጊዜንም ከዚህ በታች በተጠቀሱት ተግባሮች ላይ ማዋል ያስፈልጋል ።

ሀ/ ዲንን በጋራ በማስተማርና መማር ምግባር ፤

ለ/ ቁርአንን በማንበብ ፣ አላህን (ሱ.ወ.) በማወደስ እና የዲንን መጽሐፍት በማጥናት ፤

ሐ/ የጥሪውን ተግባር ዓላማ በማሳወቅና ሰዎች በጥሪ ተግባር ተካፋይ እንዲሆኑ ማድረግ ፤

3.5.4.5 የዕለት ጉርስን ንፁሕና ትክክለኛ በሆነ መንገድ ብቻ ማግኘት ፣ ገንዘብ ስታ ወጣ መቆጠብ ፣ ሆኖም ለቤተሰብና ለዘመዶች በእስላም ዲን ማድረግ የሚገባን በሙሉ ማድረግ ፤

3.5.4.6 በማይረቡ ክርክሮችና ውይይቶች አለመሳተፍ ፣ ጥሪን መሠረታዊ በሆኑ የእም ነት ነጥቦች ላይ ብቻ መወሰን ፤

3.5.4.7 የሃይማኖት ምግባር ፍሬያማ ሊሆን የሚችለው በንፁሕ ልቦና ሲሠራ ብቻ በመሆኑ ተግባርህን በእውነተኛውና ንፁሕ በሆነ ስሜትህና ሃሳብህ ማሳመር ያስፈልጋል ።

የዚህ ተልእኮ ተሳታፊ ለመሆን ግንባር ቀደም መለኪያው ንፁሕ ልቦና ነው ።

መታየትና ማስመሰል በዚህ ዕቅድና ተግባር ውስጥ ሥፍራ ስለማይኖረው መጠንቀቅ ግዴታ ነው ።

ለዚህ ምዕራፍ መደምደሚያ እንዲሆን ስመ ጥሩ የሆኑ የእስላም ዲን ምሁር ኢማም ኸዛሊ (ረ.ዓ.) ካደረጉትና ካስተላለፉት መልዕክት የሚከተለውን እናቀ ርባለን ።

በኢማም ኸዛሊ ዘመን የእስላም ዲን ተጠናክሮ ስለነበረ ትምህርት ቤቶችና የዲን ማዕከሉች በተማሪዎችና በምዕመናን ሞልተው ነበር ። ሆኖም ኢማሙ የጥሪ (መልዕክት) አስተላላፊዎችን አስፈላጊነት በመገንዘብ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል ።

"አንድ ሰው ስህተቱን እስካላወቀ ድረስ አዋቂዎች የማሳወቅ ግዴታ አለባ ቸው ። እያንዳንዱ ምሁር (ዓሊም) አንዳንድ አካባቢዎችን በኃላፊነት መያዝ ይኖርበታል ፤ (ለምሳሌ ፤ ከተማን ፣ መንደርን ፣ መስጊድን ፣ ወዘተ - -) ለዝሕቡ መልካሙንና ጎጂውን ፣ የተባረከ ተግባርና የተረገመ (እርኩስ) ተግባርን ፣ እንዲሁም አስፈላጊውን መመሪያ መስጠት አለበት ። ለዚሁም ሥራ ሰዎች እስኪመጡለት መጠበቅ የለበትም ። ወደ ሰዎቹ የተቀደሰውን መልእክት ለማስተላለፍ መሄድ አለበት ። "ዓሊሞች" (የዲን ምሁራን) የነቢያት ምትክ ናቸው ። ነቢያት ያልተማሩትን ሰዎች ብቻቸውን ትተው አያውቁም ። ቀና ውን መንገድ የማያውቀውን አግኝተው ለማስተማር ከቤት ቤት ሄደዋል ። መንፈሳዊ ሕመም ያለበት ሰው ብዙውን ጊዜ አያውቀውም ። እፊቱ ላይ ቆሻሻ ያለበት ሰው በመስተዋት ካላየው ወይም ሰው ካልነገረው እንደማያው ቀው ሁሉ መንፈሳዊ ሕመም ያለበትም ሰው ለራሱ አያውቀውም ። የእስላም መሪዎች በየሠፈሩ "ዓሊሞች" (የእስላም ዲን ምሁራን) የመመደብ ግዴታ አለባቸው ። ሰው አላዋቂ ሆኖ ስለሚወለድ አስተማሪ ያስፈልገዋል ።" "ይህች ዓለም በሕመምተኞች ተሞልታለች ፤ በመሬት ውስጥ ሙታን አሉ ፤ ከምድር በላይ ሕመምተኞች አሉ ፤ መንፈሳዊ ሕመምተኞች ከሥጋዊ ሕመም ተኞች እጅግ ይበረከታሉ ።" ብለዋል ።

እንዲሁም ኢማም ኸዛሊ "መሠረታዊውን የዲን ትምህርት ሕዝቡ አለማወቁ አሳሳቢ ነው ። እያንዳንዳችን ስለምናውቀው ጉዳይ ምሁር ነን ፤ ማስተማር ግዴታችን ነው ። መሠረታዊውን እንኳ ለማስተማር ጊዜው ስለማይበቃን በጥቃቅን ጉዳይ ፀጉር በመሰንጠቅ ጊዜያችንን እናጥፋ ፤ እርሱን ጥቂቶች ካወቁት ይበቃል ።" ብለዋል ።

ስለዚህ ጊዜ ሳንፈጅ ለጥሪ እንነሳ ! አላህም (ሱ ወ) እንዳለው ድሉን ይሰጠናል።

﴿ نصر من الله وفتح قريب وبشر المؤمنين ﴾

الصف ١٣

وآخر دعوانا أن الحمد لله رب العالمين

مطابع الدار الهندسية /القاهرة
تليفون / فاكس (٢٠٢) ٥٤٠٢٥٩٨

المكتب التعاونى للدعوة وتوعية الجاليات بمكة المكرمة
ص . ب : ٣٧٧٤ هاتف : ٥٧٤٤٩٦٦ - ٥٣٤٦١٨٩ فاكس : ٥٣٦٠٥٩٤